# ወንጌል ለሁሉም

(ተሻሽሎ የተዘጋጀ)



አዘጋጆች
መጋቢ ሽፈራው ፈይሳ
እና
ወንጌላዊ ነገዎ ቦሰት

አዘጋጅ

መንፈሳዊ መጽሐፍት የቴሌግራም ቻናል

https://t.me/amharicspritualbooks

# ማውጫ

**መግቢያ**

**ምዕራፍ** **ገጽ**


1. ወንጌል ለሁሉም ........................................ 2
   መ.ጋቢ. ሽፈራው ፈይሳ

2. ጸሎትና የወንጌል አገልግሎት ........................................ 22
   ወንጌላዊ ነገዎ ቦሰት

3. ወንጌል ለኢ.ኦ ተዋህዶ አማኞች ........................................ 34
   አቶ ጸ.ጋዬ ደምሴ

4. ወንጌል ለሙስሊሞች ........................................ 48
   አቶ አንዋር መሐመድ
   እና
   አቶ ሽፈራው ሰይድ

ዋቢ. መጽሐፍት (Bibliography) ........................................ 72

# መግቢያ

ወንጌል ማለት የምሥራች ሲሆን ደራሲውና ባለቤቱ ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ወንጌልን የምሥራች ያሰኘው እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ለሰዎች የሰጠው የጽድቅ/የደህንነት ስጦታ ነው። ወንጌልም የሚያወራው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና በሥጋ እንደ ተወለደ፣ስለ ሰዎች ኃጢአት ሲልም እንደሞተና የሞትንም አስፈሪነትና የበላይነትን በትንሣኤው ኃይል ሽሮ ከሞት እንደተነሣ ነው።

ይህ የማዳን ኃይል የሆነው ወንጌል ጠላቶች አሉት። እነርሱም ዲያቢሎስና የእርሱን ዓላማ ለማስፈጸም ራሳቸውን ሰጥተው በሰማይና በምድር ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የጨለማ ኃይላት ናቸው። የጦርነታቸውም ትኩረት እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የገለጠው ጽድቅ ለሰዎች እንዳይበራላቸው ልባቸውን ማጨለምና የጽድቁን ምሥራች አብሳሪዎችንም እንቅስቃሴ መግታት ላይ ነው።

ከላይ ከተጠቀሰው ምክንያት የተነሣ የወንጌል አገልግሎት ከበድ ያለ መንፈሳዊ ተጋድሎን በእጅጉ ይጠይቃል። የመጋደያውና የማጥቂያው መሣሪያ ደግሞ ጸሎት ነው። ይህ መሣሪያ (ጸሎት) የማይሻር፣የማይለወጥ፣ብርቱ ኃይል ያለውና በጠላት ላይ የማጥቃት እርምጃን ለመውሰድ የሚያስችል ነው። ከዚህም ባሻገር ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት የምንታገዝበትን ኃይል፣ምሪትና የወንጌል ፍሬትን ብርሃን ከመንፈስ ቅዱስ የምንቀበልበት ሁነኛ መንገድ ነው።

ጸሎት ጌታና የቀደሙ የእምነት አባቶቻችን በአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ በብዙ የታገዙበት፣ የጨለማን ሠራዊት የረቱበትና ዓላማቸውንም ያፈረሱበት ትልቅ ድማሚት ነው፡ የድላቸው መሠረትና የአገልግሎታቸው ስኬት ምስጢርም ይኼው በብርቱ መሣሪያነቱ የታወቀ ጸሎት ነው። ይህ የሚያስረዳን ከጸሎት ተጋድሎ ውጭ ወንጌል ወደ ማንም ሊደርስ የማይችል መሆኑን ነው።

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳትም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ቁልፍና የጨለማን ሠራዊት ለማጥቃት ወሳኝ ኃይል መሆኑ ጎልቶ መገለጡ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በዚህ መጽሐፍ ሁለተኛ እትም ላይ መሻሻል ተደርጎበታል።

መጽሐፉ ታትሞ ለዚህ ወሳኝ አገልግሎት እንዲውል ለፈቀዱ ለአፍሪካን ኢቫንጀሊስቲክ ኢንተርፕራይዝ መንፈሳዊ አገልግሎት ዳይሬክተር ለሆኑ ለዶ/ር መልሳቸው መስፍን፣በመቀጠልም ጊዜያቸውን፣ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን በሠፊው ቆርሰው በመስጠት ትምህርታዊ ጽሑፋቸውን አስተዋጽኦ ላደረጉ ለወንድም ጸጋዬ ደምሴ፣ለወንድም አንዋር መሐመድና፣ ለወንድም ሽፈራው ሰይድ እንዲሁም ደግሞ ስለ መጽሐፉ ገንቢ አስተያየትን በመስጠት ለተባበሩን ለወንድም ማሙሻ ፋንታሁን፣ ለወንድም ጌታቸው በለጠና፣ ለወንድም ፈቀደ ተፈራ በመጨረሻም በብዙ ድካም የጽሑፉን ሥራ በመሥራት አገልግሎቷን ላበረከተችው ለእህት ራሔል አንበርብር ልባዊ ምሥጋናችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

አዘጋጆች
መጋቢ ሽፈራው ፈይሣና ወንጌላዊ ነገዎ ቦሰት

# ምዕራፍ አንድ

## ወንጌል ለሁሉም
በመጋቢ ሽፈራው ፈይሣ

## የወንጌል ሥርጭት አስፈላጊነትና ባህርዩ

ወንጌልን ማሰራጨት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን እንደሞተና እንደተነሳ ቅዱስ ቃሉ በሚያዘው መሠረት በእርሱ ለሚያምኑ የኃጢያት ይቅርታና የዘላለም ህይወት እንደሚሰጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እውነትን ማወጅ ነው። የወንጌል ሥርጭት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን አዳኝና ጌታ ታሪክ የሚመሰክርለትንም እውነት በማስረገጥ ሰች በግላቸው እንዲያውቁትና ከእግዚአብሔር አብ ጋር እንዲታረቁ የምንሰጠው አገልግሎት ነው። ሰችን ለወንጌል መጋበዝና ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ማድረግ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ያደርገው የነበረ አገልግሎት ሲሆን ወደ እርሱ ሲጠራቸው ራሳቸውን ክደው መስቀሉን ብቻ ተሸክመው እንዲከተሉት ያዝዝ ነበር። ስለዚህ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ውጤት ለክርስቶስ መታዘዝን፣ ከቤ ተክርስቲያን ጋሩ መተባበርንና ለዓለም የሚገባውን ኃላፊነት የተሞላበት አገልግሎት መስጠትን ያካትታል።

### I. ወንጌል ስርጭት ምንድነው ?

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ወንጌላውያን በሉዛን ከተማ ባደረጉት አጠቃላይ ስብሰባ ስለ ወንጌል ሥርጭት ገለፃ በመስጠት የቃል ኪዳን ሃሳብ አውጥተው ነበር። በዚያ ስብሰባ ለወንጌል ስርጭት የሰጡት ትርጉም በአጭሩ ወንጌል ስርጭት ማለት «የወንጌልን የምስራች ላልሰሙት ማዳረስ ነው» ብለዋል። የወንጌል ሥልጣን በፍሬው ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ዓላማ ማድረግ ያለበት ሰችን ለክርስቶስ በመማረክ ላይ መሆን ይኖርበታል። ሥልጣኑ ሲገለጥ ፍሬው ይመጣል። በእግር ኳስ ጨዋታ ጎል ካልገባ በስተቀር ውጤት እንደማይቆጠር ሁሉ በወንጌል ስርጭት አገልግሎት ሰች ካልዳኑ የወንጌል ስልጣኑ አልታየም ማለት ነው። በአጠቃላይ አነጋገር የወንጌል ስርጭት በተለይ ላልሰሙ፣ ላልተረዱና ምላሽ ላልሰጡ ለተረሱ ሁሉ ሰች ወንጌልን ማወጅ ነው።

### II. ወንጌል ምንድነው ?

ወንጌል «የምስራች» ነው። የምስራች በራሱ የተለያዩ የይዘት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። ለየምስራቹ ቃል የምንሰጥውም አቀራረብ እንዲሁ ሊለያይ ይችላል። የምስራቹን ይዘት በተመለከተ የሉዛኑ ኮንፍራንስ የሰጠው መግለጫ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን ሞተ ቃሉም እንደሚናገር ከሙታንም ተነስቶ በክብር በማረግ በጌትነቱ ነገሰ አሁን ንስሐ ገብተው በስሙ ለሚያምኑት የኃጢያት ይቅርታ በመስጠት ለመንፈሳቸው ዕረፍትና ደህንነትን ይሰጣቸዋል» የሚል ነው።

ስለሆነም የወንጌሉ የመልዕክት ይዘት አራት ነጥቦችን ይይዛል።

(1) የወንጌሉ ወቅት
(2) የወንጌሉ ምስክርነት
(3) የወንጌሉ ተስፋች
(4) ወንጌሉ የሚጠይቀው ነገር

# እነዚህን አራት ነጥቦች በጥቂቱ እንተንትናቸው፣

## 1. የወንጌሉ ወቅት (ጊዜ)

በወንጌሉ የመልዕክት ይዘት ውስጥ ወቅትና ጊዜን አስመልክቶ ልናተኩር የሚገባን በጌታ የሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ መሞት፣ መነሳት፣መመለስና እነዚህን ወቅቶች በእውነት በታሪክና ቀለል ባለ መንገድ የወንገጌሉን ማዕከላዊ ሃሳብ ሳንለቅ መልዕክቱን ማስተላለፍ መቻል ነው:: ሌሎች ወቅቶችና ጊዜያት ለምሳሌ ትምህርቱና የፈውስ አገልግሎቱ አስፈላጊ ቢሆኑም ከላይ የጠቀስኳቸውን ሃሣቦች ከወቅቱ ጋር ለማገናኘት ጠቀሜታቸው አነስተኛ ነው:: ቢሆንም በመልዕክታችን ይዘት ውስጥ ዋናው ነጥብ የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ነው::

## 2. የወንጌሉ ምስክርነት

ሐዋርያት የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ እንደ ቃሉ (ሐዋ/ሥራ 2:25፣ 3:18-24፣ 1ቆሮ 15፣ 3-4) እንደ የዐይን ምስክርነታቸው (ሐዋ/ሥራ 2፤32፣ 5፤32) አውጀውታል:: ዛሬ እኛ የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ እንደ ሐዋርያት የዐይን ምስክሮች ሁነን ባንሰብክም የመጽሐፍ ቅዱሱን እውነት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን ምስክርነት ከሐዋርያት ቀጥሎ ምስክር በመሆን እናውጀዋለን::

## 3. የወንጌሉ ተስፋዎች

ሞትን ድል አድርጎ በተነሳው ጌታ ሁለት ተስፋች ተሰጥተውናል:: እነርሱም በእርሱ በማመን የኃጢአትን ይቅርታና የመንፈስ ቅዱስን ሥጦታ እንደምንቀበል ናቸው::

## 4. ወንጌሉ የሚጠይቀው ነገር

ከላይ የጠቀስናቸው ሦስቱ ነጥቦች ለሁሉም ሰዎች የሚሆኑ ሳይሆን ይህንን እውነት በንሰሐና በእምነት ለሚቀበሉ ሰች ብቻ ነው:: ንስሐ ማለት «የአመለካከትና የአቅጣጫ መቀየር» ጉዳይ እንጂ የቦታ ለውጥ ማድረግ ብቻ ማለት አይደለም::

## III. ወንጌሉን ለሌሎች እንዴት እናቅርበው?

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በንዑስ ሰነት ሌሎችን ነጥቦች ወደፊት ብናነሳም ጥቅት ሃሳቦችን ስንዝረን ለማለፍ እንሞክራለን:: ወንጌል ሊቀርብና ሊተላለፍ የሚችለው ሦስት ነገሮችን በማድረግ ነው:: እነርሱም (1) በአካል በመቅረብ (Presence) (2) በውይይት (Dialouge) እና (3) ወንጌሉን በማወጅ (Proclamation) ነው:: ወንጌሉን በአካል ቀርቦ ለሌሎች መናገር ለአንድ ክርስቲያን ለወንጌሉ የሚሰጠውን ትልቅ ዋጋና አክብሮት ያመለክታል:: ወንጌሉን በግል በማህበረሰብ መካከልና በተቃዋሚች ውስጥያ ዘልቆ በመግባት ማስተላለፍ መቻል እጅግ በጣም አስፈላጊ ሥራ ነው:: ሌላጡ ወንጌሉን ይዞ ወደ ሌሎች ሄዶ መናገርና ለመወያየት መፍቀድ የሌሎች አመለካከትና ሃይማኖታዊ ይዘትን የበለጠ በጥልቀት ለመረዳት ያስችላል:: በአካል ቀርቦ መናገርም ሆነ በውይይት ፈቅዶ ወንጌሉን ማስተላለፍ በራሱ ወንጌልን ማወጅንም እንደሆነ ያሳያል:: በውይይት ማቅረቡ በዚያው አካባቢ ወቅትና ጊዚያዊውን ሃሳብ ሲያመለክት ወንጌሉን ማወጅ የሚለው ሦስተኛው ሃሳብ ግን ጠቅላላና ዘላለማዊውን የሆነውን የወንጌል አቅጣጫ ፈለግ እንድንከተል ያመለክተናል::

## IV. ወንጌሉን ለምን እንሰብካለን?

ቀላሉና አጭሩ መልስ ወንጌልን ለሌሎች የምንሰብከው ሰዎች በግላቸው ወደ ጌታ እንዲመጡና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ነው:: ዋናው ዓላማ ይህ ሆኖ እያለ በቀጣይነት የምናከናውናቸው ተግባራት ደግሞ አሉን:: እነዚህም በክርስቶስ የሚያምኑት ወንዶችና ሴቶች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነው እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት በቤ/ክ እንዲያድጉ ነው:: በአራቱም ወንጌላት የምናገኘው የታላቁ ተልዕኮ መልዕክት ግብ ሰዎች ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ነው:: (ማቴ 4፤19፣ሐዋ/ሥራ5:29፣ማቴ10፤38)

## V. የወንጌል ሥርጭት ውጤቶች

ከላይ የተመለከትናቸው የወንጌል ስርጭት ውጤቶች በሶስት ነጥቦች ላይ ያተኩራሉ:: እነዚህም

1. ለክርስቶስ መታዘዝ
2. ከቤተክርስቲያን ጋር መተባበር
3. በዓለም ውስጥ ኃላፊነት በሚሰማው አገልግሎት መሳተፍ

ለክርስቶስ መታዘዝ ስንል እውነተኛ እምነትና ንስሐ በሚያዩን ሁሉ ፊት ሲኖረን እንደሚገባ ነው:: መንፈሳዊውም ሆነ ግብረገባዊው ኑሯአችን ለጌታም ሆነ ለሰች በግልጥ መታየት አለበት በማቴ7፤21 ላይ ጌታ የሱስ ክርስቶስም «የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጅ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ በሙሉ ወደ መንግስተ ሰማያት አይገባም» ብሏል:: መታዘዝን ባላካተተ ሁኔታ ለብቻው ክርስቶስን በአዳኝነቱ መቀበል አንችልም:: ክርስቶስን በአዳኝነቱና በጌትነቱ እንወደዋለን ስንል ሐዋርያው ዮሐንስ እነደጻፈው «እግዚአብሔርን እወደዋለሁ ካልን ትዕዛዙንም እንጠብቃለን» (1ዮሐ 5:3) ጌታየሱስም «የሚወደኝ ትዕዛዜን የሚጠብቅ ነው» ብሏል ዮሐ 14:21

ሁለተኛው ከቤተክርስቲያን ጋራ መተባበር የሚለው ሀሳብ ደግሞ ወደ ክርስቶስ መምጣት ማለት ወደ እርሱ ቤተሰብ መምጣትም ጭምር ነው:: በአዲስ ኪዳን ያሉ ሰባኪዎች ወንጌል ስርጭት አካሂደው ሰዎች ወደ ጌታ ከመጡ በኋላ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲጨመሩ አያደርጉም ነበር የሚለው የማይታሰብ ነገር ነው:: ከቤ/ክ ጋር መተባበር አዲሱ አማኝ በቤተክርስቲያን በሚታየው ህብረት ተጨምሮ መያዙ የቃሉን እውነተኛነት በታማኝነት መግለፁን አመልካች ነው::

ሦስተኛው በዓለም ውስጥ ኃላፊነት በሚሰማው አገልግሎት መሳተፍ ነው:: በክርስቶስ አዲስ የተለወጠው አማኝ ወደ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ኃላፊነት በጎደለው የኃጢአት እስራት ውስጥ የነበረ ሲሆን ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ኃላፊነት በተሰማው ሕይወት ይቀጥላል:: በዓለም ያሉ ሰዎች በቀላሉ ወደ ጌታ አይመጡም በዓለም ያሉትን ሰች ስንወዳቸውና በጎ ምግባራችንን ስናሳያቸው በቀላሉ ልባቸውን ለወንጌል እንዲከፍቱ ያደርጋቸዋል:: በደህንነትና በሥነምግባር መካከል ምንም ልዩነት አይኖርም የዳንን ሰች ከሆንን በጥሩ ስነ ምግባር ለዓለም ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንችላለን:: (ያዕ2:14-17) ኤፌ2፤8 10)

## በግል የወንጌል ስርጭት አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ማምጣት

ሰውን ወደ ክርስቶስ ማምጣት አስቸጋሪ ሆኖ የሚገኘው ክርስትያኖች ፍርሃት ሲይዛቸው ነው:: ፍልስጤማዊውን ጎልያድን መጣል ያቃታቸው እስራኤላውያንን ዳዊት እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር ድል አድረገው:: ሰውን ወደ ጌታ ማምጣት ትልቅ ዕድልና ልናጣው የማይገባን ክብር ነው:: በዚህ ክፍል የምንመለከተው በግል ለሚደረግ የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴ በቅድሚያ አንዳንድ መነሳት የሚገባቸውን መነሻ ሃሳቦች በመዳሰስ ይሆናል::

## እንዴት እንስራው?

### በመጀመሪያ

እኛ ለራሳችን ክርስቶስን በግል ማወቃችን ቅድሚያ የሚሠጠው አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: ያ ካልሆነ ዕውርን የቀለም አይነቶችን አስረዳኝ ብሎ እንደ መጠየቅ ይቆጠራል:: በግል ከክርስቶስ ጋር የግል ህብረት ከሌለን ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት ይከብደናል:: የግላችን ምስክርነት ይህም እንዴት ጌታ ህይወታችንን እንደለወጠውና ጌታን ከተቀበልን በኋላ ያለንን የህይወት ለውጥ ልዩነት ማሳየት ይጠበቅብናል::

## ሁለተኛ

ሰዎች ጌታን ባለማግኘታቸው እየጠፉ እንዳለ ጠንካራ የሆነ መረዳት ሊኖረን ይገባል። ሉቃ15 ን ይመልከቱ ስለመጥፋት ጉዳይ ጌታየሱስ በዚህ ምዕራፍ ሦስት ምሳሌችን አቅርቧል። የጠፋው ድሪም በአካባቢው ሁኔታ የጠፋውን የጠፋው በግ በተፈጥሮ ምክንያት መጥፋቱ የጠፋው ልጅ በምርጫው ምክንያት መጥፋቱን ያመለክታል። በአካባቢያቸው በተፈጥሮና በምርጫቸው ምክንያት የጠፉትን ሰዎች ለማዳን ጌታ ዛሬም አስቸኳይ ጥሪ አለው። «የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና» ሉቃ19:10

## ሦስተኛ

ሰዎችን የማፍቀር ባሕርይ ልናዳብረው የሚገባን አስፈላጊው ጉዳይ ነው። በዋጋ የማይተመነውን የብዙ ሰዎችን ሕይወት ለብዙ ሺ ያህል ጊዚያት ጌታ በመንገዳችንና በእጃችን ሰጥቶን ምንም ሳናደርግ የምናልፍበት ወቅት ብዙ ነው። በግላችን ከአንድ ሰው ጋር ስለ ክርስቶስ የምናደርገው ውይይት ሰውየው ራሱን ለጌታ አሳልፎ እንዲሰጥ መርዳቱ አይቀርም ወይም ከዚህ በፊት ስለ ክርስቶስ የሰማ ሰው ሊሆን ይችላል። አሁን በመንፈስ ቅዱስ መረዳት ከአንተ (ከአንቺ) ጋር ያደረገው ውይይት ደግሞ በተጨማሪ ትልቅ እገዛ ይኖረዋል። በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ውይይቱን እንጀምር ቀጣዩ እርምጃ ምን እንዲሆን አናውቅምና ፤

## የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት (ዮሐ 4)

በግል ለሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት የየሱስ ምሳሌነት በጣም አስፈላጊውን እገዛ የሚያደርግልን ነው። ታሪኩ ጥልቅና ድንቅ ነው። ከዚህ ምዕራፍ በመነሳት አንዳንድ ቁልፍ መመሪያችን እንመልከት፣

### 1. ንቁ መሆን

ጌታ እየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ፍለጋ ሲሄዱ እስኪመለሱ ድረስ በሲካር ጉድጓድ አጠገብ ቁጭ ብሎ የምትመጣውን ሴት ይጠባበቅ ጀመር። ከዚህ የተሻለ ቦታ እንደሌለ አውቆ ተዘጋጅቶ ጠበቀ።

### 2. ግንኙነትን መፍጠር

ግንኙነቱን ንግግር በማድረግ ጀመረ «የምጠጣው ውሃ ስጭኝ» ይህ የጥሩ ንግግር መጀመሪያ አካሄድ ነው። የሰዎችን ሁኔታ ተመልክተን ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ግንኙነትን መፍጠር ይቻላል።

### 3. ፍላጎትን የሚያነሳሳ ነገር መናገርና መግለጥ

ጌታ የሱስ ለሳምራዊቷ ሴት የንግግር ግንኙነትን ጀምሮ አሁን ፍላጎቷን በሚያነሳሳ ነገር ንግግሩን ቀጠለ። የሕይወት ውሃ (4:10 16) «ጌታ ሆይ ይህን ውሃ ስጠኝ» አለችው። ጌታ የሱስም ትኩረቷን አገኘ።

### 4. በግልፅ መናገር

የሕይወትን ውኃ ከማግኘቷ በፊት በሕይወቷ የነገሰው ኃጢአት መነካት ነበረበት ጌታ የሱስ አምላክ ስለሆነ በውስጧ ያለውን ያውቃል። በንግግራችን ወቅት ሰዎች ችግራቸውን ሳይናገሩ ቸኩለን ኃጢአታቸውን ለመግለፅ አንሞክር።

# ክፍል ሁለት

ከላይ ከተመለከትናቸው አስፈላጊ ነጥቦች በኋላ በመቀጠል ንግግራችንን ወደ ማጠቃለል እናምጣው:: ወደ ውሳኔ የሚመጡት ሰዎች ሊያደርጓቸው የሚገቡ ሦስት መሰረታዊ ነገሮች አሉ::

1. ክርስቶስን በግላቸው መቀበል አለባቸው (ዮሐ 1:12) ለሰዎች ይህንን በሚገባ ማስተማር ይኖርብናል:: እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ሥጦታ እጃቸውን ዘርግተው ሊቀበሉ ይገባል እርሱም የሚሰጣቸው ይቅርታውን፣ አዲስ ልደትን፣ ዘላለማዊ ሕይወትንና በመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን ኃይል እንዲኖሩ ማድረግ ነው::

2. ክርስቶስን በጌትነቱ ተቀብለው ራሳቸውን መስጠት አለባቸው

3. ልባቸውን ለክርስቶስ መክፈት አለባቸው (ራዕይ 3:20)

# ከወሰኑት ሰዎች ጋር መፀለይ

ከውሳኔ በኃላ አብሮ መፀለይ ያስፈልጋል:: ጸሎታችንም ቃል በቃል ሆኖ እኛ እየመራናው መሆን አለበት:ምክንያቱም በዚህ ወቅት ስለ ፀሎት ግንዛቤ ስለሌላቸው ነው::

# ቀጣዩን እርምጃ ለእነርሱ መግለፅ

ከፀሎት በኃላ ሊያውቋቸው ስለሚገቡ ነገሮች መግለፅ ይገባል:: ይህም ለእምነታቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል::

1. ዋስትና እንዳላቸው መግለፅ (ራዕይ 3:20 ሮሜ 8:38 39 1ዮሐ 5:11-13)

2. በየቀኑ እንዲፀልዩ መግለፅ

3. በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነቡ ማበረታታት

4. ወደ ቤ/ክ እንዲሄዱ ማደፋፈር

5. ለሌሎች እንዲመሰክሩ ማበረታታት ድብቅ ደቀ መዝሙር ሳይሆኑ እምነታቸውን ማበረታታት ይገባል::

6. ቀጣይ ግንኙነት መፍጠር (በስልክ፣በቀጠሮ፣በደብዳቤ) አስፈላጊ ሁሉ ክትትል ሊደረግ ያስፈልጋል::

# ቤ/ክንን ለወንጌል ማነሳሳት

ታዋቂው እንግሊዛዊ ሰባኪ ቻርልስ እስፐርጅን ለቤ/ክ ሙሉ ግዜ አገልጋዮች እንዲህ ብሏቸው ነበር «በአገልግሎታችሁ ወደፊት ሂዱ ልታደርጉ የሚገባችሁንም ሁሉ አድርጉ ከምትናገሩት ነገር ይልቅ የምትሰሩት ሥራ ማን መሆናችሁን ይገልፃልና»
ለዛሬዋ ቤ/ክ ያለው መልዕክት ይህ ነው:: ከቀን ቅዠት አምልጠን ለጌታችን ቢያንስ አንድ ነገር ማድረግ ፣ ይኖርብናል «*Do something* ! »

የብዙ አብያተክርስቲያናትን ጊዜ የሚበላው በአብዛኛው የኮሚቴ ስራ ነው:: ውይይት፣ብዙ ውይይት፣እጅግ በጣም ብዙ ውይይት ሰይጣን ከዳር ቆሞ ይስቃል ከምንም ነገር ይልቅ ብዙ ኮሚቴችና ድርጅቶችን ከመመስረት ይልቅ ነፍሳትን ለማዳን እንነሳ!

## 1. ወንጌልን ማዳረስ የቤ/ክ የመጀመሪያ ሥራዋ ነው

የጌታችን የመጨረሻ ቃል የእኛ የመጀመሪያ ሥራ ሊሆን ይገባል:: የሐዋ/ሥራ 1:8 ቤ/ክ ለወንጌል ሥራ ካልወጣች ለጊዜው እንደተሟሟቀ ክሰብ ትሆናለች ካልወጣች በስተቀር በምንም ምክንያት የተሟሟቀው ክሰቧ ሲያድግ መፍረሱ አይቀርም:: ዛሬ የብዙ ቤ/ክናት የውስጥ ግጭት ምክንያት ወደ ውጭ ለወንጌል ባለመሄድ ምክንያት የሚፈጠር ነው:: ብዙ ሰዎች በቤተክርስቲያናችን ስለወንጌል ስርጭት ግድ ስለሌላቸው አገልግሎቱንም አያከናውኑትም:: አንድ ወቅት ታዋቂው የአሜሪካ ወንጌላዊ ዲ ኤል ሙዲ ዘንድ አንዲት ሴት መጥታ እንዲህ አለችው: «ሚስተር ሙዲ ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት የምትጠቀምበትን መንገድ አልወደውም» አለችው:: ሙዲም ሴትየዋን «ማዳም አንቺስ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ታደርጊያለሽን?» ብሎ ጠየቃት እርሷም «አላደርግም» ብላ መለሰችለት እርሱም ምንም ከማታደርጊው ከአንቺ እኔ የማደርገውን መንገድ እመርጣለሁ» ብሎ መለሰላት:: የወንጌል ስርጭት አገልግልት የወንጌላዊውንና የመጋቢው ስራ ብቻ አይደለም ሥራው የሁላችንም ነው:: በቤ/ክ ያሉ ሙሉ ጊዜያቸውን ያልሰጡ ሰችን የበለጠ እየተጠቀምንባቸው ስንመጣ በቤ/ክ የእስታትቲክስ መረጃ የምናገኘው እውነት ከሌሎች ተሞክሮች ይልቅ ብዙች ወደ ቤ/ክ የሚጨመሩት በቤ/ክ አባላት በግል በሚያደርጉት የወንጌል ምስክርነት እንደሆነ እንገነዘባለን:: እ.ኤ.አ በ1973 ዓለም አቀፍ የወንጌላውያን ቤ/ክናት መሪዎች ለምክክር በተሰበሰቡበት ጉባኤ ከአራት ሺ መሪዎች ውስጥ ሦስት ሺቹ ወደ ጌታ የመጡት በግል በተደረገላቸው የወንጌል ምስክርነት እንደሆነ ታውቋል::

## 2. ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት ዕቅድ አውጡ

ዓላማችን እግዚአብሔርን በአካባቢያችን ማስከበር ቢሆንም ለዕቅዳችን የሚሆኑ ግቦች ደግሞ ያስፈልጉናል:: ግቦቻችንም ዓላማችንን የሚያሳካ መሆን አለበት:: ዓላማው ጠቅለል ያለ ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማስፈፀም የሚረዱን ሁለት የግብ ባሕርያት

1. ሊፈፀም የሚችል ግብ
2. ሊለካ (ሊመዘን) የሚችል ግብ ናቸው::

እነዚህን ካከናወንን በኋላ ራሳችንንና ሌሎችን ማንቀሳቀስ ይኖርበናል::
ሌሎችን ተንቀሳቀሱ ብለን እኛ ዘወር ካልን ውጤታማ ልንሆን አንችልም እያንዳንዱ የቤ/ክ አባል ሳይቀር ለዚህ ስራ መንቀሳቀስ ይኖርበታል:: መጋቢው ወይም የቤ/ክ መሪው አባላቱን በሙሉ ለማንቀሳቀስና ለማሰልጠን ኃላፊነቱ የእርሱ ነው::

## 3. የወንጌል ስርጭቱን ስልት መጠበቅ

እያንዳንዱ ቤ/ክ የራሷ ስልት ሊኖራት ይችላል:: በላቲን አሜሪካ ውስጥ በፈጣን ሁኔታ እያደገች ያለች አንዲት ቤ/ክ የምትጠቀምበትን ስልት ቀጥለን እንመልከት ቃላቱ በእንግሊዘኛ ሲያያዝ R-A-C ይባላል::

***R= Reflection***
***A= Action***
***C= Consolidation***

ይህንን ሃሳብ በመቀጠል በትንታኔ እንመልከት

## *Reflection* (ማንፀባረቅ)

ቤ/ክ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራምን ማሰብና መሥራት ስታቆም ሁለት የወንጌል አገልግሎት ታላቅ አደጋች ይገጥሟታል::

1. መልዕክቷን መለወጥ

2. ዘዴዎችን ላለመለወጥ እምቢተኛነት ማሳየት

ቤ/ክናት ምንጊዜም ግምገማን መፍራት የለባቸውም በአሜሪካን አገር የሚገኝ አንድ የኤሌክትሪክ ካምፓኒ በየዓመቱ ሠራተኞችን የሚጠይቀው ጥያቄ አለው።፡

1. የበለጠ ለማምረት እያደረግነው ያለ ጥረት ምንድነው?
2. የፈለግነውን ያህል አምርተናል?

ወደ ቤ/ክ መለስ ብለን ደግሞ ልንጠይቃቸው የሚገቡን ጥያቄች አሉ «የቤ/ክናችን መዋቅር ወጣ ብለን በወንጌል ሰዎችን እንዳናመጣ ከልክሎናል ወይንስ አልከለከለንም? «የቤ/ክናችንስ አመራርስ እንዴት ነው?» «የቤ/ክ አባላት ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት ፈቃደኝነት አላቸው?» ፈቃደኛ ካልሆኑ ለምን? በግምገማችን ሂስን የመቀበል ልምድ ልናደርግ ይገባል ግምገማውን የማይወዱ ሰዎች በተቻላቸው አቅም ለግምገማ የሚሆኑ በሮችን ሁሉ ይዘጋሉ፡፡

## *Action*- (ድርጊት)

በድርጊት እንቅስቃሴው ውስጥ ቀዳሚው ፀሎት ነው። ስለ ድርጊት የትኛውንም ያህል ብናወራ ፀሎት ከሌለ ፍሬያማ አይሆንም ፀሎት በፊታችን ላለው እግዚአብሔር ለሚሰጠን ድል ራሳችንን ሰጥተን የምናገለግለው አገልግሎት ነው። መሰረቱን ካልጣለ የፀሎት አገልግሎት ይህንን ታላቅ ኃላፊነትና ሥራ ይዘን መውጣት አንችልም።ቀጣዩ ጉዳይ ደግሞ ራዕዩን ተቀብለው ከሚወጡ ሰዎች ጋር ለሥራው መውጣት ነው፡ (1ዜና 4:10) ራዕዩን ሰዎች ካመኑበት እያንዳንዱ የቤ/ክ አባል ራሱን ጊዜውን ገንዘቡን ይሰጣል በድርጊት ውስጥ የሚካተቱ ጉዳዮች

- ለምስክርነት መውጣት
- የተለያዩ ኮሜቴች መዋቅርን ማዘጋጀት
- ሥልጠና (ቅድመ ወንጌል ሥርጭትና ክትትል)
- አገልጋዮችን መጋበዝና ጊዜውን ማረጋገጥ
- የመገናኛ ብዙሀንን መጠቀም
- ትራክትና በራሪ ወረቀቶች ማዘጋጀት የበታ ዝግጅት ወዘተ

## *Consolidation* (ሕብረት መፍጠር)

ከወንጌል ስርጭቱ እንቅስቃሴ በኃላ አዳዲስ አማኞችን ማበረታታት ማጽናናትና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። ከክትትል በኂላም ደቀመዝሙር የማድረግ ተከታታይ ዕቅድ ሊነደፍ ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

**በአንዲት አጥቢያ ቤ/ክ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ማለት ራሳችንን የምናስታጥቅበት፣ የምንገመግምበትና በግላችን ለሚኖረን የወንጌል ምስክርነት የምንነሳበት ነው። የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ለአንዲት ቤ/ክ የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይሆንም፡፡**

## በጉብኝት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት (*Visitation Evagelism*)

የዚህ አገልግሎት ዓላማ ሰዎችን በቤታቸው ሄዶ በመጎብኘት ወንጌልን የመመስከር አገልግሎት ነው። ሰዎችን የምንጎበኛቸው

ሲታመሙ
ልዩ ፕሮግራም ሲኖራቸው (ሠርግና ልደት)
በወሊድ ጊዜ
በኃዘን ጊዜ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

# በጉብኝት አገልግሎት በወንጌል ሌሎችን መድረስ ያለብን ለምንድነው?

## አንደኛ

የተልኮአችን አንድ ክፍል ስለሆነ ነው::«ሂዱ» የሚለው የታላቁ ተልዕኮ ትዕዛዝ መሄድን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህም ሄደን ሰዎችን ልናገኝባቸው የሚገቡ ዕድሎችን ሁሉ መጠቀም ያስፈልጋል::

## ሁለተኛ

የቀድሞዋ ቤ/ክ ይህንን ታደርግ እንደነበረ በአ/ኪዳን ተገልጧል በሐ/ሥራ 20:20 ጳውሎስ «ከቤት ወደ ቤት » ይሄድ እንደነበረ ተናግሯል የይሖዋ ምስክሮችና ሞርሞኖች ይህንን ዘዴ በጣም ይጠቀሙበታል:: እኛ የጌታ ሰዎች የበለጠ መጠቀም ስንችል ያለመጠቀማችን ያሳዝናል::

## ሦስተኛ

## ደቀመዛሙርት በጌታ ታዘው ሄደዋል ሉቃ 10:1-3 ማን ያድርገው ?

ይህ ኃላፊነት በቤ/ክ ያሉ የሁሉም አባሎች ኃላፊነት ነው:: ይህም ሲባል በየሰንበቱ የሚመጡና የቤ/ክ አባል የሆኑትን መጨመር የለበትም:: በቤ/ክናችን የሰንበት ትምህርት የሚማሩ ልጆች ወላጆቻቸው አማኝ ካልሆኑ በእነርሱ በኩል ወይም በመምህሮቻቸው በኩል በሚደረግ ጉብኝት ማድረግ ይቻላል:: በኃዘን ላይ የሚደረግ ጉብኝትም ውጤት ከፍተኛ ነው::

# የጉብኝት ዓላማችን ምንድነው?

የጉብኝት ዓላማችን የባላአደራነት ኃላፊነት ለመወጣት ብቻ አይደለም:: ቤ/ክ የሚኖራት ኃላፊነትና ግዴታ ተወጥታ ወንጌልን ለሌሎች ለማድረሰ ጭምር እንጂ ፣ አንዳንድ የቤ/ክ አባላቶችን በቤት ውስጥ ፕሮግራምና በጉብኝት ወንጌልን ማስፋፋት እንደሚቻል ልናስተምራቸውና ልናሳያቸው ይገባናል:: አሁን በመላው ዓለም እየተሰራጨ የሚገኝ አልፋ(*Alpha*) የሚባል ፕሮግራም አለ:: ይህ ፕሮግራም ዓላማው ሰዎችን ሕብረት በማድረግ ወንጌልን እንዲሰሙና በክትትል ትምህርት እንዲያዙ የሚረዳ አገልግሎት ነው:: ቤ/ክ መምጣት የማይደፍሩ ሰዎች በቤት ውስጥ በሚደረጉ አገልግሎቶች በቀላሉ ሊመጡ ይችላሉና::

# አንዳንድ ተግባራዊ ጉዳዮች

በጉብኝት በሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ልናከናውናቸው የሚገቡት ተግባራዊ ጉዳዮች ይህንን ይመስላሉ::

1. የመጋበዣ ወረቀት ማዘጋጀትና መላክ
2. ሰዎች ከሌሉ መልዕክቱን መተው
3. በጓደኝነት መንገድ ግልፅ ውይይት ማድረግ
4. የሚጠቅማቸውን የክትትል ትምህርት ወረቀቶች ማዘጋጀት
5. ከቤ/ክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት መወያየት
6. ከጌታ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት መወያየት
   በቤታቸው ስለሚፈልጉት ጉዳይ ተወያይቶ መፀለይ
7. ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራት

# የእግዚአብሔር ሥራና ታማኝነት

ሉቃ 10:17 «...ሰባቹም በደስታ ተመለሱ»
**ደቀመዛሙርት** በደስታ መመለሳቸው በእርግጥም ያስደስታል ቁ 21 ላይም ጌታየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት ማድረጉን እንመለከታለን፡፡ የጌታ ሥራ በታማኝነት በልጆቹ በኩል ሲከናወን እግዚአብሔር ደስ ይለዋል፡፡ ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ቢወርድም የጌታን ሥራና ታማኝነት መግታት አይችልም፡፡

# አዲስ አማኞችን መከታተል

በእንግሊዝ አገር አንድ ሰው ትልቅ የወንጌል ስብሰባ አደረገ ከፕሮግራሙ በኋላ በቀጠለው የክትትል ትምህርት ጊዜ ምላሽ ሰጥቶ በስብሰባው የተገኘው አንድ ትንሽ ልጅ ብቻ ነበር፡፡ ቢሆንም ፕሮግራሙን ያዘጋጀው ሰው ስለዚህ ትንሽ ልጅ እግዚአብሄርን አመስግኖ በእምነትና በቃሉ ያሳድገው ጀመር፡፡ የዚያም ልጅ ስም ጆን ስቶት ይባላል፡፡ እኚህ ሰው ዛሬ በፅሁፍ፣በስብከት በነብይነት አገልግሎት በሌሎች ላይ የሚያሳድሩት ከፍተኛ የሆነ ተፅእኖ አላቸው፡፡ የሳቸው እምነት መነሻ ያ ሰው ትንሽ ነው ብሎ ባለመናቅ የሰጣቸው ክትትል ነው፡፡ የክትትል አገልግሎት ለአዳዲስ አማኞች ትኩረት ሰጥቶ በማሳደግ ከቤ/ክ ጋር ሕብረት እንዲቀጥል ማያያዝ ነው፡፡ አዲስ አማኝ በስጋ እንደተወለደ አዲስ ሕፃን ስለሆነ ብርቱ ክትትል ያሻዋል፡፡

## አዲሱ አማኝ የሚያስፈልጉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

### 1. መመገብ 1ጴጥ 2:2

አዲስ አማኝ ሊያድግ የሚችልባቸውን ምግቦች መመገብ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህም

- ሳያቋርጥ ቤ/ክ እንዲሔድ
- በግሉም ሆነ ከሌሎች ጋር ጌታን እንዲያመልክ
- ሕብረት ከጌታና ከሌሎች ጋር እንዲኖረው ማድረግ
- በግል መፅሐፍ ቅዱስ እንዲያነብ
- የክርስትያን መፃሕፍትን እንዲያነብ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

### 2. መጠበቅ 1ጴጥ 5:8

አዳዲስ አማኞች ከጠላት ጥቃት እንዲጠበቁ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ጌታየሱስ በዘሩ ምሳሌ ላይ ይህንን በሚገባ አስተምሯል አዳዲስ አማኞችን ለመጠበቅ

- የበሰሉ ሰች እንዲያስተምሮአቸው
- ከተስፋ መቁረጥና ከእውነት መንገድ እንዳያስቱ ማድረግ (ማቴ 16:11) 2ጴጥ 2:1)

### 3. ማስልጠን ቆላ2:6 7

## አዳዲስ አማኞችን እንዲያድጉ ማሰልጠን የምንችለው እንዴት ነው?

1. የደህንነታቸውን ዋስትና እንዳገኙ በማስተማር (1ዮሐ 5:13)
2. የማያቋርጥ የፅሞና ጊዜ እንዲኖራቸው በማበረታታት (2ጢሞ 2.15) (2ጢሞ 3:16)
3. የፀሎት ሕይወትን እንዲያዳብሩ በማስተማር (1ተሰ 5:17)
4. እምነታቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ በማበረታታት (1ጴጥ 3:15)
5. ዕለታዊ ሕይወታቸው በመታገዝ እንዲጠነክር በመርዳት (ያዕ 1:22) (ዮሐ 3:36) ሊሆን ይችላል፡፡

# የበለጠ ለመከታተል

1. የግል ግንኙነት ማድረግ
2. በደብዳቤ (በስልክ ) የማያቋርጥ ግንኙነት መፍጠር
3. የማያቋርጥ ፀሎት (ቆላ 1:9 ፣ኤፌ 1.17 19)
4. በቡድን መመገብ (ማሳደግ)

በአንድ ላይ እንደሆኑ በማስተማር መከታተል አብረው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል፡፡ ክትትልና ሰዎችን ደቀመዛሙርት ማድረግ የሚከብድ አገልግሎት ቢሆንም ፍሬው የበለጠ ነው፡፡ (ዮሐ 15:16) (ዮሐ 8:31) እውነተኛ ደቀመዛሙርትን የምናፈራው ዋጋ ከፍለን ማገልገል ስንችል ብቻ ነው፡፡

# የጓደኛነት የወንጌል ሥርጭት
# (FRIENDSHIP EVANGELISM)

## ድልድዩን መገንባት ይቻላል

ስለ ወንጌል ስርጭት ስናስብ የሚሰማን ስሜት ምንድነው? የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ምንም ዓይነት ፍርሃት ሳይሰማን በደስታ ልናገለግለው የሚገባን አገልግሎት ነው፡ የተጠራነው ሁላችንም ምስክሮች እንድንሆን እንጂ ወንጌላውያን እንድንሆን አይደለም፡፡ (ማቴ 28:18 -20) ድልድዩን እንዴት እንደምንገነባ መማር እንደሚያስፈልገን እግዚአብሔር እንድንማር ይፈልጋል ፡፡

### ሀ. የጓደኝነት ድልድይ የማንገነባው ለምንድነው?

1. አሳሳት ይሆን የሚል የመሳሳት ፍርሀት (ሐዋ/ሥራ 1:8)
2. ተቀባይነት የማጣት ፍርሃት (ዮሐ 15:18)
3. መቀደሴን አጣ ይሆን (ቅድስናን የማጣት ፍርሐት (ዮሐ17:15)
4. የዕውቀት ማነስ ፍርሐት (ዮሐ 9:25)
5. የመከሩን ጥሪ አለማየት (ማቴ 9:35 38)

### ለ. ድልድዩን መገንባት ያለብን ለምንድነው ?

1. የኢየሱስ ምሳሌነት (ሉቃ15)
2. የእግዚአብሔር ፍቅር
3. የሰዎች ፍቅር
4. የክርስቶስን ትዕዛዝ ለመታዘዝ

### ሐ. ድልድይ በአጥር ላይ ያለው እንቅፋት (*Bridges Versus barriers*)

አንድ ሰው በመንገድ ላይ ብንገናኝ ስለ ክርስትና ብንጠይቀው ብዙ መልሶችን ሊሰጠን ይችላል፡፡ በክርስትና ውስጥ የሌሉ ሰዎች ስለክርስትና ያላቸው ቅድመ አመለካከት የተለያየ ነው፡፡ (ሰዎች የሚነግሩዋቸውን በጋዜጣ ያነበቡትን ወይም በቴሌቭዥን ያዩትን ነገሮች ክርስትና አድርገው ይወስዷቸዋል ቀድመው የሚሰሙዋቸው ነገሮችም ከፍተኛ ተፅዕኖ በኑሮአቸውና በስሜታቸው ላይ ያመጣል፡፡ ከዚያም በኋላ ከኄታየሱስ ጋር ያላቸውን የግል ግንኙነት እንዳይፈጥሩ አጥር ይሆንባቸዋል፡፡ ስለሆነም ሰዎች በውስጣቸው ደብቀው ላስቀመጧቸው ጉዳዮችና ክርስቶስን እንዳይቀበሉ ለሚከላከሉባቸው ነገሮች ድልድይ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

## ጌታ ኢየሱስን እንዳይቀበሉ በሰዎች ልብ የተደበቁት ታላላቅ ነገሮች ምንድናቸው ?

1. የግዴለሽነት ዋሻ (የብዙ ሰዎች ፍላጎት ብዙ ነው መብላት መጠጣት ማግባት ወዘተ...
2. የባሕል ዋሻ «ከሰመድኩት ነገር መላቀቅ አልፈልግም»
3. የምቾት ፍለጋ ዋሻ «ጥሩ ኑሮ እኖራለሁ ከዚህ ሌላ ምን ያስፈልገኛል»
4. በራስ የመተማመን ዋሻ «እኔ ሰው ገድዬ አላውቅም ወይም ሰርቄ አላውቅም »የሚል ቃል በመናገር

## ድልድዩን ለመገንባት እንዴት እንጀምር ?



| የእኛ ችግሮች | የእነርሱ ችግሮች |
|---|---|
| • ፍርሃት | ግዴለሽነት |
| • ተቀባይነት የማጣት ፍርሀት | ባህል |
| • የመበከል ፍርሃት | ምቾት ፍለጋ |
| • የዕውቀት ማነስ | በራስመተማመን |
| • የመከሩን ጥሪ አለማየት | |

## ሀ. ፀሎት

*«ከሰዎች ጋር ስለ እግዚአብሔር መነጋገር ታላቅ ነገር ነው፡ ስለ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ግን የበለጠ ታላቅ ነገር ነው»*
*ኢ.ኤም በውንድስ*

### 1.መፀለይ አለብን

**1.1 ለመልዕክተኞች (ማቴ 9:37**

**1.2 ስለሚከፈቱ በሮች (ዕድሎች )ቆላ 4:3-4**

**1.3 በድፍረት ለመናገር ኢፌ 6:19-20**

**1.4 በዙሪያችን ግንኙነት ላለን ቡድኖች**

**1.5 ለመንፈሳዊ ውጊያ (2ቆሮ 4:3 4)**

## ሀ. በዙሪያችን ያሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ምን ይመስላሉ?

### ሥራ

1. የሥራ ተባባሪ
2. ምሳ አብሮን የሚበላ
3. አለቃ
4. ደንበኛ
5. ቅጥር ሰራተኛ
6. የቀድሞ የሥራ ባልደረባ

### ባለ ሙያ

1. ፀጉር አስተካካይ (የውበት ሳሎን)
2. የከብት ሐኪም
3. የፖስታ ቤት ሠራተኞች
4. የጋራዥ ሰራተኛ
5. ሐኪም
6. የሕግ ባለሙያ
7. የጥርስ ሐኪም
8. የኢንሹራንስ ተወካይ
9. የሂሳብ ባለሙያ

### ቤ/ክርስቲያን

1. መጋቢ
2. የሰንበት ት/ቤት አባላት
3. የአገልግሎት ቡድን አባላት
4. የቅርብ ጓደኛ
5. የተለያዩ አገልጋዮች ሕብረት
6. ጎብኝች
7. የቤተሰብ አባላት

### ቤተሰብ

1. የቅርብ ዘመዶች
2. የጋብቻ ዘመዶች
3. አማካሪ
4. የት/ቤት ወይም የኮሌጅ
5. የቤተዘመድ ጉባኤ

### ማሕበራዊ

1. ጓደኞች
2. የቴኒስ ክለብ
3. የሕፃናት መምሕራን
4. የሕፃናት ቤተሰብ ህብረት
5. ጎረቤቶች

በአካባቢያችን ግንኙነትን የበለጠ ለማጠናከር መሠረት ለመጣል

- ✓ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ተጠቀሙ
- ✓ ስለእነርሱ ለማወቅ ጥያቄችን ጠይቁ
- ✓ ጥሩ አድማጮች ሁኑ
- ✓ የማገልገል ዕድሎችን ተጠቀሙ
- ✓ አካሄዳችሁን አስተካክሉ
- ✓ መንፈሳዊ ዘርን ለመዝራት ዕድሎችን ተመልከቱ
- ✓ ጊዜውን ላለመውሰድ ጥረት አድርጉ
- ✓ ትዕግስተኛ ሁኑ

## ለ. የወንጌል ስርጭት ዘዴችን ወይም አቀራረባችን ምን ይመስላል ?

ከዚህ በታች የምናያቸው ስድስት አቀራረቦች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት የተለየ አስተዋፅዖ ያላቸው ሂደቶች ናቸው:: የተጠቀማችሁባቸውን በሳጥኑ አጠገብ ባለው ባዶ ቦታ ምልክት ስታደርጉ ያልተጠቀማችሁባቸውን ደግሞ አስባችሁ በተግባር አውሉት::

### ❑ ፊት ለፊት በመጋፈጥ (*Confrontational* )

ምሳሌ ሐዋ/ሥራ 2፣ጴጥሮስ

- በመተማመን
- በድፍረት
- በቀጥታ
- በትንሽ ንግግር በቀጥታ ወደ ነጥቡ መምጣት
- ጠንካራ መረጃትን በመግለፅ

### ❑ በዕውቀት ( *Intellectual* )

ምሳሌ ጳውሎስ ሐዋ/ሥራ 17

- በትንታኔ
- በጥበብ ነገር ( *Logical* )
- በመጓጓት
- በክርክር
- ሰዎቹ የሚፈልጉትን የሚያስቡትን በመገንዘብ

### ❑ በምስክርነት *(Testimonial)*

ምሳሌ በዮሐ 9 የሚገኘው አይነ ስውር

- በግልፅ ግንኙነት
- በጥሩ አድማጭነት
- በግላዊ ህይወት
- በአስደናቂ ህይወት ጌታ እንዴት እንደተገናኘን
- የራስን ወይም የመሰሎችን ምስክርነት በመናገር

### ❑ በሰዎች ጥልቅ ነገር ላይ በማለፍ *(Interpersonal)*

ምሳሌ በአጋንንት የተያዘው ሰው ማር5:19

- በንግግር
- በርኅራኄ
- በጥንቃቄ
- በጓደኝነት
- የሰዎች ፍላጎት ላይ በማተኮር
-

### ❑ በመጋበዝ *(invitational)*

- ምሳሌ የሰማርያዊ ሴት ዮሐ4
- በጥሩ አቀባበል
- በማሳመን
- ከአዲስ ሰዎች ጋር ስብሰባ ማድረግ መውደድ
- ላመኑት ነገር ራሳቸውን በመስጠት
- በተለየ ዕድል ለወንጌል ስርጭት መውጣትን ማየት

- **በማገልገል (Servant hood)**

ምሳሌ ጣቢታ (ዶርቃ) ሐዋ/ሥራ 9:36

- በትዕግስት
- ሌሎችን ያማከለ
- የሌሎችን ደስታ አይቶ መደሰት
- ከቃላት ይልቅ ፍቅርን በተግባር ማሳየት
- የአገልጋይነት ሥራ ከዋጋ ጋር መገናኘት

# በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት (PRAYER EVANGELISM)

በእጃችን ያለ መፅሐፍ ቅዱሳዊው ትኩረትና ማረጋገጫ እግዚአብሔር መልክዓ ምድርን ተመልክቶ መስራት እንደሚፈልግ ሰይጣንም ይህንኑ ለማድረግ ይሞክራል የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴና ከተማን በወንጌል የማዳረስ ስልትን አስመልክቶ ሁሉ የሚነጋገርበት ጉዳይ እየሆነ ነው።

ለሥራው ስኬታማነት በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ከፍተኛ የተሳካና ውጤታማ በመሆን ላይ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ላይ የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤ/ክ ካለ ስልክና ኢንተርኔት አገልግሎት እንዴት ውጤታማ ልትሆን ቻለች?

**(ሐዋ/ሥራ 2:44)**
**ውጤቱ ምን ነበር?**
**ሐዋ/ሥራ 5:27 ተመልከቱ**

«ትምህርቱን በኢየሩሳሌም ሞልታችሁታል»

## የፀሎት የወንጌል እንቅስቃሴ ገለፃ

«በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስር- ት እንቅስቃሴ ማለት ስለ እግዚአብሔር ከጎረቤትህ ጋር ከመነጋገርህ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ጎረቤትህ ተነጋገር (ፀልይ) ማለት ነው»። ***«Prayer Evangelism is talking to God about your neighbor before you talk to your neighbor about God»***

በ1 ጢሞ 2:1-8 በእያንዳንዱ ልንፀልይበት የሚገባንን ሃሳቦችና የተሰጠንን ትዕዛዝ ሲያመለክት ሃሳቡን እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው መዳን አጥብቆ እንደሚፈልግ ፣ የኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ቤዛ አድርጎ አንዱ ለሁሉም መስጠቱን ያመለክታል።

በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ፕሮግራም ሳይሆን በሂደት የሚከናወን ቤ/ክን በፀሎት አገልግሎት ያለችበትን ከተማ እንድታንቀሳቅስ በሰማያዊው ሥፍራ ስለሚድኑት ውጊያ የምታደርግበት ነው ይህም በከተማዋ የእግዚአብሔር መንግስት እንዲመሰረት፣ የጠፉት እንዲድኑ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕልውና እንዲረዱ፣ኃይሉን ተገንዝበው እርሱን መፍራት እንዲጀምሩ በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት እገዛ ያደርጋል።

በፀሎት የሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት አራት ቀላል የሆኑ ደረጃች አሉት።«ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ፡- ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ» «ወደምትገቡበት ከተማ ሁሉ ቢቀበሉዋችሁ ያቀረቡላችሁን ብሉ በእርሷዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና የእግዚአብሔር መንግስት ወደ እናንተ ቀረበች በሉዋቸው»ሉቃ 10:5፣8፣9፣

የፀሎት የወንጌል ስርጭት መመሪያዎች በተለያዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ተጠቅሷል:: በሉቃስ 10:5፣8፣9፣ ላይ የተባለው ሃሳብ ግን ትክክለኛ ምሳሌነቱን አመልካች ነው:: እነዚህ አራት ደረጃች

1. ለሰዎች ሰላምን መናገር
2. ከሰዎች ጋር ሕብረት ማድረግ
3. የሰዎችን ፍላጎት ማሟላት
4. ለሰዎች ወንጌልን መመስከር ናቸው::

እነዚህ አራት ደረጃች አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዙ ናቸው አንዱ ከሌላው ጋር አይቀዳደሙም:: ቅደም ተከተሉን ጠብቆ መሄድ ይኖርበታል:: በከተማው የምትገኝ አንዲት ቤ/ክ የአካባቢዋን ሰዎች በክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ የምታደርገው ፀሎት ከፍተኛ ለውጥን ያመጣል::

## *III. ሦስት መሰረታዊ እውነቶች*

1. እውነት ቁጥር 1፣- ኅብረተሰባችን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ፀሎት መሳሪያ ነው ( 1 ጢሞ 2:1-8)
2. እውነት ቁጥር 2፣- ሰይጣን የሚጠፉ ሰዎች እንደጠፉ እንዲቀሩ ይሰራል 2ቆሮ 4:3
3. እውነት ቁጥር 3፣- ክፉ እንዲሸነፍ በሰማይ ያሉ ኃይላትን ማሸነፍ ያስፈልጋል ስለከተማችን ያለ ውጊያ የሚካሄደው በዚያ ነው::

## በሰማያዊ ሥፍራ መንፈሳዊ ሥልጣን የምናገኘው እንዴት ነው?

- ❑ መዝ 133:1. ኤፌ 4:3
  መልሱ በአጭሩ በሕብረት ነው:: ቀጣዮቹን ጥቅሶች ይመልከቱ:-
- ❑ መዝ 133:1. 2 ጴጥ 3:9
- ❑ ዮሐ 17
- ❑ መዝ 13:35
- ❑ ኤፌ 4:3

ፀጋ እንዲፈስልን ቢያስፈልግ ሕብረት አስፈላጊ ነው ፀጋው በሕብረታችን በአካላችን ውስጥ ካልፈሰሰ ከአካላችን ውጭ አይፈስም::

ሰይጣን በከተማ ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚገኘው እንዴት ነው?

- ኃጢአት ሲሰጥን
- ቁጣ ሲበዛ (ኤፌ 4፣26)
- የሰይጣን ምሽግ ሲኖር ነው:

## በከተማች ለሚገኙ በጎች እረኛ መሆን

1. የከተሞችና የሕዝቦች እረኛ የመሆን ግዴታችን ለምንድነው?
   - ክርስቶስ መስዋዕት የሆነው ለሁሉም በጎች ነው::
   - ሕዝብን ሁሉ ደቀመዝሙር የማድረግ ኃላፊነትና ኃይል ስለተሰጠን ነው::
   - በማቴ 28:17 20 እንደተገለፀው «ሂዱ» ስለተባልን ነው ይህ ታላቁ ተልዕኮ ከተሰጠ ጀምሮ የሚፈፀመው 33 ከመቶ ብቻ ነው::
2. እኛ «እረኛ» የምንሆንላቸው «በጎች» ያሉት የት ነው?
   - ቤ/ክ ውስጥ
   - ጎረቤቶቻችን
   - የሥራ ሥፍራችን
   - በመንግስት መስሪያ ቤት
   - በት/ቤት

3. እረኛው ምን መምሰል አለበት?
    - እያንዳንዳችን ልንሆን እንችላለን።
    - ወደ ብርሃን የፀሎት ቤቶች (*Light houses of prayer*) እንግባ

በየመንገዱ የጉዞ ፀሎት ካደረግን በኋላ በወንጌል ለምንደርሳቸው ቤቶችና ቤተሰቦች ልንፀልይ እንችላለን።

የብርሃን የፀሎት ቤት ማለት በቀላሉ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ አማኞች አንድና ከአንድ በላይ የሆኑ አማኞች ስለሚጠፉት ሰዎች ደህንነት ማግኘት ተሰምቷቸው አካባቢያቸውን ጎረቤታቸውን የሥራ ሥፍራና ት/ቤትን በፀሎት ኃይል ተፅዕኖ በማድረግ ወደ ጌታ እንዲመጡ የምናደርግበት ቤት ነው።

ብርሃን የፀሎት ቤት ማለት የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የፀሎት ስብሰባ የቤት ፀሎት ቤት (ቤ/ክ) ማለት አይደለም ቁጥራቸው ከ5-10 መሆን አለበት።

ትኩረታቸው በረከት ከማግኘት ፀሎት ይልቅ በመንፈሳዊ ውጊያ ላይ ያተኮረ ይሁን «በመንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ የእግዚአብሔር የበረከት እጅ ሁልጊዜ የመርገም እጆችን ትመታለች።» «መርገም ሊሰበር ይችላል፣አንድ ጊዜ የተለቀቀ በረከት ግን ተመልሶ አይገኝም።»

4. በብርሃን ፀሎት ቤት የሚገኝ ኃይል የሚያገኙና የሰይጣንን ሥፍራ የሚያስለቅቁ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ?
    - መጋቢች
    - ማላጆች
    - ወጣቶች
    - ሕፃናት
    - የሥራ ሥፍራች ባለቤት ያሉ ሰች ናቸው።

5. አንድንድ ማሳሰቢያች
    - «የውሻ እረኛ ወይ ይጮሃል ወይ ይናከሳል » እንደዚያ አንሁን እውነተኞች የነፍሳት እረኞች እንሁን።
    - የመንፈሳዊ መነቃቃት ጠላት ያለፈው የመነቃቃት ጊዜ ነው። ስለሆነም ባለፈው በነበረን መነቃቃት አንተማመን
    - በመንፈስ ቅዱስ ሥራና በሚድኑት ነፍሳት አነስተኛ ቁጥር መርካት አይታይብን።
    - መነቃቃት ማለት ከሞት መነሳት እንደሆነ እንመን።
    - ያለመመሪያና ያለዓላማ የሆነ ፕሮግራም አናውጣ። ከፕሮግራም ይልቅ የሕይወት ዓላማችን ሕይወታችንን ይምራው።

## ከዚህ በታች የምናየው የመጀመሪያው ቤ/ክ ይዘቱ ምን እንደሚመስል ነው።

1. **አንዱም የእርሱ ደቀመዝሙር የተቋሙ አባል አልነበረም**
2. **አንድም የእርሱ ሐዋርያ ካሕናትና የቤተመቅደስ መሪ አልነበረም**
3. **ቤ/ክ የተፀነሰችው በቤተመቅደስና በሙክራብ ሳይሆን በአንድ የግለሰብ ቤት ውስጥ ነው**
4. **ዓለምዐቀፍ ዋና ቢሮው ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ ነበር (ሐዋ/ሥራ 11)**
5. **ቤ/ክ የአንድ ባሕል ንዑስ ክፍልን ያቀፈች ሳይሆን ባህል ዘለል አመለካከት ያላት ናት።**

6. አንድን ከተማ ወይም ሕዝብ ላይ ብናተኩር መንፈሳዊ ብልጥግናው የሚገኘው ሕዝቡ ባለበት ይሆናል።
7. የቀድሞ ቤ/ክ መሪዎችም በሥራ ላይ የተሰማሩ (*Business People*) ነበሩ።

   ሉቃስ (ሐኪም)

   ማቴዎስ (ቀረጥ ሰብሳቢ)

   ዮሐንስ፣ጴጥሮስ፣ያዕቆብ (ዓሣ አጥማጅ)

   ፊሊሞና (የመንግስት ሠራተኛ)

   ጵርስቅላና አቂላ (ድንኳን ሰፊች)

   ዶርቃ (ልብስ ሰፊት)

   ሊድያ (ነጋዴ)

   ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ (የገንዘብ ሚኒስቴር)

   ቆርኖሊስ (ወታደር)

ሕዝብ ባለበት ሥፍራ የዕርቅ አገልግሎት የሚሰጠው ሰው(አገልጋይ) የራሱ ምልክቶች አሉት።እነዚህም ሁለት ሲሆኑ

1. የታላቁ ተልዕኮን መሣካት በራሱ (ሷ) ከተማ የሚጀምር
2. ድንቆችና ተአምራትን ሕዝብ ባለበት ሥፍራ ለማድረግ ከጌታ ፀጋ የተቀበለ ሰው

## 1. የዕድገት መለኪያዎች ይኑረን

አንዲት ከተማ ለክርስቶስ ወንጌል መዳረስ ተግታለች የምንለው ምን ሲሆን ነው? የዕድገት መለኪያዎችን (መመዘኛችን) ቀጥለን እንመልከት

## ደረጃ 1

ከተማዋ ወንጌል ደርሷታል የምንለው እያንዳንዱ የጠፉ በጎች እረኛ ማግኘት ሲችሉ ነው።
ጭብጥ ማረጋገጫ፣- እያንዳንዱ የከተማው ሕዝብ ጎረቤት ለጎረቤት ስለጠፉት በጎች ካለማቋረጥ መፀለይ አለበት።
መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ የጠፉትን እየባረኩ መፀለይ (ሉቃ 10)

## ደረጃ 2

ከተማዋ ወንጌል ደርሷታል የምንለው እያንዳንዱ የጠፋ በግ እረኛው ማን እንደሆነ ሲያውቅ ነው።

### ጭብጥ ማረጋገጫ

ጓደኛዊ ግንኙነት ከጠፋው በግ ጋር በታማኝነት፣ችክላ ባልበዛበትና አሰልቺ በማይሆን መልኩ መሆን አለበት።

### መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ

ከጠፉት ጋር ሕብረት ማድረግ (ሉቃ 10:7)

## ደረጃ 3

ከተማዋ ወንጌል ደርሷታል የምንለው ከቀድሞ ይልቅ መንፈሳዊ ለውጥ ሲታይባት ነው።

ቅድስና ሲጨምር የጠፉት ሲለወጡ ይህም በፀሎትና መልካም ምግባርን በማሳየት መገለጥ ሲኖርበት «ጌታየስብ ሆይ ኃጢያተኞችን ለማዳን መምጣትህ በእርግጥ ይታይ» የሚል ፀሎት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

## መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ

የጠፉት በጎችን ፍላጎት ማሟላት (ሉቃ 10

## ደረጃ 4

ከተማዋ ስትለወጥ የእግዚአብሔር መንግስት በሁሉም ሥፍራ ይስፋፋል።

## ጭብጥ ማስረጃ

የእግዚአብሔር መንፈስ በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ሲፈስስ ብዙዎቹ ወደ ጌታ ይመጣሉ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሁሉም ሥፍራ ለውጥን ያመጣልና።
መፅሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ከተማ ቀርባለች (ሉቃ10:9)

### 2. በአዲስ መንገድ የምንሰራው መንፈሳዊ ካርታ

- የብርሀን ፀሎት ቤቶች ስንትና የት እንደሚገኙ እወቁ ካርታው ያስፈልጋል
- መንፈሳዊ ርስታችንን (ውርሳችንን) እወቁ እግዚአብሔር የዘራው ዘር ምንድነው?ብላችሁ ጠይቁ።
- መንፈሳዊ የሰይጣን ምሽጎችን እወቁ ተቃራኒው መንፈስ ምንድነው? ብላችሁ ለመፈተሽ ሙከራ አድርጉ።

## በፀሎት የወንጌል ስርጭት ከተማን በወንጌል ለመድረስ የሚረዱ ስድስት ደረጃዎች

1. በከተማዋ የምንደርስባቸውን ስፍራች ለክቶ ማቋቋም
   የጌዲን ሠ ዊት ፣ መሳፍንት
   ራዕይ 12:..
2. በከተማዋ የምንደርስባቸውን ሥፍራች መጠበቅ
   .አገልግሎታችንን ለጌታ መስጠት
   .እርስ በርስ በማገልገል
   .ንስሐ ! ንስሐ! ንስሐ ! በመግባት
3. በከተማዋ የምንደርስባቸውን ስፍራች ማስፋት በተቋቋመው .አገልግሎት የሚሳቡትን ሰች አስገብቶ ማስፋፋት
4. በከተማዋ ሰይጣን ያያዛችውን ሥፍራች ማጥራት
   . በብዙ የብርሃን ፀሎት ቤቶች አገልግሎት መስመሩን መዝጋት
   . በየስላቹ ሥፍራች ያለውን የከተማዋን ቦታ በመያዝ የሰይጣን ኃይልን ማዳከም
5. በከተማዋ ሰይጣን የያዛቸውን ሥፍራች መውረር ወይም ማበላሸት በከተማዋ ላሉ ለእያንዳንዱ ፍጥረት የምስራቹን ወንጌል ማወጅ
6. በከተማዋ ሰይጣን አንድ ጊዜ የነበረባቸውን ሥፍራች አስለቅቆ ለእግዚአብሔር የሆነ ሥፍራ እንዲሆን ማቋቋም

መንፈሳዊው ውጊያ ውጤቱን እስካላመጣ ድረስ አስፈላጊ ለውጥ ካልታየና መከሩ ካልበዛ ከዚህ በኋላ ብዙ ነገሮች ሊመጡ ይችላሉ ብሎ መጠበቅ ያስቸግራል። ጠላት ሰይጣን መንፈሳዊውን ተፅዕኖ ከዚህ በኋላ አበርትቶ ሊያመጣ ይችላል ብዙ ነፍሳትም ይጠፋሉ።

## ከተማዋን በወንጌል ለመድረስ የተቀነባበረ የጋራ አገልግሎት

1. ለፀሎት ለሚደረግ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ራሳችንን አሳልፈን እንስጥ በግላችን ወይም ከጎረቤታችን ጋር በየዕለቱ እንፀልይ።
2. ከራሳችን ቤተሰብ ጋር በመሆን በጋራ እንፀልይ።
3. አብረናቸው የምንፀልያቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ይዘን አስልጥነን እየመራን እንፀልይላቸው።
4. አብረናቸው የምንሰራቸውን ሰዎች ቤተሰቦችን ይዘን አስልጥነን እንፀልይ።
5. አብረን የምንሰራቸውን ሰዎች ቤተሰቦችን ስም ዝርዝር ይዘን አብረን እንፀልይ።
6. በቤ/ክርስቲያናችን የብርሃን ፀሎት ቤት እናደራጅ፣ እናበረታታቸው።
7. እንቅስቃሴ፣ እንጀምር ጠንክረንም በአገልግሎቱ እንትጋ።

«ሰይጣን በማይናወጥ ዓላማ ባለውና መንፈሳዊ ውጊያ ወቅት ፀንቶ መቆም አይችልም። አሜን!»

# ምዕራፍ ሁለት

## ጸሎትና የወንጌል አገልግሎት
### ወንጌላዊ ነገም ቦስት

## መግቢያ

ጸሎትና የወንጌል አገልግሎት የማይነጣጠሉና አብረዉ የተቆራኙ ናቸዉ:: የወንጌል አገልግሎት ሲታሰብ ጸሎት እንደመክፈቻ ቁልፍ ሆኖ ይቀርብና ሥራ የሞላበትን የወንጌልን በር ይከፍታል:: ስለዚህ ጸሎት የወንጌልን በር የሚከፍት ቁልፍ ነዉ ለማለት ይቻላል:: ሐዋርያ ጳዉሎስም በኤፌሶን ታላቅ የሆነ የወንጌል ሥራ በር እንደተከፈተለት ይናገራል (1ቆሮ. 16:9):: ይህ የሆነዉ ጳዉሎስ ለወንጌል አገልግሎቱ አስቀድሞ በመጸለዩ ነበር:: ወደ ኤፌሶንና ወደ ተለያዩ ከተሞች ለወንጌል አገልግሎት ከመንቀሳቀሱ በፊት በአንጾኪያ ባለችዉ ቤተክርስቲያን ከነብያትና መምህራን ጋር በመሆን በጾም በጸሎት ይተጋ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ይቻላል (የሐዋ. 13):: ሐዋርያ ጳዉሎስ ይህን እዉነት በማስመልከት በሮሜ ምዕራፍ አንድ ላይም ወደ ሮም ሄዶ ወንጌልን እዚያ ላሉት መስበክ እንዲችል አስቀድሞ መጸለይ እንዳለበት ጽፎላቸዋል (ሮሜ. 1)::

ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ጸሎት የወንጌልን አገልግሎት በር የሚከፍት ወሳኝ ቁልፍ እንደሆነ የገባዉ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነዉ:: ስለሆነም ወደ እናንተ መጥቼ ወንጌልን ለእናንተ እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር በሩን እንዲከፍትልኝ እጸልያለሁ በማለት ለሮሜ ሰዎች የሚጽፈዉ የጸሎትን ኃይል ከመረዳት አንጻር ነዉ::

የወንጌል አገልግሎት የእግዚአብሔር አንገብጋቢ አጀንዳ ነዉ:: በመሆኑም ሰዎች ከዘላለም ሞት ተርፈዉ ወደ መንግሥቱ የሚገቡበት ስለሆነ እግዚአብሔር የአገልጋዮችን ጸሎት በመስማት የወንጌል አገልግሎት በር ይከፍትላቸዋል :: የነፍስ አድኑን ወንጌል ፕሮግራም ቀያሹም ሌላ ሳይሆን እርሱ ራሱ ነዉ:: ስለዚህ ለአንዲትም ነፍስ እንኳ የምንመሰክር ብንሆን የወንጌሉ ባለቤት ወደ ሆነዉ ጌታ ጽኑ ጸሎት ማቅረብና ምሪት ማግኘት አማራጭ የሌለዉ ጉዳይ ነዉ:: ስለሆነም የወንጌል አገልግሎት ማንም እንደፈለገ የሚያንቀሳቅሰዉ ሳይሆን በጸሎት እግዚአብሔርን በመጠየቅና በአመራሩ ሥር በመሆን ብሎም እርሱ በከፈተልን በር ገብተን የምናገለግለዉ ሰማያዊ አገልግሎት ነዉ:: ወንጌልን በማገልገል የቀደሙን አባቶቻችንም የሄዱበት አቅጣጫ ይኼዉ ነበር :: ጆሮአቸዉም ለእግዚአብሔር ድምጽ ክፍት ስለነበርና ድምጹንም ይለዩ ስለነበር እግዚአብሔር እንዲሄዱ ወደ ፈለገዉ አቅጣጫ ለመሄድ አይቸገሩም ነበር ::

ከላይ ላነሳነዉ ነጥብ የጳዉሎስንና የአገልግሎት አጋሮቹን ሕይወት እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል:: እነዚህ ወገኖች በአንድ ወቅት የእግዚአብሔርን ወንጌል በእስያ ሊሰብኩ እንደፈለጉና ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ይህን ሐሳባቸዉን ወደ ተግባር ከመለወጥ እንደከለከላቸዉ እናነባለን (የሐዋ. 16):: ከዚህ ይልቅ ወደ መቆዶንያ ገብተዉ ወንጌልን እንዲሰብኩ በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ በሐዋርያዉ ጳዉሎስ በኩል በራዕይ እንደመራቸዉ መመልከት እንችላለን (የሐዋ. 16:6-10) ዉጤቱም ስኬታማ ነበር:: የዚህ ስኬት ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት የነበራቸዉ የጸሎት ሕይወት ነዉ:: « ሳታቋርጡ ጸልዩ » የሚለዉ (1ተሰ. 5:17) ሐዋርያዉ ጳዉሎስም ሳያቋርጥ ይጸልይ ስለነበረ (ሮሜ. 1:9-10፣ ኤፌ. 1:15-16፣ ቆላ. 1:9-10፣ 1ተሰ. 3:9-10፣ 2ጢሞ. 1:3) በወንጌል አገልግሎት ጣራዉን የነካ የስኬት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል (2ጢሞ. 1:3) ለወንጌል አገልግሎት ስኬት ጸሎት በተራ ቁጥር አንድ የሚሰለፍ ትልቅ ኃይል እንደሆነ በመገንዘብ ተግተን ልንጸልይ ይገባል ::

የመጀመሪያዉ የወንጌል አገልጋይ የሆነዉና ትልቁ ምሳሌአችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን ጀምሮ እስከፈጸመበት ቀን ድረስ በአባቱ አመራር ሥራ በመሆን ያከናዉን ነበር:: የዚህ ትስስርና ኅብረት መሠረቱ ወደ አባቱ ያቀርብ የነበረዉ ጽኑ ጸሎት ነዉ:: ይህም የእግዚአብሔርን የማዳን ዓላማ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ከፍጻሜ እንዲያደርስ

አስችሎታል፡፡ ይህ ማለትም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረብና በሰዎች ላይ የነበረውን የሞትን እዳ ሙሉ ለሙሉ በመክፈል የተረጋገጠ እንዲሆን አድርጎታል ለማለት ነው፡፡

የወንጌል አደራን እንዲቀበሉ የጠራቸው ደቀመዛሙርትም ፈለጉን በመከተል ለወንጌል በር መክፈቻ ቁልፍ የሆነውን ጸሎት በሕይወታቸው መለማመድን ቀጠሉ፡፡ የወንጌሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን በመስማት የአገልግሎት በር እየከፈተላቸው ለብዙዎች መዳን ምክንያት አደረጋቸው ከጥንት ጀምሮ ለአባቶቻችን በድንቅ የመለሰ ጌታ የደቀመዛሙርቱንም ጥያቄ እጅ በእጅ እየመለሰ አምላካዊ ክብሩን ገለጠ፡፡ በወንጌል አገልግሎታቸውም ድንቅን፣ተአምራትንና ምልክትን ሁሉ እያደረገ የመንግሥቱን ወሰን አሰፋ፡፡

የዛሬው ትውልድ የሆንን እኛም የጌታንና የአባቶቻችን የጸሎት ሕይወትና የወንጌል አገልግሎት ፈለግ በመከተል እግዚአብሔር የሚጠብቅብንን ሩጫ እንድንሮጥ ይገባል፡፡ ይህ ከሆነ በዘመናችን ያለውን ትውልድ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማፍለስ ይቻለናል፡፡ ሥጋ ለባሹም የእግዚአብሔርን ማዳን ያያል የመንግሥቱም ድንበር ይሰፋል፡፡ የጨለማው ግዛት ግን ይጠባል አሜን፡፡

## 1. የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎትና የጸሎት ሕይወት

ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት እጅግ ወሳኝ መሆኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚናገሩ ወንጌላት መረዳት ይቻላል ኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮ ወደመጣበት የወንጌል አገልግሎት በቀጥታ ከመግባቱ በፊት ይጸልይ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ እርግብ በእርሱ ላይ ወረደ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ (ሉቃ3:21-22)፡፡

## ኢየሱስ ክርስቶስ በጸለየ ጊዜ ሦስት ነገሮች በአንድ ጊዜ ሆነዋል

### ሀ. ሰማይ ተከፍቷል

በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል የ400 ዓመታት የጨለማ ጊዜ እንደነበረ ይታመናል ይኸውም የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ ምድር ያልመጣበትና ሰማይ ተዘግቶ የቆየበት ዘመን መሆኑ ነው ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሳይከፈት ዘመናትን ያስቆጠረውን የሰማይን በር ለመክፈት ልዩ ቁልፍ ተጠቀመ ይህም ልዩ ቁልፍ ጸሎት ነው፡፡ በርግጥም ጸሎት የሰማይ በር መክፈቻ ቁልፍ ነው (ማቴ7:7-8፣ያዕ5:17-18) ወንጌልን ለማገልገል የሚያስችለው ጸጋ የሚመጣው ከሰማይ ነውና (የሐዋ.2)፡፡ይህም ሊሆን የሚችለው የሰማይ በር ሲከፈት ብቻ ነው ከሰው በብዙ ርቀት ርቆ የሚገኘው ይህ የሰማይ በር ሊከፈት የሚችለው ደግሞ በጸሎት ነው (የሐዋ1:14)፡፡ እንዲህ እጅግ ሩቅ የሆነውን የሰማይን በር ሰው በምድር በመሆን በጸሎት መክፈት ይችላል፡፡ ስለዚህ ጸሎት የሰማይ በር የሚከፍትበት ልዩ የሆነ ቁልፍ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የእምነት አባቶቻችንም በዘመናቸው ይህን የሰማይ በር ሲከፍቱና ሲዘጉ ነበር (ሕዝ1:1፣የሐዋ7:54-56፣1ነገ17:1-7፣ያዕ5:17-18)፡፡ ዛሬ ብዙዎቻችን ይህን ቁልፍ ጥለነዋል የሰማይ ደጅ በር ሳይከፈት የወንጌል አገልግሎት ስለሌለ የጣልነውን ይህን ቁልፍ እንደገና ማንሳትና የሰማይን በር መክፈት ይኖርብናል፡፡

### ለ. መንፈስ ቅዱስ በአካላዊ ቅርጽ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወርዷል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸለየ ጊዜ የታየው ሁለተኛው ክስተት ከሥላሴ አካላት አንዱ የሆነውና የእግዚአብሔር የመለኮት ሙላት ሙሉ ለሙሉ የተገለጠበት (ቆላ2:9) እግዚአብሔር የሆነው መንፈስ ቅዱስ በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ መውረድ ነው፡፡ ሉቃስ በዚህ መልክ በጽሑፍ የዘገበው ሲሆን ይህ ሁኔታ ግን ለዮሐንስ ኢየሱስ ከእርሱ በኋላ በመምጣት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ምልክት ነበር፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን እውነት በወንጌሉ እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡

> «ከዚያም ዮሐንስ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ መንፈስ እንደ ርግብ
> ከሰማይ ወርዶ በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝም
> ቅዱስ የሚያጠምቀው መንፈስ ሲወርድና በእርሱ ላይ ሲያርፍ
> የምታየው እርሱ ነው ብሎ እስከ ነገረኝ ድረስ እኔም አላወቅሁትም
> ነበር አይቻለሁ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ፡፡»
> የዩሐ 1:32-34

ለዮሐንስ ምልክት የነበረውና በሉቃስ (ሉቃ3:21-22) ብሎም በማርቆስ (ማር1:9-11) የተዘገበው ይህ ክስተት አስቀድሞ በነብዩ ኢሳይያስ የተተነበየ ነበር (ኢሳ 42:1) ነገር ግን ትንቢቱ ወደ ፍጻሜ የደረሰው ኢየሱስ ክርስቶስ በጸለየ ጊዜ ነበር:: እዚህ ላይ ካልተጸለየ በስተቀር እግዚአብሔር በነቢያት በኩል የተናገረውን ቃል አይፈጽምም ለማለት አይደለም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከተናገረ በኋላ ቅዱሳን ጸሎታቸውን ሲያስከትሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አለ:: ስለሆነም ዳንኤል ሰባ ዓመት ሲፈጸም ሲል ይህን እግዚአብሔር በኤርሚያስ በኩል ተናግሮ እንደ ነበር ካስተዋለ በኋላ እንደጸለየ መመልከት ይቻላል (ዳን9) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀመዛሙርቱ ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁ ከነገራቸው በኋላ የትጋትን ጸሎት እንደ ቀጠሉ እናነባለን (የሐዋ 1:14) ከዚህ የምንረዳው የጸሎትን አስፈላጊነትና እግዚአብሔር ደግሞ ጸሎትን እንደ መሣሪያ ወይም እንደ መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚችል ነው::

ዋናውና ልብ ማለት የሚገባን ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ወሳኝ መሆኑን ነው ይህም እውነት ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ከሆነው ጌታ ሕይወት መረዳት እንችላለን:: ይኸውም እርሱ ጌታና አምላክ ሆኖ ሳለ ስለ አገልግሎቱ መጸለይ ካስፈለገው እውነትም ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ወሳኝና አማራጭ የሌለው ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ልንገነዘብ እንችላለን:: ቁልፍነቱም ሰማይን መክፈቱና ለወንጌል አገልግሎት ኃይል ሰጪ ለሆነው ለመንፈስ ቅዱስ መምጫ መንገድ መሆኑ ነው ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ በአካላዊ ቅርጽ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ የወረደበት ዓላማው ወንጌልን ለመስበክ እንዲያስችለው መሆኑን ተናግሯል (ኢሳ61:1-3) ሉቃስም ነብዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ የተነበየውን ትንቢት ጊዜው ደርሶ በተፈጸመ ጊዜ በድጋሚ ጽፎታል:: «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድኆች ወንጌልን እንድሰብክ እርሱ ቀብቶኛልና ለታሰሩት መፈታትን፣ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ የተጨነቁትን ነጻ እንዳወጣ፣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል ሉቃ4:18-19::»

ጌታ በጸሎት ኃይልን ከላይ ከለበሰ በኋላ ባደረገው የወንጌል አገልግሎት አስገራሚ ውጤት ሊታይ ችሏል:: ሰዎች ከአጋንንት እስራት ነፃ ወጥቷል (ሉቃስ 4:14-44)፣ ሙታን ተነስቷል (ማር5:35-43፣ የዮሐ 11:1-44):: የዚህ አስገራሚ አገልግሎት ውጤት ምክንያቱ በጸሎት የተገኘው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ሉቃስ በማረጋገጥ ይጽፋል:: «ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ . . . በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ ዝናውም በአካባቢው ባለው አገር ሁሉ ወጣ ሉቃ4:1-14::»

ከዚህ በኃላ በተቀበለው ኃይል ያደረገውን ለማየት ሩቅ ሳንሄድ ከላይ ከተጠቀሰው ምዕራፍ መመልከቱ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል:: ሐዋርያው ጴጥሮስም የኢየሱስ ክርስቶስን መቀባትና አገልግሎትን በተመለከተ የሰጠውን ምስክርነት «ሉቃስ እንደሚከተለው ጽፎታል:: እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ቀባው፣ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያቢሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ እርሱ በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ላደረገው ሁሉ እኛ ምስክሮች ነን የሐዋ 10:38-39::»

ካልተጸለየ በስተቀር ከላይ የተገለጸው ዓይነት አገልግሎት ሊታይ አይችልም::ስለሆነም የእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ዳግሞ ሙሉ እርካታ ጎልቶ የሚንጸባርቅበትን የወንጌል አገልግሎት ለማገልገል እንደ ጌታ ኢየሱስ በጸሎት መጋደል ያስፈልጋል ከዚህም ባሻገር በማንኛውም የህይወታችን አቅጣጫ የእርሱን ምሳሌ በመከተል ልንኖር ይገባል (1ቆሮ11:1፣ 1ጴጥ 2:21)

## ሐ. የእግዚአብሔር ድምጽ መጥቷል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸለየ ጊዜ በሶስተኛ ደረጃ የታየው ክስተት የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ ምድር መምጣቱና መሰማቱ ነው:: ይህም የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ ምድር ከመምጣት ከተቋረጠ ከ400 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎት ወደ ምድር መጥቶ እንደተሰማ ይታመናል:: 400 የጨለማ ዓመታት ተብሎ የሚነገርበትም ምክንያት ከእግዚአብሔር ድምጽ መቋረጥ የተነሳ መሆኑንም ብዙዎች ያምኑበታል:: በዚህ አመኔታ መሠረት የእግዚአብሔር ድምጽ መቋረጥ የጸሎት መቋረጥን አመልካች ነው:: በመሠረቱ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ የሁለት አቅጣጫዎች የተግባቦት መስመር ነው ( Two ways communication) ስለሆነም የምድሩ መስመር ከታጠፈ ከሰማዩ መስመር የሚጠበቅ ምላሽ አይኖርም ታጥፎ የቆየውን ይህን መስመር ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመጣ በኃላ በተጠመቀበት እለት ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ዘረጋው እንግዲህ ጸሎት የእግዚአብሔርን ድምጽ የምንሰማበት፣ እግዚአብሔርም

ደግሞ የእኛን ድምጽ ሰምቶ ምላሽ የሚሰጥበትና ከምድር ወደ ላይ ከላይ ደግሞ ወደ ምድር የተዘረጋ የጋርዮሽ ድምጽ መተላለፊያ መስመር ነው።

ይህን የጸሎት መስመር ካጠፍነው የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ ሊመጣ አይችልም። የወንጌሉ ባለቤት ድምጽ ከሌለ ደግሞ የወንጌል አገልግሎት የለም። ስለሆነም ድምጹን እየሰማንና ፈቃዱን እየተረዳን ለማገልገል ከወደድን ብቸኛው መንገድ መጸለይ ነው። ድምጹን ከመስማት ጋር መታዘዝ ካልታከለበት ደግሞ መስማቱ ብቻ ወደ ታቀደው ግብ ሊያደርስ አይችልም። ስለዚህ መስማትና መታዘዝ ሁሉ ጊዜ የተቆራኙ ሊለያዩ የማይችሉ ናቸው (ያዕ1:22-25)። እግዚአብሔር አብ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ተወዳጅነት ያወጀው እኮ የእርሱን ቃል ሰምቶ ፈቃዱን ከማድረጉ የተነሳ ነው (የዮ4:34)። እኛም ከቃሉ በኋላ ለጥቆ ያለውን ተግባር ተለማማጆች እንድንሆን ጌታ ምሳሌውን ትቶልናል አምላክ የሆነውና ሁሉን ማድረግ የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ለአገልግሎቱ በጥብቅ (ሉቃ9:18) መጸለይ ከነበረበት እኛ ለወንጌል አገልግሎት እጅግ አጥብቀን የማንጸልይበት ምን ምክንያት ይኖረናል? ምክንያት የለንምና እግዚአብሔር በማዳኑ ወንጌል (ሮሜ1:16) ሕዝባችንን ያድን ዘንድ በማያቋርጥ ጸሎት ፊቱን እንፈልግ (1ተሰ5:17)። ያን ጊዜ ሕዝባችን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነትን ሥራ የራሱ አድርጎ በመቀበል የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ ይሆናል።

## 2. ኢየሱስ አገልግሎቱን ከጸሎት የሚጀምር የወንጌል አገልጋይ ነው

ወንጌል ነፍስ አድን መልዕክት ያለበት ዋንኛው የእግዚአብሔር አጀንዳ ነው። ሰዎች ይህን ወንጌል ሰምተው ይድኑ ዘንድ ደግሞ ጸሎት መሠረታዊ የሆነ ቁልፍ ጉዳይ ነው። (የሐዋ 2:46-47፣6:4፣7) የመጀመሪያው የወንጌል አገልጋይ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን «ሀ» ብሎ የጀመረው ሰማይን በሚከፍት ጸሎት እንደነበር ተመልክተናል። (ሉቃ 3:21-22)። እርሱ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ሆኖ ሳለ ለአገልግሎቱ መጸለይ ካስፈለገው እኛ ነገራችን ሁሉ ውሱን የሆነ ሰዎች እንደምን አብዝተን ልንጸልይ ይገባል?
የሚገርመው ደግሞ ጌታ በሚጸልይበት ጊዜ እንደ እኛ እንኳ ወንበር ተደግፎ ሳይሆን በግንባሩ በመደፋት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። «ጥቂት እልፍ ብሎ በግንባሩ በመደፋት አባቴ ሆይ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን ብሎ ጸለየ (ማቴ 26:39፣ማር14:35-36)።»

መለኮት የሆነው ጌታ በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአሔርን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በግንባሩ ተደፍቶ መጸለይ ግድ ከሆነበት የእኛ የጸሎት ሁኔታም በእጅጉ የላቀ መሆን እንዳለበት ለመገመት በጌታ ላሉት ሁሉ ቀላል ነው። ይህን የመሰለ የጌታችንን የጸሎት ሕይወት ሁኔታን በየግላችን ማሰላሰል ብንጀምር ደንግጠንና ተደናግጠን የተቋረጠውን ጸሎታችንን እንቀጥላለንና እስቲ ለጥቂት ጊዜ ይህን እናስብ። ለእኛም ሆነ በየትኛውም ዘመን በጌታ ለዳኑና ለሚድኑ ትውልድ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎት ሕይወት የመጨረሻው ትልቁ ምሳሌ ነውና።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መገለጡና በሰው አምሳል መገኘቱ በዋናነት እኛን ለማዳን የወሰደው የፍቅር እርምጃ ቢሆንም በቅርብ ደግሞ ተግባሩን ተመልክተን እንድንከተለውም ጭምር ነው። ጌታ ከተወልንና ልንከተላቸው ከሚገባን ከብዙ ምሳሌዎች መካከል ጸሎት አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ነው። በቅርብ ሆነው ይከተሉት የነበሩትም ደቀመዛሙርት የጸሎት ሕይወታቸውን የቀዱት ከፊታቸው ሆኖ ሲጸልይ ከነበረው ከዚህ ጌታ ነው። ሉቃስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል። «አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር ጸሎቱንም እንደ ጨረሰ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ጌታ ሆይ ዮሐንስ ደቀመዛሙርቱን ጸሎት እንዳስተማራቸው አንተም መጸለይን አስተምረን አለው ሉቃስ11:1።» ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀመዛሙርት ለቀረበለት ጸሎትን አስተምረን ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እቅድ ለማውጣት እስክሪብቶና ወረቀት አልመዘዘም ነገር ግን ወዲያው ማስተማሩን በመቀጠል ተግባራዊ እንዳደረገ ሉቃስ በወንጌሉ ዘግቦታል (ሉቃ11:2-4)። በመሠረቱ ጸሎት የጸሎት ጊዜ እንጂ የእቅድ ጊዜ የለውም ሳታቋርጡ ጸልዩ ተብሎ ተጽፏልና (1ተሰ5:17)። ስለሆነም ደቀመዛሙርቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጸሎት ከተማሩ በኋላ ተግባራዊ ለማድረግ ምሳሌውን እንደተከተሉ ሁሉ እኛም በክርስትና ሕይወታችንና በወንጌል አገልግሎታችን የእርሱን ፋና ልንከተል የግድ ይላል። በተለይም ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን የምንረዳው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጥብቅ የጸሎት ሕይወትና ከወንጌል አገልግሎቱ ነው። የተረዳነውን ደግሞ በተግባር በማሳየት እርሱን ልንከተል ይገባል።

ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀረጸው የደቀመዛሙርት የጸሎት ሕይወት በአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ መመሪያቸው ሆነ በጸሎታቸውም የክፋት ሠራዊትን ምሽግ አፈረሱ (የሐ5:16፣8:7፣13:8-11፣ 16:16-18)። ትውልዳቸውንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አፈለሱ (የሐዋ 2:4፣5፣6፣8) በወንጌል አገልግሎታቸውም ብዙ ድንቅ ተአምራትና ምልክቶች ተደረጉ (ዮሐዋ3፣5፣8)። ለእግዚአብሔርም ከሰዎች ዘንድ ብዙ ምስጋናና ክብር ሆነለት። ለዚህ ሁሉ ምንጩ ከኢየሱስ የወረሱት የጸሎት ሕይወት ነው። ይህ ለወንጌል አገልግሎት በቁልፍነቱ የሚታወቀው ጸሎት በአገልግሎታቸው ዘመን ሁሉ ተግባራቸውና መፈክራቸው ሆነ (ዮሐዋ6:4፣ 1ተሰ5:17)።

ዛሬ ያለነው የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጌታና ደቀመዛሙርቱ የሄዱበትን የጸሎትና የወንጌል አገልግሎት አቅጣጫን በጽናት ልንከተለው ይገባል። ድንቅ አስገራሚና አስደናቂ የሆነው የአገልግሎታቸው ዝርዝር ዘገባ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ለእኛ መቆየቱ መመሪያ ይሆነን ዘንድ ነውና። ደግሞም የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን እንደሆነ ተነግሯልና (ሮሜ15:4)። ስለሆነም የተጻፈውን ማንበብ ብቻ ሳይሆን አንብበን ጌታና የቀደሙት የእምነት አባቶች ያደረጉትን የጸሎት ተጋድሎና የወንጌል አገልግሎት ሚና በድጋሚ በመተግበር ማረጋገጥ ይኖርብናል።

## 3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከዲያቢሎስ ጋር ለመፋለም የወሰደው እርምጃ

ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ሥልጣን በመጋፋቱ ምክንያት የተጣለ ባላጋራ ነው (ኢሳ14:ሕዝ28)። በኋላም እግዚአብሔር የማዳኑን ዓላማ ለመፈጸም ልጁን ወደ ምድር በላካው ጊዜ (ገላ4:4-5) በተለያየ አቅጣጫ ውጊያን በመክፈት ተቃውመው። በመጀመሪያ በልደቱ ማግስት ሄሮድስን በመጠቀም የግድያ ሙከራ አደረገ (ማቴ2)። የዲያቢሎስንባላጋራነት ገና ከጥንቱ የተመለከተው የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ዋናው የወንጌል አገልግሎት ከመግባቱ በፊት ከእርሱ ጋር መጋደልን ቀዳሚ አደረገ። እርሱ ለነፍስ አድን ወንጌልና ለወንጌሉ አገልጋዮች ሁሉ ትልቅ ባላንጣ ነውና ስለሆነም የማጥቃት እርምጃን በመውሰድ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ማስደረጉ ለጌታ ወሳኝ ፍልሚያ ነበር።

ከላይ ባልነው መሠረት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው ነገር የነበረው የወንጌል ጠላት ከሆነው ከዲያቢሎስ ጋር የመፋለም እርምጃን መውሰዱ ነበር። ይህ ባላንጣ በልደቱ ሰሞን የተጠቀመበትን የጦርነት ስልት በመቀየርና እጅግ በረቀቀ የፍልሚያ ዘዴ በመጠቀም ጌታን ፊት ለፊት እንደገጠመው ማቴዎስና (ማቴ4) ሉቃስ ያስነብቡናል (ሉቃ4)። ጌታ ኢየሱስ ከዲያቢሎስ ጋር ጦርነት የገጠመው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድረ በዳ በጸሎት በአብ ፊት ካሰለፈ በኋላ ነበር። ስለሆነም የወንጌል ጠላት በሆነው ዲያቢሎስ ላይ በቃሉ ሰይፍ ድልን የመቀዳጀት ምስጢርም አስቀድሞ በጸሎት መቆየቱ ነው። ጸሎት የዲያቢሎስን ምሽግ ለማፍረስና ወደ ኋላውም አሸቀንጥሮ ለመጣል የሚያስችል ብርቱ ኃይል ያለው መሆኑን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ማየት እንችላለን። ይህን በሚመለከት ሐዋርያ ጳውሎስ ቀጥሎ ያለውን ጽፏል። «የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል አለው 2ቆሮ 10:3-4።»

ሰይጣን በልደቱ ጊዜ በጌታ ላይ የሠነዘረው የመግደል ሙከራ የከሸፈ ቢሆንም እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። ስለሆነም መልሶ የማጥቃት እርምጃን ለመውሰድ በብዙ ሲቀይስ እንደቆየ መገመት ይቻላል ዲያቢሎስ ጌታ በተራበ ጊዜ ፈተናዎችን ይዞ ብቅ ማለቱ በዕለት ያገኘው ሀሳብ ሳይሆን ዓመታትን የፈጀ የስልት ቅንብር ውጤት ነው ለማለት ይቻላል። ጌታን የሚፋለምበትን ምቹ ጊዜን ይጠብቅ እንደነበረም በተራበ ጊዜ የትጥቅ ዝግጅት አሳምሮ ፊት ለፊት ለመግጠም መምጣቱም በቂ የሆነ ማስረጃ ነው። ማቴዎስ በአጭሩ ያስቀምጥ እንጂ ዲያቢሎስ አርባ ቀናት ሙሉ ጌታን እንደ ፈተነው ሉቃስ ገልጾታል (ሉቃ4:1-2)። ፈተናው በእግዚአብሔር የተወሰነ ቢሆንም (ዘዳ 8:1-5) ፈታኙ ግን ዲያቢሎስ ነው። ዲያቢሎስ ለጌታ ያቀረባቸው ሦስቱም ፈተናዎች በግል ጥቅምና ክብር ላይ በማተኮር የእግዚአብሔር ቃል ተቃራኒዎች ስለነበሩ በራሳቸው ኃጢአት ናቸው። የእግዚአብሔር ልጅ ግን ጸንቶ በመቆምና በቃሉ ምላሽ በመስጠት ዲያቢሎስን ድል አደረገው።

ጌታ በአባቱ ላይ በመደገፍና የእርሱንም ፈቃድ በማድረግ የዲያቢሎስን ፈተናዎች እንደ አመጣጣቸው ድል አድርጎ አባቱን አከበረ የእግዚአብሔርና የወንጌሉ ጠላት የሆነውንም ዲያቢሎስን ወደ ኃላው እንዲያፈገፍግ አደረገው እንግዲህ ለወንጌል አገልግሎት ጌታ ጠርቶናል (1ጴጥ2:9)። ስለሆነም አስቀድመን ዲያቢሎስን በመፍላም ሥፍራን ማስለቀቁ የግድ ይለናል። ይህን እርምጃ ከመውሰድ ውጭም ምርኮን መበዝበዝ አንችልም የጦር አዝማቻችን የሆነው ጌታ የሰጠው ማሳሰቢያም ይኼው ነበር «አንድ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛ

ውን ሰው ሳያስር ወደ ኃይለኛው ሰው ቤት ሊገባና ንብረቱን ሊዘርፍ አይችልም። ቤቱን መዝረፍ የሚችለው ኃይለኛውን ሰው ሲያስር ብቻ ነው (ማር3:27)። ይህ ባላንጣ የሚያቀርበውንም ፈተና እንደየሱስ በብቃት በማለፍ ለአገልግሎት የጠራንን ጌታ ማስከበር ቀዳሚ እርምጃ ነው። በጠላታችንም ላይ ጌታ ሙሉ ሥልጣን እንደሰጠን አንርሳ (ሉቃ10:18-19)። ብዙ አገልጋዮች ግን ዲያቢሎስ የሚያቀርብላቸውን እነዚህን የክብርና የጥቅም ነክ ፈተናዎችን በብቃት ማለፍ እየተሳናቸው በአሳዛኝ ሁኔታ ሲወድቁ ተስተውሎአል ያሳያቸውን ጊዜአዊና ብልጭልጭ ነገሮችን ለመቀበል ሲሉም የከበረውን የወንጌል አገልግሎትና የሚያስገኘውን ሰማያዊ ሽልማት አሽቀንጥረው ጥለዋል እንደዚህ ዓይነቶቹ አገልጋዮች መንገዳቸውን ወደ ኃላ የቀየሱ ልባቸውንም ከሰማይ ወደ ምድር የመለሱ የዋጋቸውንም ተመን ያለወቁና ተሳላ ሆነው የጽድቅ አክሊል ሽልማትንም አሽቀንጥረው የጣሉ ናቸው (2ጢሞ4:7-8)። ባለፉት ዓመታት በአገራችን ደረጃ ብዙዎች በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ በመውደቃቸው ምክንያት በአገልግሎት ጅማሬ ላይ እንዲገቡ ሆነዋል። የጌታ ምህረት ዳግም ያግኛቸው። አሜን።

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የምንረዳው ዋነኛው ነጥብ አንድ የወንጌል አገልጋይ በአገልግሎቱ ጅማሬ ወቅት መንገዱ ላይ ከቆመው ከዚህ ዓለም ገዥ ጋር በጸሎት በመጋደል ድል አድርጎ ወደ ወንጌል አገልግሎት መግባት ያለበት መሆኑን ነው። ዲያቢሎስ በአገልግሎታችን ሂደት ሁሉ የሚዋጋን ባላንጣችን ቢሆንም ትልቁ ተጋድሎው ግን ከአገልግሎታችን ጅማሬና ፍጻሜ ላይ ነው። አሁንም ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን ከጌታ ጋር ያደረገው ጦርነት ነው። እርሱን በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይራሱ ተገልጦ የተዋጋው ሲሆን (ማቴ4:፣ሉቃ4) በአገልግሎቱ ፍጻሜ ላይ ደግሞ በሰዎች በመጠቀም የመጣበትን ዓላማ እንዲጥል ተዋግቶታል (ማቴ16:22-23፤ 27:45-49፣ ማር8:32-33፤15:21-32፤ ሉቃ23:32-37)።

ከጅማሬው እስከ ፍጻሜ ድረስ የወንጌል አገልግሎት ከዲያቢሎስ ጋር በጽናት መጋደልን የሚጠይቅ ነው። የማጥቂያ መሣሪያዎች ደግሞ ጸሎትና ቃሉ ናቸው። ጌታም በምድረ በዳ በቀንና በሌሊት ለአርባ ቀናት ሙሉ በጸሎት ሲጋደል መቆየቱን አብረን ተመልክተነዋል። በመጨረሽም ባላንጣው ስልቱን በመቀየር ከቃሉ እየጠቀሰ ውጊያውን ቀጠለ። የቃሉ አጠቃቀም በስህተት ላይ የተመሠረተ ስለነበር ጌታ መልሶ እውነኛውን ቃል በመጥቀስ ድል አደረገው። እኛም ዛሬ ዲያቢሎስን ለመርታትና የማረካቸውን ከእጁ ለማስለቀቅ ከፈለግን ከጸሎት ተጋድሎ ጋር የተቀዳጀ የቃሉ እውቀት ሊኖረን ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስም የኤፌሶን ሰዎች ከዲያቢሎስና ከተከታዮቹ ጋር መጋደልእንዲቻላቸው ይህን የማጥቂያ መሣሪያ እንዲይዙ በማሳሰብ ጽፎላቸዋል (ኤፌ6:17)። ሲጸልዩ ደግሞ «በመንፈስ ምሪት ዘወትር እንዲጸልዩም ነግሯቸዋል (ኤፌ6:18)።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎችም እግዚአብሔርን በምሥጋና ጸሎት ማክበር እንዳለባቸው ከነገራቸው በኋላ (ቆላ3:15) የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ ይላቸዋል (ቆላ 3:16)። ከሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ የምንረዳው ዋናው ነጥብ ጸሎትና በቃሉ እውነት መሞላት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ነው። አንድ አማኝ ደግሞ በጸሎት ከተጋና በቃሉ እውነት ከተሞላ ከዲያቢሎስና ከተከታዮቹ ጋር በሚያደርገው ውጊያ አሸናፊ ይሆናል። ዛሬም ላለነውና የክርስቶስን ወንጌል ለምናሠራጨው ወገኖች ሁሉ የቃሉ ሙላትና የጸሎት ትጋት ወሳኝ ነው። የጸሎት ጉልበትና የቃሉ እውቀት ጣምራነት በሙላት በሕይወታችን ከሌሉ የዲያቢሎስን ተግዳሮት ሰብረን ነፍሳትን ወደ ጌታ መንግሥት ማፍለስ አይቻለንም ስለሆነም እንደ ጌታ ኢየሱስና እንደ ቀደሙት የእምነት አባቶቻችን ሁሉ በጸሎትና በቃሉ ተደራጅተን የማጥቃት እርምጃን በዲያቢሎስ ላይ በመክፈት የማረካቸውን ከእጁ እንድንነጥቅ እግዚአብሔር ይጠብቅብናል (የይሁዳ መልእክት ቁጥር 23)።

## 3. የኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነትና የወንጌል አገልግሎቱ

ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያቢሎስን በቃሉ እውነት ድል ካደረገው በኋላ (ማቴ4:11) የወንጌል ስብከቱን ቀጠለ (ማቴ4:17)። በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም (ሉቃ4:14) አስገራሚ የሆነ የወንጌል አገልግሎትን ፈጸመ። በመሆኑም ከአእምሮ ግምት በላይ በሆነ ሁኔታ የእግዚአብሔር ብርሃንም ጨለማ በነበረው በሰዎች ልብ ላይ በራ ሰዎችም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ሆነላቸው (ማቴ4:!8-22)። ከወንጌል ማስተማርና መስበክ ባሻገርም በበሽታ የሚማቅቁትን ሁሉ በመፈወስ መድሐኒት ሆነ (ማቴ4:23-24)። ከዚህ የተነሣ ዝናው ጎልቶ ወጣ (ማቴ4:24፣ ሉቃ4-14)። እጅግ በተሳካ ሁኔታም የምድር አገልግሎቱን ፈጸመ (የዮሐ.17:4) አስደናቂ ከየሆነው ከጌታ አገልግሎት የምንማረው ትልቅ ነገር ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ወሳኝ የሆነ የኃይል ምንጭ መሆኑን ነው። እኛም ደግሞ ከጌታ ሕይወት በተማርነው መሠረት በጾም በታገዘ ጸሎት ከዲያቢሎስ ጋር ተጋድሎ በማድረግና ሥፍራን በማስለቀቅ በማዳኑ ወንጌል ሕዝባችንን ወደ መንግሥቱ ማፍለስ

እግዚአብሔር የሚጠብቅብን ትልቁ አጀንዳው ነው። ጸሎት ኃይል ያለው መሆኑን ከኢየሱስ ሕይወት የተገነዘቡ ሐዋርያትም ለሚመሩት ሕዝብ ቀጥሎ ያለውን ወሳኝ ነገር ተናግረዋል፡፡

> «ስለዚህ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሌሎችን ደቀመዛሙርት
> በአንድነት ሰብስበው እንዲህ አሉ እኛ የማዕድን አገልግሎት
> ለማስተናገድ ስንል የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው
> አይገባንም ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ከእናንተ መካከል በመንፈስ
> ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን
> ሰባት ሰዎች ምረጡ ይህን ኃላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለን
> እኛ ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት እንተጋለን
> ሐዋ 6:2-4፡፡»

በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት መትጋት እንዳለባቸው የተረዱት ሐዋርያት ይህን መረዳታቸውን ወደ ተግባር በመለወጥ የሚያስገርም ፍሬን ሲያፈሩ ችለዋል፡፡ በጸሎት ትጋት የተከናወነውን የወንጌል አገልግሎታቸውን ውጤት ሊለካ በሚችል አገላለጽ ሉቃስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡፡ «የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ የደቀመዛሙርቱም ቁጥር በኢየሩሳሌም እጅግ እየበዛ ሄደ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእምነት የታዘዙ ሆኑ የሐዋ 6:7፡፡»

እየተነጋገርን ያለነው ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት አስደናቂ የኃይል ምንጭ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ትልቅ ምስክር እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ሐዋርያትም የጸሎትን ወሳኝነት ለሚመሩት ሕዝብ ማረጋገጥ የቻሉት ጸሎት በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ያመጣውን አስደናቂ ውጤት በቅርብ ሆነው ከማየት የተነሣ መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ዛሬም ያለነው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት አስረጋጋጭ የሆነ የኃይል ምንጭ መሆኑን መረዳት የምንችለው ሐዋርያት ምሳሌ ካደረጉት ከዚሁ ጌታ ነው፡፡ ለዚህ ጌታም በምድር ሲያገለግል በነበረበት ጊዜ ሁሉ ጸሎት የመጀመሪያው እርምጃ ነበር፡፡ ይህም በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ ከድል ወደ ድል እንዲሸጋገር አስችሎታል፡፡ እግዚአብሔር አብም ደግሞ ከብሮበታል (ሉቃ7:11-17)

## 4. ኢየሱስ ክርስቶስ ከጸሎት ወደ አገልግሎት ከአገልግሎት ደግሞ ወደ ጸሎት በሆነ ሥርዓት አገልግሎቱን በድል የፈጸመ ጌታ ነው

ጸሎት ለኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ኃይልን የሚቀበልበት (ሉቃ3:21-22፣ 4:14)፣ የዲያቢሎስን እንቅስቃሴ የሚገታበትና (ማር3:27) የሚረታበት (ማቴ 4:፣ሉቃ4)፡፡ የአገልግሎቱ ጽኑ መሠረትና ጉልበት ነው፡፡ ስለሆነም የኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዱ አገልግሎት ጸሎትን መነሻና መንደርደሪያ ያደረገ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱ ዘመን ጸሎትን ቀዳሚ በማድረግ ይህን አስፈላጊ የሆነውን ልማድና ልምምድ የሚከተል አምሳያ የሌለው ኃያል አገልጋይ ነው (ሉቃ22:34-42)፡፡ ከአገልግሎቱም በኋላ ደግሞ ወደ ጸሎት ሥፍራ በመመለስ እጅግ የረዘመ ጊዜን በአባቱ ፊት የሚያሳልፍና በምሳሌነቱም ተወዳዳሪ የሌለው ልዩ አገልጋይ ነው (ሉቃ21:37-38)፡፡ ጊዜ ወስደን ረጋ ብለን ወንጌላትን ብንመረምር የምናገኘው የአገልግሎቱ እንቅስቃሴ ይህን የመሰለ መሆኑን እንደርስበታለን፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ የተገለጸውን የአገልግሎት ልምምድ የተከተለበት ምክንያት ጠላት የሆነው ዲያቢሎስ አስልቶና አድብቶ ይዋጋው ስለነበር ነው፡፡ ምናልባት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በወሰደው የፆም ጸሎት ወቅት ድል ነስቶት የለም ወይ የሚል ጥያቄ እንጠይቅ ይሆናል፡፡ መልሱም እውነት ነው ድል ነስቶታል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጠላት ድል ከተነሳም በኋላ በሌላ ጊዜ ደግሞ ዓይነቱ ሌላ በሆነ የውጊያ ስልት ራሱን አዘጋጅቶ ብቅ እንደሚል ለጌታ የሚታወቅ ነው፡፡ ሉቃስም ዲያቢሎስ ከጌታ ጋር የሚያደርጋቸው ሌሎች የውጊያ ስልቶች ሊኖሩት እንደሚችል በሚጠቁም አኳኋን ቀጥሎ ያለውን አገላለጽ አስፍሮት እናገኛለን፡፡ «ዲያቢሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለየ ሉቃስ4:13፡፡በማለት ጽፏል፡፡

ሉቃስ ዲያቢሎስ ገና ከጌታ ጋር የሚያደርጋቸው ሌሎች ጦርነቶች እንዳሉት በጻፈው ወንጌል አንጸባርቋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ አምላክ በሆነው ጌታ ዘንድ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎት መጋደል ከምንም ነገር በፊት ቀዳሚ ጉዳዩ ነበር፡፡ ስለሆነም ይፋ የሆነ የአደባባይ አገልግሎቱንም ከመጀመሩ በፊት ጸሎትን በቅድሚያ ሲያያዘው እንመለከታለን (ሉቃ3:21-22)፡፡ በዚሁ መርህ መሠረት ከእያንዳንዱ አገልግሎትና (ማር1:35-38)፣ሉቃ5:16፣9:18፣28-36፣11:1-4) ድርጊት በፊት ይጸልይ ነበር (ሉቃ6:12-13፣9:18፣21-22:39-46)፡፡ ጌታ አንዳንድ ተአምራትንም ከማድረጉ በፊት አስቀድሞ ይጸልይ ነበር (ማቴ14:19-21፣23-25 ማር6:34-44፣ ሉቃ9:10-17፣ ዮሐ6:1-14፣ 11:38-44)፡፡

በአጠቃላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎትን ቀዳሚ በማድረግ ከድል ወደ ድል እየተሸጋገረ የምድር አገልግሎቱን በሚገባ ከዳር በማድረስ የአባቱን ፈቃድ ፈጸመ (ዮሐ17:4-5):: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜም ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ በመስጠት የዘላለም ሕይወት ባለቤት አደረገን (ዕብ7:24-27):: እኛም የእርሱን የአገልግሎት ስልት ተከትለን ብናገለግል ተልኮአችንን በድል ማጠናቀቅ እንችላለን:: እግዚብሔርም ደግሞ ይከብርበታል ዛሬ የወንጌል አገልግሎት በሚያጠያይቅ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ የተገኘው ጌታና ሐዋርያቱ የተውልንን የአገልግሎት ምሳሌ ካለመከተላችን የተነሣ ነው::ወደዚህ እውነት የመመለሱ ውሳኔም በእጅ ብልጫ ሳይሆን በግል ምርጫ ነውና ወደንና ፈቅደን እንመለስ::

## 7. ሐዋርያት የጌታን የጸሎት ሕይወት መሠረት በማድረግ አገለገሉ

እንደ ጌታ ሁሉ ሐዋርያትም በይፋ የወንጌል አገልግሎታቸውን ከመጀመራቸው በፊት የወንጌሉ ባለቤት በሆነው (ሮሜ1:1-3) በእግዚአብሔር ፊት ይጸልዩ ነበር (የሐዋ 1:14):: ይህን አስፈላጊ የሆነ የጸሎትን ባህል የተረዱትም በቅርቡ ይከተሉት ከነበረው ጌታ መሆኑ ግልጽ ነው:: በግልጽም ደግሞ አስተምሯቸዋልና (ማቴ6:9-13፣ሉቃ11:2-4)::የወንጌሉን አገልግሎት በአደባባይ ከጀመሩም በኋላ ለጸሎት ተራ ቁጥር አንድ በመስጠት በድል ያገለግሉ ነበር:: እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን (የሐዋ6:4) ማለታቸውም ለጸሎት የሰጡትን ቀዳሚ ሥፍራን የሚያሳይ ነው:: ጸሎትን መነሻ አድርገው በማገልገላቸውም ኢየሩሳሌም የብዙ ደቀመዛሙርት ከተማ እንድትሆንም አስችሎታል (ዮሐ6:7)::

ሐዋርያት ጸሎት ወንጌልን ለማገልገል የሚያስችል ኃይል ያለው መሆኑን ከተከተሉት ጌታ አስቀድሞ የተገነዘቡ ስለሆነ ጸሎት ለወንጌል አገልግሎት ዋና መሠረትና የጀርባ አጥንት ስለመሆኑ ተጨማሪ ሥልጠናን መውሰድ አላስፈለጋቸውም ይልቁንም የጌታን ፈለግ በመከተል ጸሎትን በመክፈቻ ቁልፍነት ተጠቅመው ወንጌልን በማገልገላቸው ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ሲፈልሱ ችለዋል:: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለዚህ እውነተኛ ማስረጃ ነው::

ሐዋርያት በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድ ላይ ሲጸልዩ የሚገኙ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ላይ ደግሞ አስደናቂ የሆነ የጸሎታቸውን ውጤት ሲቀበሉ እንመለከታለን:: ከጸሎቱም በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከመንፈስ ቅዱስ ባገኘው ኃይል ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ወዲያው 3000 ነፍሳት እንደተጨመሩ ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ማየት ይቻላል::ይህም ሁኔታ ጸሎት በወንጌል አገልግሎት ያለው ድርሻ ሠፊና ግዙፍ መሆኑን ያመለክተናል:: በጸሎት ውስጥ ያለው ተአምራዊ ምስጢር እንዲህ ዓይነት አስደናቂ ውጤት ያለው መሆኑን ከተረዳን የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ነውና (ሮሜ15:4) የጌታንና የሐዋርያትን ዱካ እንከተል::

የጌታ ሐዋርያት የእርሱን የምድር አገልግሎቱን ዘይቤ በመከተል ከየአገልግሎታቸው በፊት ጽኑ ጸሎት በማድረግ የወንጌል አገልግሎታቸውን ያከናውኑ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብበናል (የሐዋ10:5-16-34-48፣13:1-3፣4:49፣ሮሜ1:10-15):: ከወንጌል አገልግሎት በፊት በግላቸው መጸለይ ብቻ ሳይሆን የቅዱሳንንም የጸሎት ድጋፍ ይጠይቁ እንደነበር ቀጥለው ያሉት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያስረዱናል::

> « ወንድሞች ሆይ ስለ እኔ ወደ እግዚብሔር በመጸለይ
> የተጋድሎዬ አጋር እንድትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ
> ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ::
> በይሁዳ ካሉት ከማያምኑት እጅ እንድድንና በኢየሩሳሌም
> ያለው አገልግሎቴም በዚያ ባሉት ቅዱሳን ዘንድ
> ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩልኝ ይኸውም በእግዚአብሔር
> ፈቃድ ወደ እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም ጋር
> እንድታደስ ነው የሰላም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን
> አሜን ሮሜ 15:30-33::»

«የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት እንድናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ በሰንሰለ የታሰረ መልዕክተኛ የሆንሁት ለዚህነውና ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ ፍርሃት እንድናገር ጸልዩልኝ ኤፌ 6:19-20::»

«እኔ እስረኛ የሆንሁለትን የክርስቶስን ምስጢር ማወጅ እንድንችል እግዚአብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ ቆላ 4:3-4::»

የወንጌል አገልጋዮች ለአገልግሎታቸው በግል ከመጸለያቸው ባሻገር የአማኒያን የጸሎት ድጋፍ በተጨማሪ እንደሚያስፈልጋቸው ከላይ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግልጽ ያደርጋሉ:: ስለሆነም የወንጌሉ ጠላት የሆነው ዲያቢሎስ በሚጋልብበት በዚህ ዓለም አገልጋዮች ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ማድረስ ይችሉ ዘንድ (ማር16:15):: በጌታ ፊት በመማለድ በጸሎት ከነርሱ ጋር መቆም ያስፈልጋል:: እነዚህ አገልጋዮች በወንጌል አገልግሎት እንቅስቃሴ ወቅት ለጥቃትም ሊጋለጡ ስለሚችሉ በምልጃ ጸሎት ጋሻ በመሆን መጋረድ ይጠበቅብናል (የሐዋ 12:1-11):: ሐዋርያ ጳውሎስም የጸሎትን ጋሻነት ስለሚያምን ከተቃዋሚዎች ይድን ዘንድ እንዲጸልዩለት ለሮሜና (ሮሜ15:32) ለተሰሎንቄ ሰዎች (2ተሰ2:2) የጠበቀ አደራውን አቅርቧል:: የ«Fuller Theolgical Seminary ሥነ መለኮት ምሁር የሆኑት ዶ/ር ፒተር ዋግነርም አገልጋዮች ለሰይጣን ጥቃት ሊጋለጡ ስለሚችሉ እንድንጸልይላቸው ይገባል በማለት በፃፉት መጸሐፋቸው ማሳሳቢያ ሰጥቷል::

ከጌታና ከሐዋርያት የወንጌል አገልግሎት የምንማረው ወንጌልን ለዓለም ለመድረስ የምንችለው በልብ አንድነትና በመንፈስ ኅብረት በመሆን በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መረዳዳት ሲኖር ብቻ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደሚጠበቀው የወንጌል አገልግሎት መደምደሚያ ላይ እየደረሰ ባለበት ጊዜ በጌቴሴማኒው ጸሎት ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ከሌሎች ደቀመዛሙርት ለይቶአቸው ከእርሱ ጋር በጸሎት ይተጉ ዘንድ እንደዳረገ ማቴዎስ በወንጌሉ አብራቶታል (ማቴ26:36-38):: ሐዋርያትም ደግሞ ቃሉን ለማገልገል መትጋት ለጸሎት እንዳለባቸውና (የሐዋ6:4) የጸሎት ድጋፍም እንዲደረግላቸው ለሚያገለግሉዋቸው ምዕመንም ጥሪ ሲያደርጉ ቀደም ሲል ተመልክተነዋል:: እንግዲህ የወንጌል አገልግሎት የጋራ የሆነ የጸሎት ተጋድሎን የሚጠይቅ መሆኑን ልብ በማለት አብረን ሆነን ሊጠፉ ያሉትን በእግዚአብሔር ወንጌል ለመታደግ እጅ ለእጅና ልብ ለልብ እንያያዝ አንዱም ሌላውን በጸሎት ይደግፍ::

ሐዋርያት በዘመናቸው ከምንም ነገር በፊት እየጸለዩና እያጸለዩም በማገልገላቸው ብዙዎችን በእውነተኛ ንስኃ እንዲንበረከኩ በማድረግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አፍልሰዋል:: ከዚህም የተነሣ የመንግሥቱንም ወንጌል በሚያውጁበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር በድንቆች፣ በተአምራትና በምልክቶች ቃሉን በማጽናት ይሠራ ነበር (ማር16:20):: ከበዓለ ኀምሳ ቀን የጀመረው አስደናቂ የወንጌል አገልግሎታቸው የብዙዎችን ቀንበር እየሰበረና እስራት እየፈታ ለእግዚአብሔር ብዙ ምስጋናና ክብር እንዲሆን እንዳደረገ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሕያው ማስረጃ ነው:: ጌታ አስቀድሞ እንደተናገራቸውም ከኢየሩሳሌም የጀመረው (የሐዋ 1-7) አገልግሎታቸው ይሁዳንና ሰማርያን በማካለል (የሐዋ.8-9)፣ ከዚያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በመሄድ ማለትም በቂሳርያ፣በአንጾኪያ፣በትንሹ ኤሲያ፣በግሪክና በሮም የጌታ ምስክር ሆነዋል:: ከጌታ እርገት በኋላ ሐዋርያ ሆኖ ከሐዋርያቱ ጋር የተቀላቀለው ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የሚደግፍ የአገልግሎት ምስክርነት በሮም ላሉት አማኞች እንዲህ በማለት ጽፎላቸዋል::

> «ስለዚህ እግዚአብሔርን በማገልገሌ በክርስቶስ ኢየሱስ
> እመካለሁ በተናገርሁትና በአደረግሁት ነገር አሕዛብ
> ክርስቶስ በእኔ ሆኖ ከፈጸመው በቀር ሌላ ነገር ለመናገር
> አልደፍርም ይህም የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል
> በምልክቶችና በታምራት ነበር በዚህም ሁኔታ ከኢየሩሳሌም
> እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ ድረስ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ
> ሰብኬአለሁ ሮሜ 15:17-19::»

ጳውሎስን ጨምሮ የጌታ ሐዋርያት በወንጌል አገልግሎታቸው ዘመን ሁሉ የእርሱን የጸሎት ሕይወት መመሪያ አደረጉ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልን እንዲያገኙ አስቻላቸው (የሐዋ1:2፣4):: ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ተቃዋሚዎች ባሉበት ሥፍራ ሁሉ (የሐዋ4:13) በድፍረት ተናገሩ (የሐዋ4:31):: የክርስትና እምነት መሠረት የሆነውንም የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በአደባባይ አወጁ (የሐዋ4:33፣1ቆሮ15 ሕሙማንን ፈወሱ ፣የታሠሩትን ፈቱ (የሐዋ3:5፣8):: ሙታንንም ቀሰቀሱ (የሐዋ9:20) የእግዚአዘብሔር መንግሥት ሠፋ (የሐዋርያት ሥራና መልእክቶች):: አገልግሎታቸውንም በድል ፈጽሙ (2ጢሞ4:6-8):: እግዚአብሔርም በአገልግሎታቸው ከበረ:: የዚህ ሁሉ ስኬት ምስጢሩ ሌላ ሳይሆን የኢየሱስ ክርስቶን የጸሎት ሕይወት ምሳሌ በማድረግ የጸለዩና ያጸለዩት ጸሎት ነው:: እኛም የጌታንና የሐዋርያትን የጸሎት ሕይወት ምሳሌ በማድረግ ወንጌልን ብናገለግል በነርሱ የታየው የአገልግሎት ስኬት በእኛም ዘመን የማይደገምበት ምንም ምክንያት የለም::

## 8. በወንጌል አገልግሎት የጸሎትን ቀዳሚነት ግድ የሚሉ ምክንያቶች

### ሀ. የወንጌል መለኮታዊነት

ወንጌል የእግዚአብሔር ስለሆነ (ሮሜ1:1-2) መለኮታዊ ነው። ሰዎች ይጻፉት እንጂ ደራሲው እግዚአብሔር ነው። ሰዎች ይጽፉት ዘንድ ትዕዛዝ የሰጣቸውም እርሱ ነው (ኢያ24:26፣ ኢሳ30:8፣ ኤር30:2 ዮሐ14:26፣ 1ቆሮ14:37፣ 2ጴጥ3:2)። መለኮት የሆነው ወንጌል እግዚአብሔር ለእኛ የሚገልጠው በጸሎት ስንጠይቀው ነው። ስለሆነም ወንጌል ሰዎች እንደፈለጋቸው የሚተረጉሙት ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ የሚበራና የሚፈለቀቅ ነው። እንዲህ ዓይነቱን የእግዚብሔርን ጣልቃ ገብነት ለማግኘት ደግሞ ራስን ዝቅ አድርጎ በትህትናና በእምነት ወደ ፀጋው ዙፋን ፊት መቅረብ ብቻ ነው (ዕብ4:16)። ወንጌልን መናገር የሚቻለው በእግዚአብሔር መገለጥ እንደሆነ የገባው ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር በመንሰፉ ብርሃን ይረዳው ዘንድ የሚያገለግላቸው ወገኖች በጸሎት እንዲደግፉት ቀጥሎ ያለውን ጽፎላቸዋል። «የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት እንድናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ። በሰንሰለት የታሰረ መልዕክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና ኤፌ6:19-20።»

መለኮት የሆነውን ወንጌል መግለጥ የሚቻለው በጸሎት እንደሆነ የገባው ጳውሎስ ተመሳሳይ የሆነ የጸሎት እርዳታን ከቆላስይስ ሰዎች ሲጠይቅ እንመለከታን። « እኔ እስረኛ የሆንሁለት የክርስቶስን ምስጢር ማወጅ እንድችል እግዚአብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ ቆላ4:3-4።» እግዚአብሔርም በምላሹ የወንጌልን ምስጢር ለባሪያዎቹ በመንፈሱ በመግለጥ (1ቆሮ2:7-10) በአገልግሎታቸው ከእነርሱ ጋር ቆሟል። ዛሬም ያለነው የወንጌል አገልጋዮች ይህን መለኮታዊ ወንጌል ጌታ በመንፈሱ እንዲገልጥልን መጸለይና ማጸለይም ይኖርብናል። እግዚአብሔር ደግሞ ሰምቶ ይመልስልናል።

### ለ. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈላጊነት

ከመንፈስ ቅዱስ ውጭ የወንጌል አገልግሎት ከቶውኑም የሚታሰብ አይደለም። የወንጌል ባለቤት የሆነው እግዚአብሔርም «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ዘካ4:6) ብሎ ተናግሮ የለም። አዳኙ ጌታም » የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድኾች የምሥራች እንድሰብክ እግዚዘአብሔር ቀብቶኛል » ኢሳ61:1) በማለት ተናግሯል። አምላክ ለሆነው ጌታ ወንጌልን ለመስበክ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካስፈለገው ውስን ሰዎች ለሆንን ለእኔና ለእናንተ አድርጎ ስለማስፈለጉ ምንም ጥያቄ የሌለው ነው። ጌታ ይህን እውነት አስመልክቶ ለተከታዮቹ ከሰጠው ማሳሰቢያ ደግሞ የበለጠ መረዳት እንችላለን። «እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሉቃ24:49) በማለት አሳስቧችኋል።

ሊያርግ በተቃረበ ጊዜ ደግሞ በሉቃ24:49 የተናገራቸውን ማሳሰቢያ ደገመላቸው (የሐዋ 1:4-5)። ከጌታ ማሳሰቢያ የምንረዳው መንፈስ ቅዱስ በሌለበት ለወንጌል አገልግሎት መንቀሳቀስ እንደማይቻልና ሰውም ይህን መለኮታዊ ወንጌል በጥፋት ውስጥ ላሉት ለማዳረስ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል በራሱ ብቃት እንደሌለው የሚያስረግጥ ነው። ጌታ ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ የሚሆነውን እንዲህ በማለት ይገልጻል። « . . . መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ የሐዋ1:8።» በማለት ሊሆን ያለውን ውጤት አመልክቷል።

መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድና ከላይ የተጠቀሰው የምስክርነት ትልም ከግብ ይደርስ ዘንድ ደግሞ ጸሎትን የግድ ይላል።ስለጌታ በኢሳይያስ ምዕራፍ 61 ቁጥር 1 ላይ የተነገረው ትንቢት የተፈጸመው ጌታ በጥምቀቱ ጊዜ በጸለየው ጸሎት አማካይነት ነው (ሉቃ3:21-22)። ሉቃስም የጌታን ጸሎት ተከትሎ መንፈስ ቅዱስ በአካላዊ ቅርጽ እንደርግብ በእርሱ ላይ ማለትም በጌታ ላይ እንደወረደ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል (ሉቃ3:22)። ከዚህ በኋላ ጌታ በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመልሶ የወንጌል አገልግሎቱን እንደቀጠለም ሉቃስ ያብራራል (ሉቃ4:14-44)። በአጠቃላይ የምድር አገልግሎቱን በታላቅ ድል እንዳጠናቀቀ ሁሉም ወንጌላት ይመስክራሉ። የድሉ ምስጢርም የሰማይ በር የተከፈተበትና የዲያቢሎስ ምሽግ የፈረሰበትን ጸሎት መጸለዩ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገው ሁሉ ደቀመዛሙርትም የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ተስፋ ከተነገራቸው በኋላ መጸለይን ቀጠሉ (የሐዋ1:14)። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተከናወነው የመንፈስ ቅዱስ መውረድም የጸሎታቸው ውጤት እንደሆነም የሚያሳይ

ነው (የሐዋ2:1-4)፡፡ ከዚህ የምንረዳው ጸሎት መንፈስ ቅዱስና ኃይሉን የምናገኝበት መንገድ መሆኑን ነው፡፡ ሉቃስ ይህን እውነት በአጽንዖት ዘግቦታል፡፡ «ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ሳለ ልጁ ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራልን? ወይስ ዕንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚያምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ! ሉቃ11:11-13፡፡»

ሉቃስም የሚነግረን መንፈስ ቅዱስን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ጸሎትን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ ኃጢአተኞችን ደግሞ በወንጌል ስብከት ለእግዚአብሔር መንግሥት ለማብቃት የመንፈስ ቅዱስ መኖር የግድ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ መንገዱ ጸሎት ብቻ ነው፡፡ የወንጌል አገልጋይ የሆነው John B.Rice የሕይወት እንጀራ የሆነውን ኢየሱስን ለኃጢአተኞች ለማስተዋወቅ አፋጣኝ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን መጠየቅ እንዳለብን በጻፈው መጻፍ ገልጦታል፡፡ እርሱ በመጣ ጊዜ ደግሞ ወንጌልን ለመስበክ የሚያስችል ኃይል ያለብሳል (ሉቃ24:49፣ የሐዋ1:8)፡፡ ደፋርም ደግሞ ያደርጋል (የሐዋ4:31)፡፡ የወንጌል አገልጋዮችም በእርሱ ኃይል ሲሰብኩ ነፍሳት በእውነተኛ ንስኃ ወደ ቤተክርስቲያን ይጨመራሉ (የሐዋ ሥራ መጽሐፍ ማስረጃ ነው)፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት እንዲከናወን ደግሞ ጸሎት የግድ የቀዳሚነትን ሥፍራ መያዝ አለበት፡፡ ስለሆነም ዛሬም ወንጌልን ለማገልገል የሚያስችለንን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማግኘት በቅድሚያ መጸለይ ወሳኝና ምትክ የሌለው ነው፡፡

## ሐ. የዲያቢሎስ ጠላትነት

የምናገለግለው የእግዚአብሔር ወንጌል (ሮሜ1:1-2) ጠላት አለው፡፡ እርሱም የዚህ ዓለም ገዢ እንደሆነ የተነገረለት ዲያቢሎስ ነው (2ቆሮ4:4)፡፡ ዲያቢሎስ የእግዚብሔር ወንጌል ጠላትነቱን የገለጸው ወንጌሉ ስለእርሱ የሚያወራውን (ሮሜ1:3-4) የመጀመሪያውን የወንጌል ሰባኪ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ይህን ወንጌል እንዳይሰብክ በተዋጋው ጊዜ ነው፡፡ ዲያቢሎስም ጌታ የወንጌል ሰባኪና አዳኝ ለመሆን በሥጋ መወለዱን በሰማ ማግስት ወዲያውኑ በንጉሥ ሄሮድስ ተጠቅሞ የግድያ ሙከራ እንዳደረገ ማቴዎስ ያስነብበናል(ማቴ2)፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ ጌታ በምድረ በዳ በፆም በጸሎት ቆይታ ባደረገበት ጊዜ በጨበጣ ጦርነት እንደገጠመው ወንጌላት ይገልጻሉ (ማቴ4 ማር1 ሉቃ4)፡፡ ጌታ አስቀድሞ በጸሎት ሲጋደለው ስለነበረ ይህን ባላንጣ ድል ለማድረግ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ እንደገናም በሌላ ጊዜ አጋጣሚዎችንና ምቹ ሁኔታን ሁሉ በመጠቀም (ሉቃ4:13) ተዋግቶታል፡፡ ጌታ ግን በጸሎት በመጋደል ይመላለስ ስለነበር ማር1:35-39)፡፡ ከዲያቢሎስ ጋር ባደረገው ውጊያ ሁሉ በላዩ ላይ ድልን በመቀዳጀት ጦርነቱን አጠናቋል፡፡

ዲያቢሎስ የወንጌሉ ሥራ እንዳይሳካ የማይሞክረው ዓይነት ጦርነት የለም፡፡ ጌታን መደበኛ በሆነ መልኩ የካህናት ሽማግሌዎችንና ፈሪሳውያንን በመጠቀም ከመዋጋቱም ባሻገር እንደ ይሁዳም የባሰ ባይሆንም በጴጥሮስም ተጠቅሞ ቁልፍ የሆነውን ተልዕኮ ለማስጣል ፍልሚያ ገጥሞታል (ማቴ16:21-23፣ ማር8:31-33)፡፡ በጸሎት ሁሌ የሚያጋደለውና (ሉቃ5:16) የዲያቢሎስን አመጣጥ በእጅጉ የሚያውቀው ጌታ ይህን ጠላት ወደ ኃላው አሸቀንጥሮ ለመጣል ሰፊ ጊዜ አላስፈለገውም፡፡ ወንጌል ባላንጣ እንዳለው ጠንቅቆ የተረዳው የእግዚአብሔር ልጅ በጸሎት አስቀድሞ በመጋደል ባላንጣውን ድል በማድረግ አገልግሎቱን በድል ፈጽሟል፡፡ እንግዲህ አምላክ የሆነው ጌታ የወንጌል ጠላት የሆነውን ዲያቢሎስን በጸሎት እየተጋደለው ማገልገል ግድ ካለው እኛ ደግሞ ምን ያህል ብርቱ ተጋድሎ ማድረግ እንዳለብን ለመገመት የሚከብድ አይሆንም፡፡

ዲያቢሎስ ጠላትነቱ ለወንጌል ብቻ ሳይሆን ለወንጌል አገልጋዩና ወንጌልን መስማት ለሚገባቸው ሁሉ ነው፡፡ ሐዋርያ ጳውሎስ ሲናገር «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊ ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» (ኤፌ6:12) በማለት ያረጋግጣል ይህ ጠላት በአንድ በኩል አገልጋይ ወንጌልን እንዳያውጅ የሚዋጋው ሲሆን (1ተሰ2:18) በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ወንጌል መስማት የሚገባቸውን ሰዎች ልቦናቸውን በማጨለም ይዋጋል (2ቆሮ4:3-4)፡፡ ስለሆነም ምርኮን ለመበዝበዝ እንዲቻለን ይህ ጠላት የሚንቀሳቀስበትን ጉልበት አስቀድመን ጽኑ በሆነ የጸሎት ኃይል ማፍረስና (2ቆሮ10:3-5) እንቅስቃሴውን ሁሉ መግታት ያስፈልጋል፡፡ ከጌታም ዘንድ የተሰጠን ምክር ማሳሰቢያም ይኼው ነው፡፡ ማርቆስ በወንጌሉ እንዲህ በማለት ጽፎታል፡- «. . . ከዚህም የተነሳ አንድ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሰው ሳያስር ወደ ኃይለኛው ሰው ቤት ሊገባና ንብረቱን ሊዘርፍ አይችልም ቤቱንም መዝረፍ የሚችለው ኃይለኛውን ሰው ሲያስር ብቻ ነው ማር3:27፡፡»

እንግዲህ ምርኮን ለመበዝበዝና ሕዝብን ወደ ጌታ መንግሥት ለማፍለስ ጌታ የሰጠውን ምክር ከመስማትና እርሱም የሄደበትን መንገድ ከመሄድ ውጭ ሌላ አማራጭና አቋራጭ መንገድ የለም። ይህን ልብ በማለት የወንጌል ጠላት የሆነውን ዲያቢሎስን አስቀድመን በጸሎት በመጋደል ስኬታማ የሆነ አገልግሎት አገልግለን ትውልዳችንን ከሞት እንድንታደገው እግዚአብሔር ይጠብቅብናል (1ጢሞ2:3-4)።

## መ. የክፉ ሰዎች ተጻራሪነት

መልካም ሰዎች የመኖራቸውን ያህል (ሉቃ7:1-10) ክፉ ሰዎችም ደግሞ እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (መዝ1)። ዳዊትም የክፉዎችን ማኅበር ጠላሁ ካለ በኋላ (መዝ26) እግዚብሔር ከክፉዎች እንዲያድነው ይማጸነዋል (መዝ59)። ሐዋርያ ጳውሎስም በወንጌል አገልግሎቱ ዘመን እግዚአብሔር ከክፉ ሰዎች እንዲያድነው ይጸልይና ያጸልይም ነበር።ሐዋርያው ጳውሎስም ከእነኚህ ክፉ ሰዎች ጌታ ይሰውረው ዘንድ በጸሎት ይረዱት ዘንድ ወገኖቹን አጥብቆ የጠየቀበትን ከታች ማንበብ እንችላለን።

> «ወንድሞች ሆይ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ
> የተጋድሎዬ አጋር እንድትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ
> ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ። በይሁዳ
> ካሉት ከማያምኑት እጅ እንድንድንና በኢየሩሳሌም
> ያለው አገልግሎቴም በዚያ ባሉት ቅዱሳን ዘንድ
> ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩልኝ ይኸውም በእግዚአብሔር
> ፈቃድ ወደ እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም
> ጋር እንድታደስ ነው (ሮሜ15:30-32)።»

«በቀረውስ ወንድሞች ሆይ በእናንተ ዘንድ እንደ ሆነው የጌታ ቃል በፍጥነት እንዲሠራጭና እንዲከበር ለእኛ ጸልዩልን፣ ደግሞም ሰው ሁሉ እምነት ያለው ስለማይሆን ከዐመፀኞችና ከክፉ ሰዎች እንድንድን ጸልዩልን (2ተሰ 3:1-2)።»

ክፉ ሰዎች እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት የጠራቸውን ባሪያዎቹን በመዓረርና ብሎም ከአገልግሎታቸው በማዘግየት (1ተሰ2:18) እንቅፋት የሚሆኑ ናቸውና አጥብቀን ስለ አገልጋዮች ልንጸልይ ይገባል። ዛሬ የእነዚህ ክፉ ሰዎች አድራሻ በዓለም ብቻ ሳይሆን በቤተክርስቲያንም ጭምር ሊኖር እንደሚችል እየተረጋገጠ የመጣበት ጊዜ ነው። እነኚህ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ቁልፍ የሆነ የአገልግሎት ቦታ ላይ ተፈናጠው ሊገኙ ይችላሉ። (የዮሐ12:1-8፣3ዮሐ9-10) ስለሆነም ከጳውሎስ ዘመን ይልቅ በእኛ ዘመን የዚህ ነገር አሳሳቢነት በእጅጉ የጨመረ መሆኑን በመገንዘብ ጽኑ ምልጃን በማድረግ አገልጋዮችን በጸሎት መታደግና መከለል ያስፈልጋል። እኛም ደግሞ የአገልግሎቱ ተካፋይ ስለሆንን ለራሳችንም ጭምር መጸለይና ማጸለይም ይኖርብናል። እንደ ጌታና እንደ ቀደሙ አባቶችም ጸሎትን ቀዳሚ በማድረግ ብናገለግል አገልግሎታችን ስኬታማ ይሆናል። ጌታም ደግሞ ይከብራል። በአጠቃላይ ለዲያቢሎስ ውድቀት ለአገልግሎት ስኬት ሦስት ቁልፍ ነገሮች ከዚህ በታች ተደጋግመው የሚገኙ ናቸው።

ሀ. ጸሎት
ለ. ጸሎት
ሐ. ጸሎት ናቸው።

የጸሎት ሰዎች በመሆን ወንጌልን ማገልገል እንድንችል ጌታ ሁላችንንም በጸጋው ይርዳን አሜን !

# ምዕራፍ ሦስት

# ወንጌል ለኢ.ኦ. ተዋሕዶ አማኞች

በአቶ ፀጋዬ ደምሴ

## አጠቃላይ መግቢያ

«እንዲህም አላቸው፣ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ:: እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፣ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፣ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር:: ማር16:15-20 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ስለማሠራጨት በሰጠው ቋሚ ትእዛዝ ውስጥ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ሦስት አረፍተ ነገሮች አሉ::
እነርሱም :-

## አንደኛ

«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣» ዓለም ደቀ መዛሙርት ወደሚገኝበት እንዲመጣ አይጠብቅም ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም መሄድ አለባቸው እንጂ::

## ሁለተኛ

«ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ» ሲል በተናገረውም ፍጥረት ሁሉ ማለት የሰው ዘር ሁሉ ወንጌልን የመስማት መብትና ግዴታ እንዳለው ተመልክቷል የራሱ የሆነ ሃይማኖት ኖረውም አልኖረውም ወንጌል ለሰው ዘር ሁሉ እንዲሰበክ ታዟል፣ ሐዋርያትም ይህንኑ ተልዕኮ በአግባቡ ተወጥተዋል፣ [7]ቆላ1:6-23

## ሦስተኛ

«እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ወንጌልን ሰበኩ:: ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር::» የሚለውም ጌታ ትእዛዙን ከሚፈጽሙ አገልጋዮች ጋር በቃሉ እንደ ተናገረው ተስፋው እስከ ዓለም ፍፃሜ አብሮ እንደሚሠራ አረጋግጧል::[1]

## የወንጌል ምንነት

በዘመናችን ወንጌል ተብሎ የሚሰበከው በአብዛኛው የአገልጋዮች ልምምድ ወይም የቤተ ክርስቲያናቸው የተለያየ አስተምህሮ እየሆነ መጥቷል ነገር ግን ወንጌል ተብሎ በእግዚአብሄር ቃል የሚጠራው የሰው ደኅንነት መገኘት በተረጋገጠበት በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ የተመሠረተው የምሥራች ቃል ብቻ ነው::[2] ሊሰብክ የሚገባው ፣በእምነት የተቀበሉትንም ማዳን የሚችለው ይኸው ወንጌል ብቻ እንደሆነ ቅዱሳን መስክረዋል::[3]
ስለሆነም ምንም ዓይነት ቋንቋና ባህል ወይም ሃይማኖት ቢኖረውም፣ ራሱንና አካባቢውን የሚገነዘብበት ጠባብ ወይም ሰፊ ርእዮት (ጽንፈ ዓለም) ቢኖረውም የሰው ሁሉ የመዳን እርግጠኝነት በተሰቀለው በወንጌል በተገለጸው የእግዚአብሄር ኃይል ሲያምን ብቻ ነው፣ ያለመዳን ዕድሉንም የሚወስነው ለመቀበል የማይፈቅድ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው::[4]

---

[1] ማቴ 28:20
[2] 1ቆሮ 15:1-4
[3] ሮሜ 1:16
[4] ዮሐ3:14-18

ታዲያ ይህ ወንጌል ግለሰብንም ሆነ ቤተሰብን ሕዝብንም ሆነ አሕዛብን፣ ከነበረበት ባህል ወደ ሌላ ባህል፣ ከአንድ ቤተ እምነት ወደ ሌላ ቤተ እምነት ወዘተርፈ የምናፈልስበት ሰብዓዊ ጥበብ ወይም ፍልስፍና አይደለም ሰዎች ሁሉ የራሳቸውን የማንነት መታወቂያ እንደ ያዙ፣ የመዳን ጥያቄያቸው በወንጌል ስብከት ሊመለስላቸው ይገባል::[5] ከጨለማው ስልጣን የባርነት አገዛዝ ነጻ ወጥተዋል በመንፈስ ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንዲፈልሱና በመንፈስና በእውነት እግዚአብሄርን ወደ ማምለክ እንዲመጡ ማድረግ የወንጌል አገልጋዮች ኃላፊነት ነው::[6]

## አገልጋይ ወደ ተሰባኪዎች ማንነት መፍለስ አለበት

ተሰባኪዎች የራሳቸውን የማንነት መታወቂያ እንዲጥሉ፣ የአገልጋዮችን ማንነት እንዲላበሱና እንዲፈልሱ ሲደረግ የቆየበት አሠራር የወንጌልን የሩጫ ፍጥነት እንዲቀንስ አድርጓል ፣አላስፈላጊ መሥዋዕትነትንም ሲያስከፍል ኖሮአል ሐዋርያ ጳውሎስ ግን ወንጌልን ለአይሁድና ከተለያየ ነገድና ቋንቋ ለሆኑት አህዛብ ያሠራጨበትን መንፈሳዊ ጥበብ ሲገልጽ፣

- ነጻ ሰው ሆኖ ሳለ ራሱን ለሁሉ እንደ ባሪያ በማስገዛት
- አይሁድን በወንጌል ለመጥቀም እንደ አይሁዳዊ በመሆን
- ሕገ ኦሪት የሌላቸውን ለመጥቀም ሕገ ኦሪት እንደሌለው በመሆን
- ደካሞችን ለመጥቀም እንደ ደካማ በመሆን ማገልገሉን ይተርክልናል ሲያጠቃልል «በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንኹ በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ ብሏል[7] እንግዲያስ የምናገለግላቸውን ሰዎች ለመላበስ ወደ እነርሱ ሁኔታ መግባት ያለብን እኛ የወንጌል አገልጋዮች ነን እንጂ እነርሱን ወደ እኛ ማንነት መሳብ እንደሌለብን ማወቅ ይገባናል::

## ወንጌል በግልጥነት መሰበክ አለበት

አንዳንድ የወንጌል ሰባክያን በዓመታት ብዛት በደረሱበት የእድገት ደረጃ መጠን ጀማሪዎችን ያገለግላሉ እንዲህ መሆን የለበትም የምናስተላልፈው የወንጌል መልዕክት በተሰባኪዎች የመረዳት ችሎታ የተመጠነና ግልጽ መሆን አለበት ይህንንም በተመለከተ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ በጸሎት መጠየቅ ቀዳሚ ዝግጅት ሊሆን ይገባል:: [8]ግልጽነት የጎደለው ቃል በመናገር ሰሚዎችን ብናሰናክል ተጠያቂዎች እንሆናለን::[9]

## አስቀድመን ስለምናገለግላቸው ሰዎች ሁኔታ ማወቅ አለብን

ልናገለግለው ስለ ተጠራንለት ስለ እያንዳንዱ ሕዝብ መንበረ ሰብእ፣ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ አስፈላጊ መረጃዎችን ማጠናቀር አለብን በዚሁ መሠረትም የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናን እንድናገለግል ተጠርተን ከሆነ በሚከተሉት ርዕሶች መረጃዎችን መሰብሰብና ከግንዘቤ ማስገባት አለብን::

*አንደኛ:- የቤተ ክርስቲያኗን የሕዝቧን ታሪክ በመጠኑ*
*ሁለተኛ:- የመሠረተ እምነት አስተምህሮአዊዋን በጥልቀት*
*ሦስተኛ:- ችግሮቿን (ክርስትናዋን የበረዙባትን ትምህርቶች)በስፋት በውቀን ልናገለግል የምንችልበትን ስልት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን ጥበብ ልንቀይስ እንችላለን::*

### ታሪኳን በሚመለከት ዐጭር ማስታወሻ

ማንኛውም ሰው ታሪኩ በሌላ ዘንድ መታወቁና መነገሩ ያስደስተዋል ለሚነገረውም ቃል ጆሮውን እንዲሰጥ ይጋብዘዋል ይኸንንም ዘዴ ብዙዎች ከጥንት ጀምሮ ሳይጠቀሙበት አልቀሩም ለማስረጃ

---

[5] ሐ.ሥራ 16:30-31
[6] ዮሐ4:23-24 ሐ.ሥራ 26:17-18 ቆላ1:13-14
[7] 1ቆሮ9:19-23
[8] ሐ.ሥራ4:29-31
[9] ማቴ18:6-14

- የአይሁድ ጠበቃ ጠርጠሉስ ፊልኪስ ከተባለው አገር ገዥ ታሪክ በመቀጠል መናገር ጀመረ [10]
- ጳውሎስም እንዲህ አደረገ [11]
- በሌላም ጊዜ ጳውሎስ በንጉስ አግሪጳ ፊት እንዲሁ አደረገ[12]

## 1. ቅድመ ክርስትና ኢትዮጵያ

በሰባው ሊቃናት ትርጉምና ከእርሱ በተቀዳው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ «ኢትዮጵያ» የሚለው ስም ከ40 ጊዜ በላይ መጠቀሱ ተገልፅዋል::[13]
ሰባው ሊቀናትም ኢትዮጵያ በማለት ወደ ግሪክ ብሉይ ኪዳን ተተርጉመው ያስተሳሰፋት በዕብራይስጥ ለተናገሩት ሁለት ቃላት ምትክ አድርገው ነበር::

1. በአንድ ቦታ ኩሽ ለሚለው የካም ልጅ ስም ምትክ አድርገው ያስገቡት ሲሆን [14]
2. የኩሽ ምድር በማለት ፈንታ የኢትዮጵያ ምድር ተብሏል [15]
3. ኩሻውያን፣ ኩሻያዊ፣ ኩሻያዊት በማለት ፈንታ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊት ተብሏል:: [16]
4. የበረሃ ትርጉም ባለው ዲይም ለተባለው የዕብራይስጥ ቃል ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ተክተውለታል[17]

## 2. ኩሀና ዲያም (በረሃ) ኢትዮጵያ የተባሉበት ምክንያት

ሰባው ሊቃናት ኩሽና በረሃ መባል የነበረባቸውን በመለወጥ ኢትዮጵያ ያሉበት ምክንያት የኩሽ ልጆች የሰፈሩበት ምድር በመሆኑ ከግብጽና ከሊቢያ በስተደቡብ የተንጠለጠለው ኩሻውያን የሰፈሩበት ምድር እልም ያለ የበረሃነት ስሜት ያላው በመሆኑ ሳይሆን እንዳልቀረ ይታመንበታል::[18]

## 3. የቀድሞይቱ ኢትዮጵያ ወሰን

ኢትዮጵያውን የግብጻውያንና የሊብያውያን ጦር አዋሕደው እስከ መካከለኛው ምስራቅ ድረስ ይዘምቱ እንደ ነበረ ተረጋግጧል ስለሆነም ይህ ሁኔታ እርስ በርስ መገዛዛትም ሳይኖር እንዳልቀረ ይጠቁማል ያም ቢቀር የተባበረ ጦር ለማዝመት የቻሉት ወሰንተኞች ቢሆኑ ነው የሚለውን ሐሳብ ያጠናክራል::[19]

## 4. የስምም መወራረስ ያለ ይመስላል

ከግብጽና ከሊቢያ አዋሳኝ የሆነው ወደ ደቡብ የተንጠለጠለው በደቡብና በምዕራብ ግን ወሰኑ ያልታወቀው የዚያን ዘመኑ በረሃማው ሰፊ ክፍል ቢያንስ የዛሬዋን ሱዳንንና ኢትዮጵያን ወሰንተኞቹንም ጨምሮ በሰባው ሊቃናት እይታ ኢትዮጵያ ሳይባል አይቀርም ስለሆነም በተጠቀሰው ክልል ዛሬ የሚገኙት ሀገሮች ባንድነትም ሆነ በተናጠል ይህን ስም ተጠርተውበታል ብለን እናምናለን::

- ግብጽ ጭምር ኢትዮጵያ ተብላለች

በ2ኛነገ 18:19-25 እና በኢሳ 36:4-10 ባለው ምንባብ ሕዝቅያስ የታመነበት የግብጽ ንጉስ ፈርኦን ተብሎ በደፈናው የተገለፀው በተከታዮቹ ምዕራፎች 2ነገ 19:5-13 እና ኢሳ 37:8-13 የኢትዮጵያ ንጉስ ቲርሐቅ ተብሏል::

---

[10] ሐ.ሥራ24:2-4
[11] ሐ.ሥራ24:10
[12] ሐ.ሥራ26:1-3
[13] የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት 1995 ገጽ
[14] ኪዳን ወልድ ክፍ የግዕዝ መዝ. ቃ 1948 ገጽ
[15] ዘፍ 2:13 ኢዮ28:19 ኢሳ11:11
[16] ዘጉ12:1 2ዜና14:13 ኤር13:23
[17] ኪ.ወ.ክ የግዕዝ መዝገበ ቃላት 248 ገጽ
[18] መዝ 72:31 74:14
[19] 2ዜና 12:2-4 14:9-12 16:8

አንዳንዴ ኢትዮጵያ ተብላ እንደነበረ በተገመተችው ግብጽ የዛሬዋ ሱዳንም ሳትጠቃለል አልቀረችም ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለግብጽ ወሰንተኛ ተደርጋ የተነገረበት ስፍራ ስላለ[20] ነው።

## 5. መቼ ተለያዩ

ከግብጽና ከሊቢያ አዋሳኝ የሆኑት ሀገሮች ተለያይተው የየራሳቸውን መንግስት ያቋቋሙበት ጊዜ በውል እንደማይታወቅ እየገለጹ ምናልባት ግን ቢያንስ ከክርስቶስ ልደት በፊት 800 ዓመት ጀምሮ የአሁኗ ሱዳን በኑብያ ስም ሀገራችንም ጥንታዊ መጠሪያዋን ኢትዮጵያ መባልን ይዛ እንደ ቀረች የጸፉ እንዳሉ ታውቋል።[21]

## 6. የሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት

አብዛኞቹ ነዋሪዎች ኩሻያውያን ቢሆኑም ከነገደ ሴም የሆኑ ሳባውያን በሰሜናዊ የኢትዮጵያ ምድር ገብተው ለኩሻያውያን እየገበሩ ከኖሩ በኋላ የኩሽን መንግስት ወግተው ራሳቸውን ነጻ አወጡና አግዚያን ባሉ ቋንቋቸውም ግዕዝ ከዚሁ ወጥቷል ይላሉ። ሳባውያንም የመሠረቷት ከተማ አክሱም ለብዙ ዓመታት የሀገራችን መዲና ሆና ኖራለች።[22]

## 7. የቤተ እስራኤል በኢትዮጵያ መገኘት

ከነገድ ሴም የሆኑት እስራኤላውያን በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች በአክሱም፣ በሽሬ፣በላስታ፣በሰሜን፣በወገራ፣በቋራ፣ ይኖሩ እንደ ነበር ታውቋል በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች ወደ ሀገራቸው በመመለስ ላይ ቢሆኑም ጥቂቶቹ አሁንም አሉ ሲያከርከር የኖረው መቼ ገቡ ? የሚለው ነው። እስራኤላውያን በዓለም ላይ ከተበተኑባቸው ሦስት ወቅቶች በአንዱ ወይም በሁሉም ወቅቶች ገብተው ይሆናል ቢባል ያስኬዳል።

1. ከክርስቶስ ልደት በፊት በ722 ዓሥሩን ነገድ ያቀፈው መናገሻ ከተማውን በሰማርያ አድርጎ የነበረው የሰሜኑ ወይም የእስራኤል መንግሥት ይባል የነበረው በአሦር ንጉስ በሳርጎን ሲፈርስ[23]
2. አሁንም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 ሁለቱን ነገድ ያቀፈው መናገሻ ከተማውን ከኢየሩሳሌም ያላነቃነቀው የደቡብ ወይም የይሁዳ መንግስት ይባል የነበረው በከለዳውያን መንግስት ሲወረር[24]
3. ከ67-70 ዓ.ም ኢየሩሰሳሌም በሮም መንግሥት ጦር ስትደመስስ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል።[25]

## 8. አምልኮት በኢትዮጵያ

ኩሻያውያን በምድር ፍጥረታት ሳባውያን በሰማይ ፍጥረታት ማምለካቸውን ይዘው የገቡ ሲሆን በጦርነት በመመስቃቀል በጉርብትና በጋብቻ ምክንያት የአምልኮ መወራረስ ተከናውኗል። ቤተ እስራኤል ግን በሕገ ኦሪት መሠረት እግዚአብሄርን ያመልካሉ ረቢዎችና ምኩራቦችም አሏቸው።

## 9. በአተ ክርስትና (የክርስትና መግባት)

ሳባ ኢትዮጵያና ኑብያ ኢትዮጵያ ቅደመ ልደት ክርስቶስ ተለያይተው በየራሳቸው መንግስት ይተዳደሩ እንደ ነበር በ5.0 ነጥብ ላይ ተመልክቷል ከዚህ የተነሣም ክርስትና ወደ እነዚህ ሀገሮች በተለያየ ጊዜ ገብቷል።

---

[20] ኤር 46:25 ናሆም3:8-9 ሕዝ29:10
[21] የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1956 199 ገጽ

[22] ዜና ክማሁ እና ኪ.ወ.ክ መዝገበ ቃላት 15-16 ገጽ
[23] 2ኛ ነገ 17:22-24
[24] 2ኛ ነገ 25:8-12
[25] የኢት ታሪክ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ገጽ 283

## 9.1 ኑብያ(ኢትዮጵያ)

በቋንቋ፣ በባሕል፣በታሪክ፣በሥነ ጽሑፍ፣ በአምልኮ አንዳንድ ጊዜም በመንግሥት አስተዳደር ከግብጽ ጋር ቁርኝት ለነበረባት ለኑብያ ኢትዮጵያ ወንጌልን የሰበከላት ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ወንጌላዊ ፊሊጶስ ነበር::[26]

በ34 ዓ.ም የኑብያ ንግስት የነበረችውን የሕንደኬ 4ኛን ጃንደረባ ፊልጶስ በጋዛ ተገናኝቶት ከሰበከውና ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ክርስትና ውስጥ ለውስጥ እየተሰበከ ቆይቶ በ58 ዓ.ም የኑብያው ንጉስ ስልኪ ክርስቲያን ሆነ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንም ጋር ግንኙነትን አጠናከረና ክርስትናን አስፋፋ የኑብያ ቤተ ክርስቲያንም በሙስሊም ወራሪዎች እስከ ተደመሰሰችበት 1100 ዓ.ም ድረስ ፀንታ ቆማ ነበር::[27]

## 9.2 በሳባ ኢትዮጵያ

በእኛ ሀገር ክርስትና ስለ ተሰበከበት ጊዜና ከዚያ በፊት ነበር ስለሚባለው አምልኮተ እግዚአብሄር የተለያየ ትረካ አለ::

9.2.1 ንግስተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ በነበር ጊዜ ቀዳማዊ ምኒሊክን ከሰለሞን ፀንሳ ተመለሰች ምኒልክ ሲያድግ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በኢትዮጵያ አምልኮተ እግዚአብሄርን ለማቋቋም ታቦተ ፅዮንን ሰርቆ መጣ ከአባቱ የተሰጡትን ከየነገዱ አንዳንድ ሲህ ተውጣጥቶ ከተሰጠው ሰው መካከል ከነገድ ሌዊ የሆኑ ካህናትና ሌዋውያን ስለ ነበሩ በአክሱም በታቦተ ፅዮን የተማከለ አምልኮተ እግዚአብሄር አቋቋመ:: እስከ ክርስትና መግባት ድረስም በሕገ ኦሪት መሠረት አምልኮተ እግዚአብሄር በኢትዮጵያ ሲካሄድ ነበር::[28]

9.2.2 ወንጌላዊ ማቲዎስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወንጌልን ሰብኳል::[29]

9.2.3 ወንጌላዊ ፊሊጶስ ያጠመቀው ጃንደረባ የእኛ ዜጋ ነው ጥምቀት አልባ ክርስትናን ያመጣልን እርሱ ነው::[30]

9.2.4 በ330 ዓ.ም ፍሬምናጦስ የተባለው ግሪካዊ ክርስትናን ያመጣልን::[31]

# 10. የቅዱሳት መጽሐፍት መተርጎም

ለወንጌል መስበክ ለክርስትና መስፋፋትና ለቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ አስፈላጊ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በግዕዝ ተተርጉሞ ሲሠራበት ቆይቷል::

10.1 በፍሬምናጦስ መሪነትና በሀገር ሊቃውንት ተሳታፊነት ከሴፕቱዋጀንት መዝገብ መጀመሪያ ተተረጎመ::

10.2 በ6ኛው ምዕተ ዓመትም ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዘጠኝ (ተስዓቱ) ቅዱሳን ከሶርያው ምንጭ ጋር በማናበብ አሻሸሉት ያልተተረጎመ ክፍሎችንም ተረጎመ ተብሎ ይተረካል

10.3 በ14ኛው መቶኛ ዓመትም ይኸንኑ ትርጉም በካልእ ሰላማ ከዐረብኛው መዝገብ ጋር የማናበብና የማሻሸል ሥራ ተከናውኗል:: [32]

# አስተምህሮዋን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት አስተምህሮ የያዘው ምእላድ «ዐምስቱ አዕማድ ምስጢር» ይባላል:: «ምስጢር» የተባለው ራሱ የመሠረተ እምነቱ አስተምህሮ ሲሆን በስሜት ሕዋሳት አማካይነት መረዳት እንደማይቻል ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለሰው መንፈስ የሚያሰጨብጠው ምስጢር መሆኑን ለመግለጽ ነው:: [1]

---

[26] ሐ.ሥራ 6:3-6 8:26-39

[27] የኢትዮጵያ ታሪክ ተ.ዲ.መ 1956 ገጽ 181

[28] ዝኒ ከማሁ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ 1974 17-27 ገጽ

[29] ዝኒ ከማሁ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ 1974 17-27 ገጽ

[30] ዝኒ ከማሁ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ 1974 17-27 ገጽ

[31] ዝኒ ከማሁ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ 1974 17-27 ገጽ

[0] ኪ.ወ.ክ መዝገበ ቃላት 1948 16-20 ገጽ

[1] 1ቆሮ 2:11-17 ቆላ 1:25-27

«ዐምድ» ምሶሶ ማለት ሲሆን አዕማድ ምሰሶዎችን (ኮለኖችን) በሚመስሉ አምስት ታላላቅ ክፍሎች ተሰብስቦ መቅረቡን ለማመልከት ነው። ዐምስቱ አዕማደ ሚስጢርም

1. ምስጢረ ሥላሴ (የእግዚአብሄር ሦስትነትና አንድነት ምስጢር የተብራራበት)
2. ምስጢረ ሥጋዌ (ቃል ሥጋ የሆነበት ምስጢር የተብራራበት)
3. ምስጢረ ጥምቀት
4. ምስጢረ ቁርባን
5. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ይባላሉ።

## 1. ምስጢረ ሥላሴ

በሥሉስ አካላትና በተዋህዶ መለኮት ራሱን የገለጠው የልዑል እግዚአብሄር (ሥሉስነትና አሐድነቱ) ሦስትነቱና አንድነቱ እንዴት እንደሆነ በተጣሩና በተራቀቁ ጥንታውያን ቃላት በዚህ የአስተምህሮ ክፍል ውስጥ በቃለ እግዚአብሄር ላይ የተመሰረተ ሰፊና ዝርዝር ገለጻ አለበት።

የእግዚአብሄር ሦስትነቱ ፦

1. በአካላት(በህላዌያት)
2. ሦስቱ አካላት እያንዳንዳቸው ባለቤት ሆነው በሚሠሯቸው ግብራት(ሥራዎች) እና
3. በኩነታት ሲሆን የሦስት አካላት አንድነትም በመለኮታዊ ባሕርይ በፈቃዱ በሥልጣን፣በዙፋን፣በመፍጠር፣በመግዛት፣በመመለክ ወዘተርፈ እንደሆነ በትምህረቱ ተገልጿል።[2]

### 1.1 ሥላሴ ሦስትነት

ሥላሴ በግዕዝ ሦስት ሦስቱ፣ሦስትነት፣ሦስትዮሽ፣ማለት ነው አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ ተብለው በመጽሐፍ ቅዱስ ለተገለጹት ህላዌያት (አካላት) የተሰጠ የአካላትን ብዛት የሚገልጽ በቁጥር ላይ የተመሠረተ ስም ነው።[3] ሥላሴ የየራሳቸው መጠሪያ ስም አላቸው ማለት ነው ስሞቻቸውም የአካል (የህላዌ) ስም፣ የግብር ስም፣ የኩነት ስም፣ ተብለው የሚታወቁ ሲሆን እነዚህም ሦስቱም አካላት በውል ከሚጠሩባቸው እግዚአብሄር አምላክ ፈጣሪ ወዘተ ከተባሉት የአንድነት ስሞች በቀር ናቸው።

1.1.1 የአካላት ስም አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ መባል ነው

1.1.2 የግብር ስም አብን ወለዲና አሥራጺ ወልድን ተወላዲ መንፈስ ቅዱስንም ሠራጺ ማለት ነው።[4]

1.1.3 የኩነት ስም ማለት እያንዳንዱ አካል በክበበ ሥላሴ በተለየ አካሉ ምን ሆኖ እየሠራ እንዳለ የሚገልጽበት የመሆን፣የኹነት ስም ነው።

ይኸውም:-

- ቃል የሆነውን ወልድን ቃል ከልብ በሚወጣ አወጣጥ ዓይነት የሚወልደውና ሕይወት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ህይወት ከልብ በሚሰርጽ አውጣጥ ዓይነት የሚሰርጸው አብ በክበበ ሥላሴ ልብ መሆኑ ወይም ልብ በመሆኑ መጠራቱ [5]
- ቃል አስቀድሞ ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፣ቃልም እግዚአብሄር ነበረ፣ ተብሎ በተገለጸው መሠረት
- በልብ ዘንድ እየኖረ ከልብ በሚወለድ ቃል አወጣጥ ዓይነት በአብ ዘንድ እየኖረ በዘላለማዊ ልደት የሚወለደው ወልድ በክበበ ሥላሴ ቃል መሆኑ ወይም ቃል በመሆን መጠራቱ[6]

---

[2] ትምህርት ክርስትና ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
[3] ማቴ 28:19-20
[4] የግዕዝ መዝገበ ቃ.ኪ.ወ.ክ 1946 669 ገጽ ሃይማኖተ አበው ቲዋዲሎስ
[5] ምሳ4:23 ዮሐ16:27-28

በልብ ዘንድ እየኖረ ከልብ በሚሰርጸው ህይወት አወጣጥ ዓይነት በአብ ዘንድ እየኖረ በዘላለማዊ ስርዓት የሚወጣው መንፈስ ቅዱስ በከበበ ሥላሴ ሕይወት መሆኑ ወይም ሕይወት በመሆን መጠራቱ እንደ ሆነ ልብ ይሏል:: [7]

በዚህም መሠረት አብ ለራሱ፣ለወልድና፣ለመንፈስ ቅዱስ ልብ ነው ወልድም ለራሱ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃል ነው እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ለአብና ለወልድ ሕይወት ነው::

### 1.2 ህልውና

ከኩነት የተነሣ በሥላሴ ዘንድ ህልውና አለ ህልውና በምስጢረ ሥላሴ ጽንዐተ አካላት እንደ ተጠበቀ የግብራትና የኩነታት ባለቤትነት ሳይፋለስ አንዱ ሁለቱ አካላት በሚሠሩት ሥራ ህልው ነው:: ሁለቱ አካላትም አንዱ በሚሠራው ሥራ ህልዋን ናቸው::[8]

## 2. ምስጢረ ሥጋዌ

ከሥላሴ (ከሦስቱ) አካላት አንዱ ወልድ ሰውን ለማዳን ሲል በተለየ አካሉ ሰው የኾነበት ትምህርት የተቀረጸበት አንቀጽ ነው::

### 2.1 የቃል ሥጋ ኾነ ትርጉም (ዮሐ1:14)

- ስጋ ኾነ የሚለውን የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን «ሰው ኾነ » ከማለት ለይታ አትተረጉመውም::
- አንዳንዶች ሥጋ ብቻ እነደ ኾነ ቢረዱትም በሌላ ስፍራ « ሰው ኾነ » በሚል ቃል ተተክቶ ይገለጸልና 1ጢሞ.2:5:
- እራሱም በትስብእቱ «የሰው ልጅ» መኾኑን ተናግሯልና:ማቴ.15:13:28 ዮሐ8:40

### 2.2 የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን መግለጫ «ፍፁም አምላክ: ፍፁምም ሰው» የሚል ነው

### 2.3 ጥንተ አብሶ ያለበትን ባሕርይ ሳይወርስ እንዴት ተወለደ?

መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ወደ ድንገል ማርያም በመምጣቱና አብም በኃይሉ እርሷን በመጸለሉ: «ስለዚህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሄር ልጅ ይባላል» እንደ ተባለው ከአዳም የወረደውን ኃጢያተኛን ባሕርይ ሳይወርስ ተወለደ:ሉቃ.1:35::

### 2.4 የኢየሱስ ክርስቶስ ሐረገ ትውልድ ሲመዘዝ ማቴ1:1

- የሴቲቱ ዘር ነው: ዘፍ3:15 ገላ4:4
- የአብርሃም ዘር ነው: ዘፍ22:18 ገላ3:16
- ከነገደ ይሁዳ ነው: ዘፍ49:10 ዕብ7:13-14
- ከእሴይ ሥር መኾን የበቀለው የዳዊት ቅርንጫፍ ነው: ኢሳ፣11:1-2 ኤር 23:5-6 ራዕ22:16
- ዘርዐ ብእሲ ያተጨመረበት የሴቲቱ ዘር ብቻ ኾኖ ከድንግል ማርያም የተወለደ ነው: ኢሳ7:14 ሉቃ1:26- 33 2:6-7
- ከሰዎች ጋር በሥጋና በደም ጋር የተገናኘ የሰዎች ወንደም ነው:ዕብ 2:14-17
- ስለዚህም ከሰዎች መካካል ተመርጦ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነው:መዝ44:7 ዕብ1:8-9
  ሊቀ ካህናት ኾኗል፣ ዕብ 5:1-6
  ንጉስ ኾኗል ሉቃ1:32-33
  ነብይ ኾኗል ሉቃ13:33 ዕብ1:1-2

### 2.5. ሥጋን ብቻ ሳይኾን የሰው ኹለንተና ይዟል:: የሰው ኹለንተና የሚባለውን ሥጋን ደማዊት ነፍስንና ሕያውነት ነፍስን (መንፈስን) ከሰው ገንዘብ አድርጓል

---

[6] ማቴ 12:34-35 ዮሐ 1:1-3
[7] ምሳ 4:23 ዮሐ 16:26
[8] ዮሐ 10:37 14:10-11 2ቆሮ 5:18-19

## 2.6 ደማዊት ነፍስ ስላለችው ይርበው ነበር ማቴ4:1-2



- ይጠማው ነበር ዮሐ19:29
- ይደክመው ነበር ዮሐ4:6::
- ሕያዊት ነፍስን ከሰው ገንዘብ አድርጓል
- መንፈሳዊ ውርደት ይሰማው ነበር ማቴ27:46
- ሕያዊት ነፍስንም መንፈሱንም ለአባቱ ዐደራ ሰጠ ሉቃ23:46 የሐዋ ሥራ 2:29-31

እርሱ እንዳዘነ በማርቆስ ወንጌል ተጽፏል፡፡ ሐዘን ትካዜ የነፍስ ሕመም ነው፡፡ መራብ መጠማት ኀዳና በመኼድ መድከም በሐሰት ያይደለ በእውነት የተቀበላቸው የቀሩት ሕመማት የስጋ እንደሆኑ እንደሚታወቅ ውርደት፣ባዶነት፣ሐዘን፣ትካዜ፣ወዘተ የሕያዊት ነፍስ ሕማም እንደሆነ የቀሩት ሕማማት የሥጋ እንደ ኾኑ እናምናለን፡፡[9]

## 2.7 የመለኮት የትስብእት ግንኙነት «ተዋሕዶ» ወይም «ተዋሕዶ በተዓቅቦ» እንደ ኾነ የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ታምናለች

- የራሱ ህላዌ (ማንነት) ያለው ቃል (ወልድ) የራሱ የኾነ ማንነት ያለው ትስብእትን ተዋህዶ (ነሣ:ገንዘብ አደረገ ያዘ)፡፡
- ከተዋህዶ በኋላ በአንድ ህላዌ (ማንነት) ይታወቃል፡፡
- ተዋህዶው መለኮትና ትስብእት፡-
  - ሳይደባለቁ
  - ሳይለዋወጡ አንድ ሌላው ወደ ራሱ ሳያፈልሰው
  - ሳይከፋፈሉ የመለኮትና የትስብእት ድንበር የተለየበት ክፍል ሳይኖር
  - መዳበል ያልኾነ አንድነት ኅብረት ተዋሐደ[10]

## 2.8 በተዋህዶ ምክንያት የግል የኾነ የለም መገናዘብ ተተክሏል

- የቃል የኾነ ክብር ብልጥግና ኃይል ጥበብ ከቃል ጋር ለተዋሐደው ትስብእት ገንዘብ ኾኗል፡፡
- በዚያው ቅጽበትም የትስብእት የኾነ ውርደት ድህነት ድካም አላዋቂነት ከትስብእት ጋር ለተዋሀደው ቃል ገንዘቡ ኾኗል ፡፡

## 2.9 ተዋሕዶው ዘላዓለማዊ ነው

- እስከ መስቀል ሞት ብቻ አይደለም ከሞትም በአዲስ አካል ማለት ከእንግዲህ ሞት በማይገዛው ሰብዐዊ አካል ተነሣ ዐረገ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛ ለፍርድ ይመጣል በዘላለማዊ መንግስቱ ኹሉን ይገዛል ዕብ 2:5-9
- እኛም ከሞት ስንነሣ ወይም ሳንሞት ተለውጠን የእርሱን ክብር ሥጋ የመሰለ አካልን እናገኝና ከእርሱ ጋር ለዘላዓለም እንኖራለን [11]

# 3. ምስጢረ ጥምቀት

## 3.1 የጥምቀት መሠረት

«እንግዲህ ኺዱና አሕዛብን ኹሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» በሚለው በመድሀኒታችን ቃል መሠረት የሚፈፀም ነው፡፡[12]

## 3.2 የጥምቀት ዐላማ

1. በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ መተባበር *ወተጠምቆትከ በማይ ውእቱተሳትፎትነ በሞተ ዳግም ልደት«* በኢየሱስ ክርስቶስ ዐዲስ ልደት ተገኘ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
2. የሚያምንም ሰው ኹሉ ክርስቶስን ይመስለዋል» ብሎ ይህም የሚገኘው በክርስቶስ ሞት በመጠመቅ እንደ ኾነ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ታምናለች፡፡ ሮሜ 6:3-11 2ቆሮ5:17

---

[9] ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ 61:11

[10] ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ.ወርቅ ሃይማኖት አበው ዘጎርጎሪዮስ ወዘቄርሎስ

[11] 1ቆሮ15:20 23:42-54 ፊል3:20-21 1ተሰ4:15-17

[12] ማቴ 28:19-20

## 3.3 የጥምቀት አፈጻጸም

1. በወራጅ ውሃ ወይም ከወንዝ ለማጥመቂያ ወደ ተዘጋጀ ስፍራ በሚፈስ ውሃ ወይም ተቀድቶ ሦስት እፍኝ በተጠማቂው ዐናት ላይ በሚፈስ ውሃ ይፈጸማል።
2. ከዲያቆን በላይ በኾነ አገልጋይ እጅ ጥምቀት ይሰጣል።
3. የተጠመቀ ሰው ወዲያውኑ በሜሮን ይቀባል ይህም በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱን ወይም መታተሙን የሚያረጋግጥ ነው።
4. ለተጠመቁ በዐንገት ላይ ነጭና ቀይ ፈትል ይታሰርላቸዋል ነጩና ቀዩ ፈትል ከክርስቶስ ጎን በፈሰሰው ውሃና ደም ይመሰላሉ።
5. ሕፃናት ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን ሴቶች በተወለዱ በሰማንያ ቀን ዕድሜያቸው ይጠመቃሉ።
6. ከዚህ ዕድሜ ከመድረሳቸው በፊት በከባድ ሕመም ቢታመሙ ከተወሰነላቸው ቀን በፊት ሊጠመቁ ይችላሉ።
7. ዐዋቂዎች ካመኑና እምነታቸው ከተመረመረ በኋላ ይጠመቁ ተብሏል[14]

# 4. ምስጢረ ቁርባን

## 1.1 መሠረቱ

ጌታችን መድሐኒታችን በስቅለት ዋዜማ በምሴተ ኀሙስ ኅብስቱን አንሥቶ «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ጽዋውንም አንሥቶ እንካችሁ ጠጡ ይህ ደሜ ነው ይህንም ለመታሰቢያዬ አድርጉ » ባለው መሠረት ይፈጸማል የሚፈጸም መኾኑን መጽሐፈ ቅዳሴ በ14ቱም ቅዳሴያት ይናገራል።[15]

## 1.2 ዛሬም አማናዊ ሥጋና ደም ነው

ቄሱ ሳያከብረው ኅብስትና ወይን የነበረ ቄሱ ባከበረው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ይወርዳል ኅብስት ከመኾን የወልደ እግዚአብሔር አማናዊ ሥጋ ወደ መኾን ይለወጣል ወይኑም እንዲሁ ወይን ከመኾን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ አምላካዊ ደም መኾን ይለወጣል ተብሏል።[16]

## 1.3 ኅብስቱ እርሾ የሌለበት የስንዴ ዱቄት ልውስ ተጋግሮ ሲኾን ወይኑም ዐዲስ ከተጨመቀ ዘቢብ መኾን አለበት

## 1.4 አፈጻጸሙ

ከዲቁና ማዕረግ በላይ ያለ አገልጋይ ነው ሊያቆርብ የሚገባው።

# 2. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን

## 5.1 መሠረቱ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት በማይገዛው አካል ተነሥቷል በእርሱ ያመኑ ኹሉ በጥምቀት የተቀበሉት ዐረቦን የያዘውን የትንሣኤ ክብር ይቀዳጃ ዘንድ የተዋረደው ሥጋቸው ተለውጦ መድሐኒታችን ከሞት የተነሣበትንና ያረገበትን ዳግመኛም ተመልሶ የሚመጣበትን አካል በሚመስል አካል ይነሣሉ። **1ቆሮ 20:23-42-54 1ተሰ 4:15-17 1ዮሐ3:1-2**

---

[14] ፍትሐ ነገስት አንቀጽ3
[15] መጽሐፈ ቅዳሴ 14 ቱም
[16] ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ

## 5.2 አፈጻጸሙ



አማኞች ከተነሡ በኋላ የዘላለም ሕይወት ይወርሳሉ ያላመኑት ግን ወደ ዘላለም ሥቃይ ይኼዳሉ ዮሐ5:28:29

## 6. ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን

በዚህ ክፍል የሚገለጹት ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ምስጢራት ለማገልገል እንደ አግልግሎት መሣሪያ የምትጠቀምባቸው 7 ምስጢራት ናቸው እነዚህም፡-

1. ጥምቀት (በውሃ)
2. ሜሮን እንደ መንፈስ ቅዱስ
3. ቊርባን (በኅብስትና በወይን)
4. ክህነት (ምስጢራትን የሚያገለግልን ለመሾም)
5. ተክሊል (ምዕመናንንና ምእመናትን ለማጋባት)
6. ንስሐ (ምእመናን በኃጢያት ሲወድቁ ትንሣኤ እንዲያገኙ የሚደረግበት)
7. ቀንዲል (በዘይት ላይ ጸልዮ ሕሙማንን ለመቀባት)

## 7. ቀኖና መጻሕፍት

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የላከችልን ቀኖና መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙ ቅዱሳት መጻሕፍት 81 ናቸው ይልና ከእስክንድርያ የተላከልንና ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ አሁን ደግሞ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ፍትሐ ነገሥት አንቀፅ 2 ስማቸውን እየጠራ ሲዘረዝር ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ስማቸውን እየጠራ የቆጠራቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት | | 46 |
| ስማቸውን እየጠራ የቆጠራቸው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት | | 27 |
| | በድምሩ | 73 ናቸው |
| ከእነዚህ መካከል ውፁኣን ናቸው የተባሉ ሲቀነሱ | | - 2 |
| | የተጣራ ድምር | 71 ይኾናል |

81 ናቸው ብሎ የ71 መጻሕፍትን ዝርዝር ሲሰጥ የ10 መጻሕፍትን ዝርዝር አልጠቀሰም ለምን? በዚህ ውስጥ የተገለጸ ነገር የለም። የኛ ሊቃውንት ውፁኣን ናቸው የተባሉትን ጨምሮ የ10 መጻሕፍት ስም በመጥራት ቁጥሩን 81 ለማድረስ ቢሞክሩም ከቁጥር መግባት አላባቸው የሚሏቸው መጻሕፍት ከ10 ስለሚበልጡ ከቁጥር ይግቡ ወይም ይውጡ በሚሉአቸው መጻሕፍት ማንነት አልተስማሙም። ቀድሞውንም ድንጋጌው ብሔራዊ ስላልኾነ መስማማት አልተቻለም።

ስለዚህ የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ይህን በተመለከተ ድንጋጌ የላትም ማለቱ ይቀላል።
በአንዳንድ ሊቃውንት አመለካከት ብሉይ ኪዳን 46 አዲስ ኪዳንም 35 በማድረግ 81 ለማምጣት ሲሞክሩ በ1981 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኒቱ ባሳተመችው መጽሐፍ ቅዱስ ግን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተቀበሏቸውን 39 ብሉያትን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ያልተቀበሏቸውን 15 ብሉያትን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተቀበሏቸውን 27 ሐዲሳትን አውጥታለች። «መጽሐፉንም ሰማንያ ወአሐዱ» በማለት ትጠራዋለች። ሌሎች ግን በዝርዝር የቆጠሯቸው መጻሕፍት 71 ኾኖ ሳለ በምድር 81 ማለቱ ሲደመር ተሳስቶ ይኾናል እንጂ አሁን መግባት አለባቸው የተባሉት ሁሉ ያን ጊዜ በትርፍነት የሚታወቁ ነበሩ ይላሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተቀበሏቸውን 66ና ያልተቀበሏቸውን 15 መጻሐፍት በቀኖና የተጨመሩ ብላ እንደምትቀበል እየታወቀ መጥቷል።

## 8. መጻሕፍት ሊቃውንት

ቤተ ክርስቲያኒቱ ትክክለኛ ሊቃውንት ብላ የምትቀበላቸው እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ(451 ዓ.ም) ድረስ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲኾን በቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ከመጣ በኋላ ግን የአንጾኪያና የእስክንድርያን ሊቃውንት ብቻ ትቀበላለች። ከነዚህ ሊቃውንት ድርሰቶች በእክንድርያ አባቶች ተውጣጥቶ «ሃይማኖተ አበው» ተብሎ በአማርኛና በግዕዝ ይገኛል። ይህ መጽሐፍ ሐዋርያትና 318 ሊቃውንት በቡድን ጻፉት ከሚባለውና 55 ሊቃውንት በየግላቸው በየዘመናቸው ከጻፉት ትምህርተ ሃይማኖት በከፊል ተውጣጥቶ ወደ እኛ የተላከ

መኹኑን መጽሐፉ ራሱ ይጠቅማል። በአብዛኛው ሐሳብ በምስጢረ ሥላሴና በምስጢረ ሥጋዌ ላይ የተመሠረተ ነው ይባል እንጂ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ብዙ ምስጢራትን ይዳስሳል።

የሌሎች ሊቃውንት መጻህፍት ለምሳሌ የቄርሎስና የዮሐንስ አፈ ወርቅ መጻህፍት የሌሎችም ሊቃውንት መጻሕፍት ማር ይስሐቅ ፊልክስዩስና አረጋዊ መንፈሳዊ የተባሉ መጻሕፍተ መነኮሳትም ሲኖዶሶችና ፍትሐ ነገስት ጭምር በብዙዎች ዘንድ የሚነበቡ ናቸው። እነዚህም ኹኑ ሌሎች የሊቃውንት መጻሐፍት ጠቃሚነታቸው የጎላ መሆኑን መግለፅ ይገባል። አብዛኞዎቹ መጻህፍተ ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ ለመተርጎም ለማብራራት እርስ በርስም ያላቸውን ተዛምዶ ለመግለጽና ለመሠረተ እምነት አስተምህሮ ዝግጅት የሚጫወቱትን ሚና ከፍተኛነት ለማጉላት ተብለው የተደረሱ ናቸው። ከፊሉም ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ አምልኮ በካህናትና በምእመናን አስተዳደር ልትከተለው የሚገባውን አቅጣጫ የሚጠቁም ሲኾን የአንባብያን እዝነ ልቡና የሚስቡ ተግሣጻትና ምዕዳናት(ምክሮችም) አሉባቸው። ሊቃውንቱ በሕይወተ ሥጋ ኾነው በቤተ ክርስቲያን ያገለገሉባቸው ዘመናት የተለያዩ የኑፋቄ ትምህርተ መምህራን ውስጥ ለውስጥም ኾነ ፊት ለፊት ክርስትናን እንደ ነቀርሣ ሊበሉ የተነሡበት ጊዜ ስለ ነበር እነርሱን በቃለ እግዚአብሔር ሰይፍ በመዋጋት ያደረጉትን ተጋድሎ ቤተ ክርስቲያን በአድናቆትና በክብር መዝግባቸዋለች።በዚያ ዘመን የተነሡት የነገረ መለኮት ሊቃውንት የጻፏቸውን ሁሉ ብሉይና ሐዲስን ለመረዳት እንደ ማጣቀሻ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

## 9. አዋልድ መጻሕፍት

የቅዱሳን ተጋድሎና ተራዳኢነታቸውን ለመግለጽ የተጻፉ እንደ መኾናቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ ሊኖራቸው ስለሚገባ መስማማት ጸሐፊዎቹ የተጨነቁበት አይመስልም ስለሆነም በአብዛኛው ለመሠረተ እምነት አስተምህሮ ማጣቀሻ የማይውሉ መኾናቸው እየተረጋገጠ መጥቷል። ነገር ግን በተደረሱበት ዘመን ስለ ነበረው ሥጋዊና መንፈሳዊ አስተዳደር አልፎ አልፎ የሚዳስሱ ናቸውና በተለይ ታሪኩን በሚመለከት ማጣቀሻ የሚሆኑ መጻሕፍት አይታጣባቸውም።

## 10. ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡ ስሕተቶች

ቤተ ክርስቲያኒቱ በ1600 ዓመታት ውስጥ ንፁህ የሆነውን መሠረተ እምነቷን የሚሸፍኑ ብዙ የስሕተት ትምህርቶች ገብተውባታል። ከእነዚሁ ዋና ዋናዎቹ :-

በቅዱሳን አማላጅነት ድኅነት ነፍስ እንደሚገኝ ማመን ለሥዕልና ለምስል መስገድ *በሥርዐተ ምንኵስና ጽድቅ እንዳለ ማመን ከሞቱ በኋላ በሚደረገው ፀሎት ፍትሐትና ተዝካር መታመን የሚባሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።* እንደነዚህ ዕውቅና ባይሰጠውም ስር የሰደዱ የአስማትና የባዕድ አምልኮ ልምምድ አለ። ሆኖም በንጹህ መሠረተ እምነት ላይ እነዚህ ተደራቢ የሆነው የስሕተት አስተምህሮና ልምምድ ቢቀር ንጹህ የሆነው መሠረተ እምነታችን ወለል ብሎ ይወጣል ይታያል።

## 11. ታዲያ ኦተቤ ቤተ ክርስቲን አይደለችምን ?

ይህን ጥያቄ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መመለስ ከብዙ ስሕተት ይጠብቀናል አገልግሎታችንንም ስኬታማ ሊያደርገው ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ለመባል ያላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ:-

1. ብዙ ችግር የወረሳት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን
2. የገላትያ ቤተ ክርስቲያን (ባዕድ ወንጌል የተቀበለች)
3. ፍቅር በጎደላትና የወደቀችው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን
4. በሰይጣን ዙፋን ሥር የዋለው የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን
5. በአመንዝራዋ ኤልዛቤል ነብይነት የምትመራዋ የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን
6. ሙት የተባለቸው የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን
7. 7 ዕውር፣ ጎስቋላ፣ የተራቆተችና

ጉድለቷን ያላወቀች የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን በጌታችንና በሐዋርያው ግምገማ እነዚህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተብለዋል። ግን ሁሉም የንስሐ ዕድል ተሰጥቷቸዋል።

# 12. ባሕልና ወንጌል

## 12.1 ባሕል

ባህል የአንድ ሕዝብ እሴት ነው አንድ ሕዝብ ከቀደሙት አበው የተቀበለው በዕለታዊ ኑሮው የሚያንጸባርቀው የሚለማመደው የሚጠብቀው የሚያስተላልፈው እንደ ሁኔታው ጎጂ ጠቃሚ ተብሎ ሊፈረጅ የሚችል ሊለወጥ ሊሻሻል ሊተላለፍ የሚችል የማንነት መግለጫ ለእርሱነቱ መለያ በተለያየ መንገድ በአመጋገብ በአለባበስ በአኗኗር በአምልኮት በአነጋገር በሥነ ጽሑፍ የሚገለጽ ነው።

## 12.2 ወንጌል

ወንጌል ሰውን ሁሉ ማለትም በየትኛውም ባህል የሚኖረውን ማናኛውም ዓይነት ቋንቋ የሚናገረውንና በማንኛውም ሃይማኖትም ይሁን ርዕዮተ ዓለም የሚኖረውን የሰው ልጅ ከኃጢያት ኃይልና ከኃጢያት ውጤት የሚያድንና በክርስቶስ የተሰጠውን ዘላለማዊ ህይወት የሚያጎናጽፍ የእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ ሰውን በእኛ አስተሳሰብ ይበልጣል ይሻላል ባልነው ባህልና ሥርዓት እንዲኖር የምናፈልስበት የሰው አእምሮ ያስገኘው ጥበብ ወይም ፍልስፍና አይደለም። የወንጌል ተልዕኮ በየትኛውም ባህል ያለውን ሰው ሕይወት መለወጥ እንጂ ከወንጌል ጋር የማይጣላውን ባህሉን የማስለወጥ ተልዕኮ የለውም።

ስለሆነም:-

12.2.1 ወንጌል በማንኛውም አይነት ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ አካባቢ ለሚኖር የሰው ልጅ በሙሉ በራሱ አስተሳሰብና ባህል ቋንቋና ሥራዓት ሊሰበክ የሚገባው የእግዚአብሔር እውነት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጥልናል። ወንጌል የማንንም ባህል ከሌላው ኅብረተሰብ ባህል እንደሚያንስ ምንም ፍንጭ አይሰጥም።

12.2.2 የወንጌል እውነት የሚጋፋ ወንጌልን እንዳይቀበሉ የሚከለክል ፀረ ወንጌል የሆኑ ባህሎችን ብቻ ይቃወማል ሐዋ ሥራ 15:28-29

12.2.3 ወንጌል በባህል ውስጥ ሲሰበክ ባህል ግን በወንጌል ውስጥ አይሰበክም

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን የአይሁድ ባህል በጣም ይጫኗት እንደነበረና የአይሁድ ክርስቲያኖች የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያንን በአይሁድ ባህል እንዲኖሩ ያስገድዷቸው እንደ ነበር በሐዋርያት ሥራና በገላትያ መልዕክት የተጻፈው ይገልጽልናል። ምክንያቱም የመጀመሪያዎቹ የክርስትና እምነት ተቀባዮች አይሁዶች ስለነበሩ የወንጌልም ሰባኪያን ሆነው ስላገለገሉ በአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ላይ የራሳቸው ባህል ከወንጌል እምነት ጋር ቀላቅለው ለማስተላለፍ በመሞከራቸው ነው። ይህ ችግር በተፈጠረ ጊዜ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ሲኖዶስ ለችግሩ ትክክለኛ መፍትሔ ሰጥተው አልፈዋል። ይህም አይሁድ በባህላቸው የወንጌልን እውነት ይዘው እንዲኖሩ አሕዛብ በራሳቸው ባህል ወንጌልን እንዲቀበሉ የሚያደርግ ነው። ሐዋርያት ያስተላለፉት ውሳኔ እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን ሲሠራ ቆይቶ በኋላ ግን በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን የቤተ ክርስቲያን አባቶች አርዮስን ለማውገዝ በተሰበሰቡ ጊዜ በተጨማሪ በዚህ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሲደነግጉ የአይሁድ ክርስቲያኖችን ባህል የሚጫንና አይሁድ በአሕዛብ ባህል እንዲኖሩ የሚያደርግ ነገር ወሰኑ።

### 12.2.4 ኢትዮጵያን በሚመለከት

ወደ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ እኛ ኢትዮጵያውያን ስለሆንን የምንኖረውም በኢትዮጵያ ምድርና በኢትዮጵያውያን መካከል ስለሆነ የአገራችንን ሕዝብና ባህል የአኗኗርም እሴቶችን መረዳታችን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማገልገልና ለምድራችን መንብኘት በረከት ልንሆን እንድንችል ትልቅ አስተዋፅዎ ያደርጋል።

አገራችን የኔ የምትለው ወደ ኅብረተሰቡ ሰርጾ የገባ ከጥንት አባቶች የተሰወረ በኅብረተሰቡ አጠቃላይ ኑሮ (አመጋገብ አለባበስ አምልኮ) ውስጥ የሚገለፅ ባህል በአጠቃላይም ራስንና አካባቢን የምትረዳበትና የምትገልጽበት ሥርዓት ቋንቋ እንዳላት

ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን ብዙ ባህልና ብዙ ቋንቋዎች ቢኖሯትም በዚህ አጋጣሚ ልንገልጸው የሚገባን ከአምልኮተ እግዚአብሔር ጋር የተያያዘውን በተመለከተ ይሆናል፡፡

በተለይም በሀገሪቱ ካሉ ቤተ እምነቶችና የእምነት ተከታዮች ብዛት አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ የያዘችው ኦ.ተ.ቤ. መሆኗ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከ36-40 ሚሊዮን ምእመናን አባላት ከ32532 በላይ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከ364769 ካህናትና ከ130292 በላይ ዲያቆናት አገልጋዮች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

ቤተክርስቲያኗ በምድሪቱ ከኖረችበት የ1600 ዓመታት ርዝመት የተነሣ ለአገራችንም መንፈሳዊ ቋንቋ ባህል ቅርሳቅርስና ሥነ ጽሑፍ የመሳሰሉትን በማበርከት ባለውለታ መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ባህል በአብዛኛው የኢትዮጵያ ባህል ነው፡፡ የወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት እምነተ አስተምህሮም አንዳንዱን ብንመለከተውም ከኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ አስተምህሮ ጋራ የጎላ ልዩነት እንደሌለ መግለፅ እንችላለን፡፡

ለምሳሌ፡- በትምህርተ ሥላሴና በትምህርተ ሥጋዌ በመካከላቸው ልዩነት የለም በሌሎችም የመሠረተ እምነት አስተምህሮ ዘርፎች ከመሠረታዊ ልዩነት ይልቅ መሠራታዊ አንድነታቸው ጎልቶ ይታያል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ለኢትዮጵያውያን ወንጌል መስበክ ያለበት ባህላቸውንና ሥራዓታቸውን በመጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም 60.000.000 (ስድሳ ሚሊዮን) ከሚገመተው ሕዝባችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነት ጌትነት ሥር የተጠለለው ገና ከ10.000.000 (ከአስር ሚሊዮን) በታች እንደሆነ ሲታይ እጅግ የሚያሳዝን ነው፡፡

## 13. በአገልጋይ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

ስለዚህ ይህንን ሕዝብ በወንጌል የማገልገል ኃላፊነት ያለብን ባለዓደራ ስለሆንን እያንዳንዳችን በወንጌል ሥርጭት ጊዜ መውሰድ የሚገባንን የጥንቃቄ እርምጃ ማጠት አስፈላጊ ነው

ለምሳሌ ያህል፡-

13.1 ከሕዝቡ መካከል ስናነሣቸው ሁልጊዜ ግጭት የሚያመጡ ሃሳቦችን ማዘግየት እንዚህንም፡-

- የቅዱሳንን አማላጅነት
- ታቦት፣ተዝካር፣ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ መስቀልን መሳለም፣ሥዕል፣ ዝክር ፍታት፣ የጸሎት መጻሕፍት፣ ጾም፣ ጸበል፣ አዋልድ መጻሕፍት፣ በጸሎት ጊዜ ማማተብና ማደግደግ በአጠቃላይ ሃይማኖትን መንቀፍ
- ማርያምን አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ብሏታል ማለት
- ኢየሱስም ታላቅ ወንድሜ ነው የሚለውና የመሳሰለው በምንም መንገድ ቢሆን ደኅንነትን ከመቀበል በፊት መነሣት የለበትም፡፡

### 13.2 መነሣት የሌለባቸውን ሐሳቦች አለማንሳት ለወንጌል ምስክርነት ጠቃሚ ነው

ከእነዚህም ሁለቱ ለምሳሌ፡-

- ድንግል ማርያም የዮሴፍ ሚስት ነበረች ማለት
- ከኢየሱስ በቀር ሌሎች ልጆችን ወልዳለች ብሎ መናገር

### 13.3 በሌላ ቃል መተካት ያለባቸውን ለሕዝብ ጆሮ ጸያፍ ባልሆኑ በሚቀበሏቸው ቃላት መተካት ለምሳሌ

- ኢየሱስ አማላጅ ነው ከማለት ይልቅ /መካከለኛ አስታራቂ ሊቀ ካህናት ነው/
- ጌታን እንደግል አዳኝህ ተቀበል ከማለት ይልቅ /ሕይወትህን ለክርስቶስ ስጥ/
- ቸርች ከሚለው ቃል ይልቅ /ቤተ ክርስቲያን/
- ኦ.ተ.ቤን ምኩራብ መቅደስ ቤተ ጣዓት አለማለት
- ምዕመኑን አሕዛብ ነው ከማለት ይልቅ /ኦርቶዶክስ ነው/ ዓለማዊ ክርስቲያን ነው ማለት
- ጌታ ይባርክህ ከማለት ይልቅ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ማለት
- ኢየሱስ ከማለት አምላካችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ /መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ማለት

ይህ በእግዚአብሔር ማዳን ላይ እንደተጨመረ እንደ ሰው ብልሃት ልናስበው አይገባም ምክንያቱም ሰው ባለበት ቦታ ሁሉ ባህል እናዳለ አውቀን የወንጌል ብርሃን እንዲደርሰው የሚገባንን ሁሉ ማድረግ የወንጌል አገልግሎት ግዴታ ነው:: በተጨማሪም ለወገኖቻችን የእግዚአብሔርን እርዳታ ሳንጠይቅ ወንጌልን ባንናገር ጥሩ ነው:: የጨለማው ዓለም ገዢ ለሰዎች የወንጌል ብርሃን እንዳይበራ ስለሚቃወም በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ ከፍ ከፍ የሚል የሰውም ክፉ አሳብ ስላለ ይህን ለማፍረስ ተግተን ልንጸልይላቸው ይገባል::

## 14. የመመስከሪያ መድረኮች

ከኦርቶዶክሳውያን ወገኖች ጋር የምንገናኝባቸውን መንገዶች በተቻለን መጠን ማስፋት እንጂ ከእነርሱ ለመለየት ጥረት ባናደርግ ጥሩ ነው ለምሳሌ:-

- የመረዳጃ ዕድሮች የሴቶች የወንዶች በመስሪያ ቤት በአካባቢ በሰፈር
- የቤተ ዘመድ ስብሰባ ማኅበሮች
- ጉርብትና
- ት/ቤትና መሥሪያ ቤት የመሳሰሉት በሁሉ ነገር አብሮነትን በሚፈጥሩና በሚያዳብሩ እንደነዚህ ባሉ ዕድሎች ሁሉ በመጠቀም በዓላማ እነርሱን በመውደድ በመቀበልና ሐሳባቸውን በማስተዋል በመስማት ሳንነቅፋቸው ወንጌልን ማስተላለፍ መቻል አለብን::

## 15. ወንጌልን ከፍልሰት መለየት

ወንጌልን ስናስተላልፍ /ስንመሰክርላቸው/እኛ ወዳለንበት ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ የቦታ (የቤተ ክርስቲያን) ለውጥ እንዲያደርጉ ብቻ ባንጠይቃቸው ጥሩ ነው:: አንዳንዶም በግል እነርሱን በማገልገል ያሉ ወገኖቻቸውን ከቤተሰቦቻቸው ጀምሮ ለሌሎችንም መርዳት እንዲችሉ ብንረዳቸው ለእግዚአብሔር መንግስት ሥራ እጅግ የተሻላ መንገድ ነው::ወንጌልን የተረዱ ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያኗን ሳይለቁም ወደ ተለያየ ቦታ ሳይሄዱም ባሉበት የወንጌልን ብርሃን ለሌሎች እንዲያስተላልፉ መርዳት ይገባል::

## 16. መደምደሚያ

በመጨረሻ አሁን በእግዚአብሔር መንግስት ያለን ሁላችን ለክርስቶስ ክብር ለመኖር የጌታ ደቀ መዝሙር ለመሆን ደግሞም ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ለማብዛት ተጠርተናልና:: ክርስትናም ሕይወት እንጂ ሃይማኖት ስላልሆነ እንደሚገባ ኖረን እንድናልፍና ታሪክ በመሥራት የክርስቶስን ሕይወት በእኛ ማንነት ተገልጦ ሌሎችን መሳብ እንድንችል አብልጠን እንድንተጋ አሳስባችኋለሁ::

# ምዕራፍ አራት

# ወንጌል ለሙስሊሞች

## በአቶ አንዋር መሐመድ እና
## በአቶ ሽፈራው ሰይድ

## ሙስሊሞችን በወንጌል መድረስ

### 1. ሙስሊሞችን በወንጌል ለማድረስ በእስልምና እምነትና በክርስትና መሐከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል

**1.1 ፈጣሪን በተመለከተ**

**1.2 ሙስሊሞች ስለ ፈጣሪ (አላህ) ያላቸው እምነት**

አላህ አንድ አምላክ ነው:: ሱራ 112፣28-88፣39፣3) የአላህ አንድነት ደጋግሞ መናገር ከአምስቱ የእስልምና ተግባራት አንዱና ዋነኛው ነው:: አሽሀድ ኢላሀ ኢል አላህ ወሽሀዱ አላህ መሀመድ ረሱል አላህ ይህም ማለት አላህ አንድ ነው መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው:: ስለአላህ ማንነት ሙሉ በሙሉ ማወቅ አይቻልም፣ አላህ የቅርብም የሩቅም አምላክ ነው:(ሱራ 50:16) ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ አለ ብሎ ማመን ስርየት የሌለው ኃጢአት ነው:: አላህ ልጅም ሚስትም የለውም:: ሱራ 112 አላህ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው::ሱሩ 6:73:7:54 ሁሉም ነገር የፈጠረው «ሁን» በሚለው ቃል ነው:: አላህ ሁሉን ከፈጠረ በኋላ አላረፈም ምክንያቱም እርሱ ስለማይደክም:: አላህ 99 ስሞች አሉት:: ሱራ(7:180) እነዚህም ስሞች ደጋግሞ የጠራ ሰው መንግስተ ሰማያት ይገባል ተብሎ ይታመናል::

አላህ መሐሪ አምላክ ነው:: ምህረቱንም ለሁሉም ፍጥረት ገልጧአል ሱራ40:6፣64 ምህረቱ ከተገለጠባቸው መንገዶች ለፍጥረት በተለይም ለሰው ሰላምን፣ደስታን፣ተስፋን እና ለህይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን በመስጠት ነው:: የአላህ ፍቅር ግን ለሚወዱትና ለሚታዘዙት ብቻ ነው ሱራ3:31:: አላህ ሁሉን ቻይ ነው:: ከአላህ ፈቃድ ውጪ በሰው ላይ ምንም መልካምም ሆነ ክፉ ነገር አይመጣም:: ሱራ 3:26 አላህ ጥበበኛና ሁሉን አዋቂ ነው፣ ሱራ 67:13-14:34:1-3 አላህ ዘላለማዊ ነው ፊተኛም ኋለኛም እርሱ ነው ሱራ 55:26-27:: አላህ በምንም ነገር አይመሰልም፣ ራሱንም ቁሳዊ በሆነ መንገድ አይገልጥም:: አላህ ራሱን ሳይሆን ፈቃዱን ነው የገለጠው::

### 1.3 ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው እምነት

እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው:: ዘዳ 6:4-9 ፣ማር 12:28-30 አማኞች ይህንን አንድ አምላክ እንዲወዱና እንዲታዘዙ መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል:: እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፣ ፍጥረቱንም የሚጠብቅና የሚያኖር እርሱ ነው::ቆላ1፣15-18 እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ገልጧአል::በብሉይ ኪዳን በተለያየ መንገድ (Anthropomorphism) እና በአዲስ ኪዳን በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ተገልጧል:: ዕብ1:1-3፣ዮሐ1:18፣2ጢሞ3፣16፣2ጴጥ1፣20-21፣ ዘፍ 18፣1 እግዚአብሔር ፍቅር ነው ሰዎችን ሁሉ ይወዳል:: ፍቅሩንም በተለያዩ መንገድ ገልጦታል:: ለምሳሌ በማዳን ስራው:: (1ኛ ዮሐ 4:16) እግዚአብሔር በመለኮት አንድ ነው በአካልና በግብር ሦስት ነው፣ ይህም ማለት አንድ ፈጣሪ በሦስት አካላት ይኖራል ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሦስት ስጋዊ (ቁሳዊ) አካሎች አሉት ማለት አይደለም:: ማቴ28:18-20 2ቆሮ 13:14 1ኛዮሐ 5:7 የእግዚአብሔርን ማንነት ፍፁም እውቀት ባይኖረንም ራሱን በታሪክ ውስጥ ገልጧል:: ከቅዱሳን ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ ለምሳሌ ከኖህ ጋር (ዘፍ9) ከአብርሃም ጋር (ዘፍ12፣17፣22) እግዚአብሔር መሀሪ ነው፣ ምህረቱና ፀጋው የተገለጠው በክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞት ነው:: እግዚአብሔር መንፈስ ነው:: ዮሐ 4:23-24 እግዚአብሔር የሩቅም የቅርብም አምላክ ነው::ኢሳ 66:1-2

አላህ ከፍጥረቱ ጋር ስላለው ግንኙነት ሙስሊሞች አላህ ፈቃዱን እንጂ ራሱን አልገለጠም ይላሉ። ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር ራሱ በክርስቶስ በኩል ፈቃዱን ደግሞ በነብያት በኩል ገልፆአል ይላሉ። ስለአላህ ማንነት ልዩነት አላቸው ፤ ሙስሊሞች የአላህን ፍፁም አንድነት ሲያምኑ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አንድ ነው ነገር ግን ራሱን በሦስት አካላት ገልፆአል ይላሉ።

ሙስሊሞች አላህ የሚወደው የሚወዱትን ነው ሲሉ፣ ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሁሉ ይወዳል ይላሉ። ሙስሊሞች አላህ ልጅ የለውም ሲሉ ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር ስጋዊ ልጅ የለውም ነገር ግን በአብና በክርስቶስ መካከል ያለው ግንኙነት የአባትና የልጅ አይነት ግንኙነት ነው። ይህም ከፍጥረት ጅማሬ በፊትም ነበር ይላሉ።

## 1.5 ክርስቲያኖች አላህ የሚለው ስም ለእግዚአብሔር መጠቀም ይችላሉን ?

### አላህና እግዚአብሔርስ አንድ ናቸውን ?

በአላህና በእግዚአብሔር መካከል ብዙ መመሳሰሎች አሉ ነገር ግን በቁልፍ ጉዳዮች ላይ የጎላ ልዩነት ስላለ በሁሉ ነገር አንድ ናቸው ብሎ መናገር አይቻልም። ነገር ግን በወንጌል ምስክርነታችን ውስጥ አላህ የሚለውን ቃል ለእግዚአብሔር ተክተን መጠቀም እንችላለን። ለዚህም ሦስት ምክንያቶች አሉን።

### 1. ሰዋሰዋዊ ምክንያት:- አላህ (Allah ) የሚለው ቃል የመጣው ከሁለት የአረብኛ ቃላት ኢል(El ) እና ኢላህ (illah) ነው

ይህም «The God» ወይንም አምላክ ማለት ነው ስለዚህ የጣኦት ስም ሳይሆን አምላክ ማለት ነው። እስልምና ከመጀመሩ በፊት በአረብያ ብዙ ጣዖቶች ቢኖሩም አላህ ግን በሰማይ የሚኖርና የጣዖት አምልኮ ስፍራ የሌለውና ሁሉን ነገር የሚቆጣጠር አምላክ ተደርጎ ይታመን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አረብኛ ሲተረጎም የእግዚአብሔር ስም አላህ ተብሎ ተጽፏል። አረብ ክርስቲያኖችም እግዚአብሔርን የሚጠሩት አላህ ብለው ነው። ነገር ግን ሙስሊም አረቦችና ክርስቲያን አረቦች አላህ የሚለውን ቃል በጋራ ቢጠቀሙም ስለአላህ ማንነት፣ ባሕርይ እና ስራ ያላቸው መረዳት ይለያያል። ለምሳሌ በኦሮምኛ ክርስቲያኖችም የኦሮሞ ባሕላዊ እምነት ተከታዮችም እግዚአብሔርን «ዋቀዮ» ይሉታል። ነገር ግን የመረዳት ልዩነት አላቸው።

### 2. መጽሐፍ ቅድሳዊ ወይንም ስነ መለኮታዊ ምክንያት

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ብቸኛ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ ተገልፆአል በአዲስ ኪዳንም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተገልጧል። ነገር ግን አይሁዶች እስካሁን ድረስ ይህን እውነት አያምኑም። ክርስቲያኖችና አይሁዶች የሚያምኑት በብሉይ ኪዳን የተገለጠውን አምላክ ነው። ስለዚያ አምላክ ያላቸው መረዳት ግን ሰፊ ልዩነት አላቸው የሙስሊሞችና የአላህ መረዳት ከዚህ ብዙ የተለየ አይደለም ስለዚህ ልዩነቱን በጣም የሰፋ አድርገን መመልከት የለብንም። በእርግጥ መሠረታዊ ልዩነቶች አሉ ነገር ግን መመሳሰሎችን መዘንጋት አያስፈልግም።

### 3. ከወንጌል ተልዕኮ አንፃር

በሐዋ 17:23 ጳውሎስ የተለያዩ አማልክት የሚያመልኩትን የአቴና ሰዎች «ለማይታወቅ አምላክ » የሚል መሠዊያ ባየ ጊዜ ከዚህ በመነሳት እናንተ የማይታወቅ አምላክ ያላችሁት እግዚአብሔር ነው። ልጁን ወደዚህ ምድር ላከ በማለት አስረድቷቸዋል። ምንም እንኳን ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ አመለካከት ቢኖራቸውም ይህ አምላክ ማን እንደሆነ ከራሳቸው አውድ በመነሳት ገለጠላቸው። ስለዚህ ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔር በቂና ትክክለኛ እውቀት ስለሌላቸው አላህ የሚለውን ቃል ሳንቀይረው አላህ እንደ አምላክ ማን እነደሆነ ልንነግራቸው እንችላለን። እኛ ተቃውሟችን አላህ ከሚለው ቃል ሳይሆን ስለእርሱ ካለው መረዳት ጋር ነው። አላህ የሚለው ቃል መጠቀማችን ከሙስሊሞች ጋር ላለን ግንኙነት ሆነ ለወንጌል ስራ መልካም ስለሆነ መጠቀሙ ይበጃል። ነገር ግን ሙስሊሞች ስለ አላህ ያላቸው መረዳትና ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ያላቸው መረዳት አንድ አይደለም።

# ስለፍጥረት

## ስለፍጥረት ስለ ሰው አፈጣጠርና ኃጢዓት

## 1. የሙስሊሞች አመለካከት

አላህ ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጥሯል:: ሱራ 7:54፣ 21:30-33 አንዳንድ የቁርዓን ሊቃውንቶች የቁርዓን ትምህረት ከሳይንስ ጋር ለማጣጣም ስድስቱ ቀናች ስድስት ረጃጅም ጊዚያት (Periods)ናቸው ይላሉ:: ሁሉም ህይወት ያለው ፍጥረት ከውሃም ተፈጥሯል ይላሉ:: አላህ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ምድርን እንዲገዛ ወኪል አድርጎታል:: ሰው የተሰራው ከአፈር ወይንም ሸክላ (Clay ) ነው:: ከተፈጠረም በኋላ ሁሉም ፍጥረት ስምና አጠቃላይ ማንነታቸው አላህ አስተምሮታል፣ የተማረውንም ነገር ለመላዕክት እንዲናገር ሲጠይቅ በትክክል ተናግሮአል ሱራ 2:30-35 ሁሉም መላዕክት ከሰይጣን በስተቀር ለአዳም ሰግደዋል:: ሱራ 7:12 አዳም ከተሰጠው መብት በላይ የአላህን ፍጥረት የማጥፋት ስልጣን አልነበረውም፣ መብቱም ፍጥረትን የመንከባከብ፣ የመጠቀምና፣ የመግዛት ነበር:: አላህ አዳምን ሲፈጥረው የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት:: ሰው ከሌላ እንስሳ የሚለየው በዚህ ነው:: ብዙ ሙስሊም ሊቃውንቶች ባይቀበሉትም አንዳንድ የዘመኑ የቁርዓን ሊቃውንቶች ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል ይላሉ:: ይህም ዘፍ1:26-27 ካለው ክፍል ጋር ይስማማል:: አዳም ለሰው ዘር የተላከ የመጀመሪያ ነብይና ህግም ተሰጥቶት ነበር እርሱ ሙስሊም ነበር ማንም ሰው ሲወለድ ሙስሊም ነው:: ነገር ግን ሰይጣን አሳሳታቸው እንጂ በኃጢያት አልወደቁም(Not fall in sin) ኃጢያት አይወራረስም ወይንም የውርስ ኃጢያት የለም::

አንድ ሰው በፍፁም ልቡ አላህን የሚከተልና የሚገዛ ከሆነ ኃጢያትን ማስወገድ ይችላል:: ኃጢያት የሚባለውም ሰውየው በሕይወት ዘመኑ የሚሰራውን ብቻ ነው:: ለኃጢያትም ምንም አይነት መስዋዕት አያስፈልግም:: ሰውን ያሳሳተው ሰይጣን ስለሆነ የመጀመሪያ ተጠያቂ ሰይጣን ነው ይላል::

## 2. የክርስቲያኖች አመለካከት

ስለፍጥረትና ስለሰው አፈጣጠር ከዘፍ 1-3 ባለው ክፍል በዝርዝር እናገኛለን:: እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጥሯል:: እግዚአብሔር ብቻውን ፈጠረ፣ የተፈጠረውም ፍጥረት መልካም ነው አለ:: በአፈጣጠር ስርዓት ውስጥ ሁሉም ነገር ደረጃ በደረጃና ማንም ሊረዳው በሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል::
እግዚአብሔር ሰዎችን ከፈጠረ በኋላ በኤደን ገነት አኖራቸው፣ በዚህ ስፍራ ይፈፅሟቸው ዘንድ የተሰጡ ስራዎች ነበሩ:: እነዚህም ልጅ በመውለድ ምድርን እንዲሞሏቸው፣ ምድርን እንዲገዟት፣ ምድርን እንዲጠብቋትና እንዲንከባከቧት ለእያንዳንዱ እንስሳ ስም እንዲያወጣ እና ከተከለከለው ዛፍ እንዳይበላ ናቸው:: (ዘፍ 1:26-2-17) እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአምሳሉ ፈጠረው:: (ዘፍ 1:26-27) ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር የሰው መልክ አለው ማለት አይደለም::

ነገር ግን ሰው ከእግዚአብሔር የህይወትን እስትንፋስ ተሰጠው ከዚህም የተነሳ ከሌሎች እንስሳት በተለየ የማሰብ ሁኔታ የመናገር ህብረት የማድረግ፣ የማፍቀር እና ሌሎችም ሞራላዊ እሴቶች አሉት ማለት ነው:: እነዚህ በእግዚአብሔር ዘንድ ያሉ ሲሆኑ የሰው ግን ከእግዚአብሔር የሚለየው እሴቶች ውስኖች ናቸው:: የእግዚአብሔር ግን ፍፁምና ውስንነት የላቸውም ::አዳምና ሔዋን እንዳይበሉ ከታዘዙት ዛፍ በሉ በእግዚአብሔርም ፊት ኃጢያት ሰሩ:: ዘፍ 3:1-7 ከእነርሱም የተነሳ የሰው ዘር ሁሉ ኃጢያት ሰራ ሮሜ 3:23 ከአዳምና ከሔዋን የተነሳ ሁላችንም በኃጢያት ተወለድን መዝ(51):5 ከእነርሱም የተነሳ ኃጢያት ለሰው ሁሉ ደረሰ ነገር ግን በክርስቶስ ስራ የደህንነት ፀጋ ተገለጠ ሮሜ 5:12-21፣ 1ቆሮ 15:22፣ ኢሳ 53:6 ሰው ከመሳሳት አልፎ በኃጢያት ወደቀ ከኃጢያትም የተነሳ ከኤደን ገነት ተባረረ:: እርግማንም በሰው እና በምድር ላይ መጣ ዘፍ 3:14-21 አዳምና ሔዋን ተጸጽተው ንስሓ አልገቡም ይልቁንስ ከፍርሃታቸው የተነሳ ተሸሸጉ የሰሩትንም ጥፋት ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም:: አንዱ ሌላውን ተጠያቂ አድርጓል እንጂ ዘፍ 3:12፣13

ከኃጢያት የተነሳ የስጋም የመንፈስም ሞት በአለም ላይ ነገሰ ሮሜ 6:23፤ዘፍ 3:19 ከአዳም ጀምሮ ኃጢያት ሰዎች በህብረት እና በሁሉ ቤተሰብ ላይ መከራን አመጣ:: በዘፍ 4:1-16 ቃየል አቤልን ገደለ:: የሰው ኃጢያት ዋናው መንስኤ ሰው የተሰጠውን ነፃ ፈቃድ በትክክለኛ መንገድ አለመጠቀሙ ነው:: ስለዚህ ለኃጢያት የመጀመሪያው ተጠያቂ ሰው ራሱ ነው:: ሰው ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሄር የደህንነት ተስፋ ሰጠው:: ዘፍ 3:15 ይህም በክርስቶስ የመስቀል ላይ ስራ ተፈፀመ ለኃጢያት ስርየት ደም መፍሰስ ግድ ሆነ ዘሌ 16:፤ዕብ9:7፤14-14፤22፤ኤፌ1:7

## 3. በሁለቱ እምነቶች መሐከል ያሉ ልዩነቶች

ሙስሊሞች አዳም ከተፈጠረ በኋላ ከሰይጣን በስተቀር መላዕክቶች ሁሉ ለእርሱ ሰግደዋል ሲሉ ክርስቲያኖች ይህንን አባባል አይቀበሉትም:: ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጥሯል የሚለው ትምህርት ሙስሊሞች አይቀበሉትም አዳምና ሔዋን ኃጢያት ከሰሩ በኋላ ተጸጽተው ንሰሐ ገብተዋል የሚለው የቁርዓን ትምህረት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ይቃረናል::

እስልምና የውርስ ኃጢአት የለም ሲል ክርስትና የአዳም ኃጢአት ለሰው ዘር ሁሉ ደርሷል ይላል::

እስልምና ከኃጢአት ለመንፃት ሰው የአላህን ፈቃድ ማወቅና መገዛት በቂ ነው ሲል ክርስትና ግን ለሰው አዳኝ ያስፈልገዋል እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡- የማዳኑንም ስራ የፈፀመው በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስና በሞቱ ነው::

እስልምና በአዳም ምክንያት ምድር አልተረገመም ሲል ክርስትና በአዳም ምክንያት ምድር ተረግማለች ይላል:: እስልምና የኃጢያትና የክፋት ምንጭ ሰይጣን ነው ሲል (ሱራ 15:28-31) ክርስትና ግን የኃጢያትና የክፋት ምንጭ ለሰይጣንም ሆነ ለሰው የተሰጠውን ነፃ ፈቃድ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ መጠቀም ነው ይላል:: ሲብራራም ሰይጣን የተሰጠውን ነፃ ፈቃድ ለአመፅ ሲጠቀምበት ኃጢያት ሰራ:: ሰውም እንደዚህ አታድርግ የተባለውን ሲያደርግ በኃጢያት ወደቀ::

## ቅዱሳን መጽሐፍትን በተመለከተ

## 1. የሙስሊሞች አመለካከት

አላህ ሰውን ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ ብዙ ነብያቶች ቢልክም ለአራት ነብይቶች ቅዱሳን መጻሕፍት ተሰጥቷቸዋል::ይህ አስተምህሮ ማንኛውም ሙስሊም ሊቀበለው የተገባ ነው:: እነዚህም መጻሕፍት ተውራት (ኦሪት) ለሙሴ የተሰጠ፣ ዘቡር (መዝሙር) ለዳዊት የተሰጠ፣ ኢንጅል (ወንጌላት) ለኢየሱስ የተሰጠና ቁርዓን (ፋርቃን) ለመሐመድ የተሰጡ ናቸው:: አስር ጥቅልል መጽሐፎች ለአብርሃም ተሰጥተው ነበር ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ አይገኙም:: እነዚህ አራት መጽሐፍት ከሰማያዊ መጽሐፍ ቀጥተኛ ኮፒዎች ናቸው:: ቁርዓን የመገለጦች ሁሉ መጨረሻና ከፊቱ ያሉትን መጽሐፍቶች እውነተኛነት ያረጋግጣል ሱራ3:3-4)::

ቁርዓን ሁሉም ሰዎች ወደ አላህ ፈቃድ ይመለሱ ዘንድ የሚያስተምር የፈጣሪ ቃል ነው:: ከበፊቱ የነበሩት መጽሐፍት ትምህርቶች የያዙና በእነርሱ ውስጥ ያልተገለጡትንም እውነታዎች አካቷል:: ቁርዓን ለነብዩ መሐመድ በመልዓኩ ገብርዔል አማካይነት ተገልጧል ::ሱራ 85:21-22 እያንዳንዱ ቃል፣ ፊደል እና ይዘቱ የአላህ ፈቃድ መገለጥ ነው::መገለጡ ለነብዩ መሐመድ የመጣው በ23 አመታት ውስጥ ሲሆን በ114 ምዕራፎች የተከፈለ ነው:: መገለጡ ከመጣ በኋላ አንድ ላይ እስኪጻፍ ድረስ በተለያዩ ነገሮች ላይ ተጽፎ እንዲሁም በሰዎች አእምሮ ሊቀመጥ ችሏል::

ከቁርዓን በተጨማሪ የመሐመድ ድርጊቶችና ንግግሮችን የያዘው የሐዲስ መጽሐፍ ሙስሊሞች ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያስተምራል:: ቁርዓን የአላህ ፈቃድ መገለጥ እንጂ አላህ ራሱ በቁርዓን ውስጥ አልተገለጠም ብለው ያስተምራሉ::

## 2. የክርስቲያኖች አመለካከት

ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው የፃፉትና የሰው ልጆች ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የሚያደርግ ነው። 2ጴጥ1:20-21 2ጢሞ3:16-17 ከእግዚያብሔር ንግግር የተገለበጠ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነገር ግን የራሳቸው የአፃፃፍ ስልትን በመጠቀም ያለምንም ስህተት የተፃፈ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጥና የእግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ ውስጥ መገለጥ በተለይም ተሰገዖ (incaration) በክርስቶስ በኩል መገለጡን የያዘ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ያደረገውን ሁለት ኪዳኖች የያዘ ነው አዲስ እና ብሉይ ኪዳን ናቸው የብሉይ ኪዳን ነብያቶች የአዲስ ኪዳን ተስፋ የሚፈፀመው በመሲሁ በኩል እንደሆነ ጽፈዋል። 2ሳሙ7:12-13 መዝ22:16-17 ብሉይ ኪዳን ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት ኦሪት፣የታሪክና የግጥም መጽሐፍት፣ እና የነብያት መጽሐፍት ናቸው። አዲስ ኪዳን አራት አይነት መጽሐፍት የያዘ ሲሆን እነዚህም ወንጌላት፣የሐዋርያት ስራ፣የሐዋርያት መልዕክት፣ እና የዮሐንስ ራዕይ ናቸው። የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተፃፉት በዚያን ዘመን ለነበሩት ሰዎች ምሪት እንዲሰጥ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ወደፊትም ላሰው ህዝብ ታስቦ ነው።

## በሁለቱ እምነቶች መካከል ያለው ልዩነት

ሙስሊሞች ቁርዓን የአላህ ፈቃድ መገለጥ ነው ሲሉ ክርስቲያኖች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ እየገባ ፈቃዱና ማንነቱን የገለጠበት መጽሐፍ ነው ይላሉ ዮሐ 1:1-18 ሙስሊሞች ቁርዓን ከአላህ ንግግር ቃል በቃል የተገለበጠ ነው ሲሉ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የራሳቸውን ባህል፣ቋንቋ እና የአፃፃፍ ዘዴያቸውን ተጠቅመው ነው ይላሉ። 2ጴጥ1:20-21 ሙስሊሞች ተውራት፣ዘቡር፣ኢንጂልና ቁርዓን የአላህ መገለጦች ናቸው ብለው ሲያምኑ ክርስቲያኖች ቁርዓን የእግዚያብሔር ቃል አይደለም ይላሉ። ምክንያቱም ከክርስቶስ በኋላ በስልጣን መጽሐፍ የሚጽፍ ነብይ አይነሳም እንዲሁም ቀኖና ከተሰራ በኋላ መጽሐፍት አይፃፍም ብለው ስለሚያምኑ ነው። በተጨማሪም ቁርዓን ወይንም የነብዩ መሐመድ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በብዙ ስለሚቃረን ነው ገላ1:6-8።

ሙስሊሞች ተውራት፣ዘቡር፣እና ኢንጂል የተላኩት (የተፃፉት) በዚያ ዘመን ለነበሩ ሰዎች ብቻ ነው ቁርዓን ግን ከነብዩ መሐመድ በኋላ ላለው ትውልድ ሁሉ ነው የሚል አመለካከት አላቸው ነገር ግን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በእስራኤላዊያን አውድ ቢፃፍም ለሰው ዘር ሁሉ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ላለ ሰው ያገለግላል፣ ምክንያቱም የሚናገርበት መንገድ ይለያያል እንጂ የፈጣሪ መልዕክት አንድ አይነት ነው። ማቴ5:17-19 ሙስሊሞች በአብርሃም የተጻፈ ጥቅልሎች ነበሩ ሲል ክርስቲያች ይህንን አይቀበሉም።

## ነብያትን በተመለከተ

## 1. የሙስሊሞች አመለካካት

በእስልምና እምነት ነብያቶች በሁለት ይከፈላሉ።
ነብያት (Nabi):- መልዕክታቸው/ትምህርታቸውን በጽሑፍ ያላስቀሩ/ያልፃፉ።
መልዕክተኞች (Massangers):- ትምህርታቸውን በጽሑፍ ያስቀመጡ ለምሳሌ ሙሴ፣ ዳዊት፣ኢየሱስና መሐመድ ናቸው ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ነብያት ተልከላቸዋል። በአጠቃላይ 124000 ነብያቶች ወደ ምድር ተልከዋል እነዚህን ሰዎች ወደ አላህ ፈቃድን ለመመለስ የተላኩ ናቸው ቁርዓን 25 ነብያቶችን በስም ይጠቅሳቸዋል። መሐመድ የነብያት ሁሉ መደምደሚያና ትልቁ ነብይ ነው ትልቅነቱን ያገኘው ከማንነቱ ሳይሆን ከመልዕክቱ ነው።

ከመሐመድ ቀጥሎ በቁርዓን በሰፊው የተነገረለት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የቁርዓንና የሙስሊሞች አመለካከት:-

ኢየሱስ ከድንግል ተወልዷል (ሱራ19:20) ነገር ግን ያለአባት በአላህ ፈቃድ ተወለደ ሱራ 19:21-22 ኢየሱስ የአላህ ነብይና መልዕክተኛ ሲሆን የመጣውም እስልምናን ሊሰብክ ነው:: ሱራ19:31-31 3:84 አገልግሎት የጀመረው በልጅነቱ ነው ሱራ5:110፣ሱራ19:29-33 ከጭቃ ወፎችን ሰርቶ እፍ አለባቸው ህያው ፍጥረትም ሆኑ ሱራ5:110 ለእስራኤል መልዕክተኛ እንዲሆን ተልኳልም ሱራ3:49 ተዐምራት አድርጓል ሱራ3:49፣ 5:110፣ 5:112-115 ክርስቶስ በመስቀል ላይ አልሞተም:: ሱራ4:157-158 ወደ ሰማይ ወስዶታል፣ በመስቀል ላይ የሞተው ሌላ ሰው ነው በተቃራኒው አላህ ቁርዓን ስለክርስቶስ መሞቱንና ትንሳዔ ፍንጭ ይሰጣል ሱራ19:33፣ 5:117፣ 3:55 አንዳንድ ሙስሊም ሊቃውንቶች ክርስቶስ የሚሞተውና ከሞት የሚነሳው ወደፊት ወደዚህ ምድር ሲመለስ ነው ሲሉ ሌሎች በዚህ ሀሳብ አይስማሙም ሱራ6:164፣ 17:15፣ 35:18 ክርስቶስ ደግሞ ይመሰሳል ሱራ43:61 ስለነብዩ መሐመድ መምጣትም ትንቢት ተናግሯል ሱራ61:6፣ 7:157 ቁርዓን ለክርስቶስ የማዕረግ ስሞችን ይሰጣል::እነዚህም ስሞች ከማንነቱና ከስራው ጋር የተያያዙ ናቸው ለምሳሌ ኢሳ እና መሲህ (ሱራ4:171)፣የማርያም ልጅ (ሱራ4:171)፣ የአላህ አገልጋይ (ሱራ4:43:57-59፣ 3:59)፣ ነብይ (ሱራ2:87፣4:157)፣የአላህ መንፈስ (ሱራ4:171)፣የአላህ ቃል (ሱራ3:45፣4:171)፣የእውነት ቃል ነው በዚህ ዓለምና በመጪውም የተከበረ ለአላህ የቀረበ ለሠው ዘር ምልክት ነው:: ሱራ19:34፣ 3:45፣ 46 ክርስቶስ አምላክ/የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም ሱራ112፣53:19-21፣ 5:17፣72-73 4:171፣ 5:116 ኢየሱስ ኃጢያት የለበትም ሱራ19:19 ምክንያቱም ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ነብይ ስለነበር ነው ይላሉ:: ሌሎች ነብያት ኃጢያት ሰርተዋል ነገር ግን ንስሐ ገብተው ይቅርታ አግኝተዋል:: ሱራ11:47፣ 71:26-28፣ 40:55፣ 26:70-82 የእርሱ የሆኑት አልተቀበሉትም ሱራ3:52

## 2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የክርስቲያኖች አመለካከት

ኢየሱስ ከድንግል ማርያም ተወልዷል ሉቃ1:32:35፣ ዮሐ5:17-18 ዮሐ3:16፣ ማር14:61-64 እርሱም አምላክ (እግዚአብሔር) ነው ዮሐ1:1፣ ሮሜ9:5፣ ኢሳ9:6፣ ዕብ1:8፣ ፊል2:5-11 እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው ዕብ1:3፣ ቆላ1:16 ክርስቶስ ፈራጅ ነው:: ማቴ 25:31-46 ዮሐ5:27 ክርስቶስ ኃጢያትን ያስተሰርያል ማር2:5 አምልኮንም ተቀብሎአል:: ዕብ1:6፣ ዮሐ9:37፣ ማቲ15:25 እርሱ የአለም ብርሃን ነው ዮሐ1:9 እርሱ ህይወት ነው ዮሐ14:6 እርሱ ነብይ ነው ሐዋ3:22 ባሪያ ተብሏል ፊል2:7-8 እርሱ ካህን (ከአብ ጋር) አስታራቂ ወይንም አማላጅ ነው ዕብ7:25 እርሱ አዳኝ ሲሆን ሮሜ6:24፣ ሉቃ 2:11 ሰዎችን ለማዳን በመስቀል ላይ ሞቷል:: ኢሳ53:1-12፣ ማር8:31-33፣ 9:30-32፣ ማር10:32-34፣ ማቲ12:40፣ ማር14-16፣ ማቲ26:28፣ ሉቃ22-24 እና ዮሐ18-21 አገልግሎት የጀመረው በ30 አመቱ ነበር::ዳግም ተመልሶ ይመጣል ሐዋ1:11 መጀመሪያና መጨረሻ ነው ራዕ1:18 ዘላለማዊ ነው ዮሐ8:58፣ ራዕ1:18፣ ኢሳ9:6 በሁሉ ስፍራ ይገኛል ማቲ28:20፣ ከስላሴ አካላት አንዱ ነው ማቲ28:18፣20 2ቆሮ13:14፣ 1ኛዮሐ5:7 እርሱ ጌታ ነው ዮሐ20:28

## የደህንነት መንገድ

## 1. የሙስሊሞች አመለካከት

ሰው በተፈጥሮው ኃጢያተኛ ስላልሆነ ወደአላህ ፈቃድ ለመምራት ትምህርት ብቻ ያስፈልገዋል:: መዳን የሚችለውም በቁርዓን ውስጥ ለተገለጠው እውነት በመታዘዝ ነው ይህም ሁለት ነገሮችን የያዘ ነው::

**ሀ. እምነት ማንኛውም ሰው ለመዳን ስድስቱ የእምነት አቋሞች በሙሉ ልብ መቀበል አለበት**

እነዚህም በአላህ አንድነት ማመን ከአላህ የተላኩ ነብያቶች/መልዕክተኞች መኖራቸውን ማመን በአላህ መላዕክት ማለትም ቅዱሳን መላዕክት እና የወደቁ መላዕክት (ሰይጣንና ጅኒ) መኖራቸውን ማመን ከአላህ ነብያቶች የተሰጡ መጽሐፎች (ተውራት፣ ዘቡር፣ ኢንጂል፣ እና ቁርዓን) መኖራቸውን ማመን፣ የፍርድ ቀን መኖሩን ማመን፣እና ሁሉንም ነገር በመጀመሪያ በአላህ መወሰኑን ማመን ናቸው::

**ለ. በሁለተኛ ሰው ለመዳን አምስቱን ሀይማኖታዊ ግዴታዎች መፈፀም ያስፈልገዋል::**

1. እነዚህም ሸሃድ፣የአላህ አንድነትና ነብዩ መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ እንደሆኑ
   ደጋግሞ መጥራት:-ይህም በአረብኛ«አሸሀድ አለ ኢለህ ኢል አላህ ወአሸሀድ አላህ መሐመድ ረሱል አላህ» ይህም አላህ አንድ ነው መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ማለት ነው::
2. በቀን አምስት ጊዜ ደንቡንና ስርዓቱን ጠብቆ ሠላት መስገድ
3. በረመዳን ወር ለሰላሳ(30) ቀናት መፆም
4. ዘካ መስጠት ይህም አንድ ሰው ከአመት ገቢው 2.5% ለድሃ መስጠት
5. ገንዘብ ያለው ሰው በህይወት ዘመኑ ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጉዞ (ሐጅ) ማድረግ አለበት::

ከእነዚህም ውጪ ሐይማኖቱ የሚያዘውን ተግባራት መፈፀም ይጠበቅበታል:: ስለዚህ በእስልምና እምነት ሰው ለመዳን እምነትና ስራ ያስፈልገዋል:: በእምነት ብቻ መዳን አይችልም ፣ መዳኑን የሚያውቀውም በፍርድ ቀን ብቻ ነው:: መዳኑ የሚረጋገጠው መልካም ስራውና ክፉ ስራው ከተመዘነ በኋላ ነው::ለደህንነት መስዋዕት አያስፈልግም ኢየሱስ ለሰዎች ደህንነት ሲል አልሞተም ሰው የሚጠየቀው በህይወት ዘመኑ በሰራው ስራ እንጂ በአዳም ኃጢያት አይደለም::

## 2 . የክርስቲያኖች አመለካከት

ሰው በተፈጥሮው ኃጢያተኛ ነው ምክንያቱም አዳምና ሔዋን ኃጢያት ሲሰሩ በእነርሱ ውስጥ ሆነን እኛም ሠርተናል:: ምክንያቱም የእነርሱ ኃጢያት ወደ ሰው ዘር ሁሉ ተላልፏል:: ሮሜ5:12-21፣ ዘፍ3:1፣ ሮሜ3:23 የኃጢያት ዋጋው ሞት ነው:: ሮሜ6:23 ሁሉም ሰው ወደ ገዛ መንገዱ አዘንብሏል ማንም እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም:: ኢሳ53:6 ኃጢያታችን ከእግዚአብሔር ለይታናለች ኢሳ59:1-3፣ ሮሜ5:10 ኃጢያት የምትሰራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች:: ሕዝ18:1-4 ሰው ከኃጢያቱ የተነሳ ተስፋ የሌለውና ለጥፋት (ለዘላለም ቅጣት) የተመደበ ነው:: ኢፌ2:19፣ ዮሐ3:16፣ 2ተሰ1:6-10 ለሰዎች ደህንነት የሚያስፈልጋቸው በኃጢያት ምክንያት ስለጠፉ ነው በተፈጥሮአቸው ጥሩዎች ቢሆኑ ደህንነት አያስፈልጋቸውም::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ራሱን ማዳን አይችልም ይላል ደህንነትን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው:: ኢሳ59:1-4፣15:21 ሉቃ18:23-27 ሮሜ5:6-8 የደህንነት ምንጭና ጀማሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው ዘፍ3:15 6:17-18 12:3 22፣12-19 ዘፀ 12:21-30 ዕብ11:28፣ ዘሌ16:1-34 ራዕ 13:8 ዮሐ1:29 ሮሜ5:6-8 1ዮሐ4:7-10 ማር10:45፣ 2ቆሮ5:16-19 የደህንነት መሠረቶች የእግዚአብሔር ምህረት ፍቅርና ፀጋ ናቸው:: ሰው ሁሉ የሚድነው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በማመን ለሚያምን ሁሉ የክርስቶስ ደም ከኃጢያት ሁሉ ያነፃል ምክንያቱም ደም ሳይፈስ ስርዬት የለም:: ዕብ9:7፣ 13-14፣

22:10-19-22 ኤፌ1:7 ራዕ5:6-10 የደህንነት ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነው:: ሐዋ4:12፣ዮሐ14:6 ዮሐ3:16 17:3 ለመዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ግድ ነው ምክንያቱም በኃጢያታችን ምክንያት ሞት ይገባን ነበር ነገር ግን በእኛ ፈንታ እርሱ ሞቶ አዳነን:: ለደህንነት ቁልፍ ነገር እምነት እንጂ ስራ አይደለም ዘፀ12:21-29 ዕብ11:28 ኤፌ2:8-10 ሮሜ3:23-25 ዮሐ5:24 የእምነት ይዘቱ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ሰው በኃጢያት ምክንያት የጠፋና ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ወደምድር በመምጣት ለኃጢያታችን ስርየት በመስቀል ላይ ሞቶ ከሦስተኛ ቀን በኋላ ከመቃብር መነሳቱንና ብቻውን የደህንነት መንገድ እርሱ መሆኑን ነው::ሮሜ10:9-10 መልካም ስራ በዳነ ሰው ህይወት የሚታይ የደህንነት መግለጫ እንጂ መዳኛ መንገድ አይደለም:: ኤፌ2:8-9 ያዕ2:18-26

## በሁለቱ እምነቶች መካከል ያለው ልዩነት

ሙስሊሞች ሰው የውርስ ኃጢያት የለበትም ይላሉ ነገር ግን ክርስቲያኖች ሰው ከአዳም የወረሰው ኃጢያትና ራሱም እየሰራው ያለ ኃጢያት አለበት ብለው ያምናሉ:: ሰው ለመዳን መልካም ስራ መስራት (ሃይማኖታዊ ግዴታዎች መወጣት)እስልምና እና በእስልምና የእምነት አቋሞች ማመን አለበት ይላሉ:: ይህም ማለት ለደህንነት እምነትና ስራ አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን በጣም ትኩረት የሚሰጠው መልካም ስራ ነው:: ክርስቲያኖች ግን ሰው የሚድነው በክርስቶስ በማመን ብቻ ነው መልካም ስራ የእምነት ወይንም የደህንነት መግለጫ ነው::

ሙስሊሞች ለደህንነት ምንም አይነት መስዋዕት አያስፈልግም ሲሉ ክርስቲያኖች ግን ክርስቶስ ስለኃጢያተኞች በመስቀል ላይ መስዋዕት ሆኖአል ይላሉ::ሙስሊሞች እስከ ፍርድ ቀን ድረስ መዳናቸውን እርግጠኞች አይሆኑም ነገር ግን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያመነ ሁሉ በመዳኑ እርግጠኛ ነው ይላሉ::

# ለሙሲሊም ጥያቄዎች መልስ

## መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች

### 1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ በምን እናውቃለን

**መልስ**

መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ መገለጥ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እና ቁርዓን ያረጋግጣሉ. 2ኛጴጥ 1:20-21 «ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍት ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ፣ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» ይላል:: ይህ ክፍል የሚያሳየን መልዕክቱ ከእግዚአብሔር ሲሆን ፀሀፊዎቹ በእግዚአብሔር መንፈስ የተመሩ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው:: ይህም ቃል ሰዎችን ሁሉ ወደእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ለመመለስ ለሰው ልጆች የተሰጠ ነው:: 2ጢሞ3:16-17፣ መዝ119:105 ቁርዓንም ስለመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ ምስክርነት ይሰጣል:: እግዚአብሔር ለነብያቶች መጽሐፍትን እንዲላኩ ይገልፃል:: እነዚህም ተውራት፣ ዘቡር፣ እና ኢንጅል በመባል ይጠራሉ እኛ መጽሐፍ ቅዱስ የምንለው መጽሐፍ ማለት ነው:: ሱራ5:44-48 አይሁዶችና ክርስቲያኖችም አላህ በሰጣቸው መጽሐፍ መመሪያ መሠረት እንዲኖሩ ያዛቸዋል ሱራ5:43፣47 ይህንንም መጽሐፍ ሙስሊሞች በሙሉ ነብዩ መሐመድን ጨምሮ እንዲቀበሉና እንዲያምኑበት ያሳስባል:: ሱራ2:136

## 2. መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው ለጥንት ሰዎች ስለሆነ በቁርዓን ተተክቷል

ዘላለማዊ ቃል ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ የተሰጠ ነው አሁን ስለተሻረ ለዚህ ትውልድ አያገለግልም።

**መልስ**

መጽሀፍ ቅዱስም ይሁን ቁርዓን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሯል ወይንም ተቀይሯል የሚለውን አመለካከት ይቃወማል ዕብ4:12 የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም ሁለትም አፍ ካለው ሠይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው...ይላል። «ህያው» ማለት የማይሻር፣ የማይሞት፣ ወይንም የማይጠፋ ማለት ነው። በማቴ5:17-18 ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር መጽሐፍትንና ነብያትን ለመሻር ሳይሆን የመጣው ለማጽናት እንደሆነ በአጽንኦት አስገንዝቧል። ይህንን መልዕክት በማቴ24:35 እና በዮሐ10:35 ደግሞታል ነብዩ ኢሳያስም በኢሳ40:8 «ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል የአምላካችን ቃል ለዘላለም ፀንታ ትኖራለች» ሲል የእግዚአብሔርን ቃል ዘላለማዊነት ገልፆአል። ቁርዓንም የእግዚአብሔርን ቃል ሲቀይር እንደማይችል በሱራ6:34 እና 10:64 ይናገራል።

## 3. መጽሀፍ ቅዱስ ተበላሽቷል ስለዚህ

የተበላሸን መጽሐፍ መጠቀም አግባብ አይደለም ይልቁንስ ያልተበላሸ ቁርዓን ስለሆነ መጠቀም መልካም ነው።

**መልስ**

መጽሐፉ ያልተበላሸ እንደሆነ ጥንት ከነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎችና ትርጉም መጽሐፍት ጋር አንድ አይነት መሆኑን በቂ መረጃዎች አሉ። ታዋቂና የተከበሩት የሙስሊም ስነ መለኮት የቁርዓን ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ያልተበላሸ/ያልተበረዘ/ እንደሆነ ይስማማሉ። በ11ኛክ/ዘመን የኖረው ኢብን ሐዝም በ1209 የሞተው ፋህሩዲን ራዚ የተሰኘው ሙስሊም ፈላስፋና የቁርዓን ሊቅ አል-ታባሪ የተባለው ሙስሊም የታሪክ ሊቅ እና አቡ ሐሚድ አል -ጋዛሊ የተሰኘው የስነ መለኮት ሊቅ መጽሀፍ ቅዱስ በምንም መልኩ ችግር እንደሌለበት ጽፈው አልፈዋል።ቁርዓን በየትኛውም አንቀፅ መጽሐፍ ቅዱስ በጽሑፍ ደረጃ ተበላሽቷል አይልም። በሱራ-4:46፣ 2:75፣ 5:13-14፣ 5:41፣ 3:71፣ እና 3:77-78 አይሁዶችና ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ቀይረዋል ይላል። ነገር ግን በእነዚህ ጥቅሶች ቁርዓን የሚናገረው ክርስቲያኖችም ሆኑ አይሁዶች ከመጽሐፉ የተወሰነ ክፍል አውጥተው ሌላ ጨምረዋል አይልም። ይልቁንስ ቃሉን ሲያስተምሩ ወይንም ሲሰብኩ በመጽሀፍ የሌለውን ያስተምራሉ ነው የሚለው። በአረብኛ ቋንቋ ለንግግር «ከላም» የሚል ቃል ሲጠቀም በጽሑፍ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል «ኪታብ» ይለዋል።ስለዚህ በእነዚህ የቁርዓን ጥቅሶች ቁርዓን የተጠቀመው «ከላም» የሚለው ቃል ነው። ይህም ማለት አይሁዶችና ክርስቲያኖች ከመጽሐፉ ሲያስተምሩ አጣመው ያስተምራሉ ማለት እንጂ ቃሉን በጽሁፍ ደረጃ ቀይረውታል ማለት አይደለም። ለበለጠ መረጃ «Holy quran» በአብደላ ዩሱፍ አሊ ወደእንግሊዘኛ የተተረጎመውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

ከነብዩ መሀመድ ልደት በፊት የነበሩ ቅዱሳን ነብያት እውነተኛ ናቸው ብለው የመሰከሩላቸው በተለያየ ቋንቋ የተተረጎሙት መጽሐፈ ቅዱሳት ህያው ምስክሮች ናቸው። እነዚህም በአሁን ጊዜ በእጅ ይገኛሉ። ለአብነት ያህል ለመጥቀስ

1. የአሌክሳንድርያ መጽሐፍ (Alexandrines codex)
2. የሰናይቲክስ መጽሐፍ (Codex Semantics)
3. የቫቲካነስ መጽሀፍ (Codex Vatican us)

4. የእብራይስጥ ማዛሬቲክ መጽሀፍ (The Hebrew massoretic text)
5. የሙት ባህር ጥቅልል (Dead sea scroll)
6. ሰፕቱጀንት
7. የላቲን ቩልጌት ናቸው።

## 4. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን ሦስት አይነት ንግግሮችን የያዘ ነው

እነዚህም የእግዚአብሔር ንግግር የነብያት ቃልና የፀሀፊው ሐሳብ ናቸው። ቁርዓን ግን እንደዚህ አይደለም ስለዚህ እንዴት መጽሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሊባል ይችላል?

**መልስ**

መጽሀፍ ቅዱስ ቃል በቃል የተፃፈ ሳይሆን ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የበላይ ተቆጣጣሪነት በራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና የአፃፃፍ ዘይቤ የተፃፈ ነው።

እግዚአብሔር ፈቃዱንና ማንነቱን የገለጠው በራሳቸው አውድ ውስጥ ነው። ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መልዕክት በሰዎች ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ተገልጧል። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች የሰይጣንና የመላዕክት ንግግሮችን የያዘው በእነዚህ ንግግሮችና ታሪኮች ውስጥ እግዚአብሔር ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት አስተላልፏል። መጽሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል የሚያሰኘው በውስጥ የሚተላለፈው መልዕክት ነው እንጂ በመፅሀፍ ያሉት ቃላት ሁሉ እግዚአብሔር ለነብያት ቃል በቃል የተናገረው ማለት አይደለም። ቃል በቃል መሆን ነበረበት ብለን ካሰብን ተሳስተናል።

በሌላ አንጻር ቁርዓንን ስንመለከት በውስጥ ያሉት ንግግሮች ሁሉ የአላህ አይደሉም። ቁርዓን የአላህ ንግግር፣የሰዎች፣የመላዕክት፣የሰይጣን ንግግሮችና ታሪኮችን የያዘ ነው። ለምሳሌ ዘካሪያስ ከመላዐከ ጋር ያደረገው ንግግር /ሱራ19:8 እና 3:40-41/ ተመልከቱ የገብርኤል ንግግር /ሱራ-19:64/የሰይጣን ንግግር ሱራ7:12 እና የተለያዩ ታሪኮች /ሱራ19:20/እንዲሁም ሌሎችም ታሪኮች ይገኙበታል።

## 5. ብዙ የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም መጽሐፍት /Versions/ ስላሉ ተበላሽቷል አንድ ወጥ መልዕክት አያስተላልፉም

**መልስ**

በእርግጥ መጽሀፍ ቅዱስ በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፣ በአማርኛ ቋንቋም ሦስት የትርጉም መጽሀፍት አሉን። በእንግሊዘኛ ደግሞ ብዙ ናቸው። ብዙ የትርጉም መጽሀፍት ስላሉ የእግዚአብሔር ቃል ተበላሽቷል ከማለት ይልቅ መጽሀፍ ቅዱስ የሚተረጎመው እንዴት ነው ? ለምንስ ብዙ ትርጉሞች አሉት? ብሎ መጠየቅ ይሻላል ማንኛውም ጽሑፍ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጎም በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ነው።

እነዚህም፦

1. ቃል በቃል መተርጎም (Literal Translation) ይህም መጽሀፉ ላይ ያለውን ሐሳብ ቃል በቃል መተርጎም ማለት ነው።
2. ሐሳብን መተርጎም (Paraphrased Translation) ይህም ደግሞ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር ወይንም አንቀፅ ውስጥ ያለውን ሐሳብ /መልዕክት/ መተርጎም ማለት ነው።

3. ቃል በቃልና ሐሳቡን ማዕከል ያደረገ ትርጉም /Dynamic equivalent/ እንዲህ አይነቱ
ደግሞ ከሁለቱ መካከለኛ የሆነ ትርጉም ነው፡፡

ስለዚህ መጽሀፍ ቅዱስም ቁርዓንም እንዲሁም ሌሎች ጽሁፎች በእነዚህ በሶስቱ መንገዶች ይተረጎማሉ ይህም ህጋዊም አለማቀፋዊም ስርዓት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በእንግሊዘኛው ቋንቋ ብዙ ቁርዓኖች አሉ ለምሳሌ «Holy Quran, glorious Quran Sales Quran» እና ብዙ የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንዳሉ ሁሉ የቁርዓንም አሉ፡፡ እነዚህ የትርጉም መጽሀፍ የቃላት ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል ነገር ግን የሐሳብ መዛነፍ አይታይባቸውም በአጠቃላይ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም መፅሀፍት ሁሉ ተበላሸ ካልን የቁርዓንስ በምን ተለየ ?

## 6. መጽሀፍ ቅዱስ 50,000 ስህተት ካለበት እንዴት የእግዚአብሔር ቃል ሊባል ይችላል?

**መልስ**

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ 50000 ስህተቶች አሉ የሚለው ተቃውሞ በመረጃ ያልተደገፈ መሠረትቢስ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ የዚህ ተቃውሞ ምንጭ ከ35 ዓመታት በፊት በይሖዋ ምስክሮች ተጽፎ የወጣ መጽሀፍት ሲሆን ወደሙስሊም ህብረተሰብ ጆሮ ያደረሱት ሚስተር አህመድ ዲዳት ናቸው፡፡ የይህዋ ምስክሮችም ሆኑ አህመድ ዲዳት ስህተቶቹን ለመዘርዘር አልደፈሩም፣ ስህተቶቹን በውል ስለማያውቋቸው በደፈናው ለመዘርዘር ጊዜ የለንም በማለት ተቃውሞዎቻቸውን ዘግተዋል፡፡ መረጃም አልሰጡም እንዳይባሉም ሚስተር አህመድ ዲዲት ከ50000 ስህተት አለ ካሉት ውስጥ አራቱን ጠቅሰዋል፡፡

በጣም የሚገርመው ግን እርሳቸው ስህተት ያሉት በተለያየ ትርጉም መጽሐፍት መሐከል ያለውን የቃላት ልዩነት ነው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር 5 ላይ እንደተመለከትነው የተለያዩ ትርጉሞች የቃላት ልዩነት ቢኖራቸውም አንድ አይነት መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ይህ ስህተት ሳይሆን የትርጉም ዘዴው ያመጣው ነው፡፡ ለምሳሌ አህመድ ዲዳት ካነሱት ውስጥ አንዱ በኢሳ7:14 ላይ ይገኛል፡፡ በRSV ላይ «ወጣት ሴት» ብሎ ሲጠቀም በKJV ላይ «ድንግል» ተብሎ ተጽፏል፡፡ በሁለት የእንግሊዘኛ ትርጉም መጽሀፍት ለመግለጽ የተፈለገው ሐሳብ« ወንድ ያልነካት ሴት» የሚል ነው፡፡

በእስራኤል ባህል ወጣት ሴት እና ድንግል አንድ አይነት ትርጉም አለው ምክንያቱም ሴት ሳታገባ ግብረ ስጋ ግንኙነት ስለማትፈጽም ነው፡፡ የቀሩት ሶስት ተቃውሞዎች ተመሳሳይ ይዘት አላቸው፡፡ 50000 ተብለው የተጠቀሱት በተለያየ የትርጉም መጽሀፍት መሐከል ያለውን የቃላት ልዩነት ከሆነ ቁርዓን ብዙ ሺህ ስህተት አያጣውም፡፡ ተቃውሞ በግብታዊነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በማስተዋልና በጥንቃቄ መረጃም ባለው መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

## 7. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ አሳፋሪ የሆነ የቅዱሳን ነብያት ኃጢዓት ታሪክ ለምን ይፃፍበታል ?

ለምሳሌ በ2ሳሙ·11:12 የዳዊትና የቤርሳቤህ የዝሙት ኃጢዓት

**መልስ**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ኃጢአት መናገር የለበትም የሚል ምንም አይነት ምክንያት የሚኖር አይመስለኝም፡፡ ይልቁንስ የእግዚአብሔርን ቅድስና የምናውቀው የሰዎችን ኃጢያተኛነት በደንብ ሲገባን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እውነት በተደጋጋሚ ያስተምራል በሌላ አንጻር ደግሞ ሰው በተፈጥሮ ኃጢሃተኛ መሆኑን የምናውቀው ከትልቅ እስከትንሽ ኃጢሃት መስራቱን ነው፡፡ በሮሜ3:23 «ሁሉ ኃጢሃትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» ይላል፡፡ የታላላቅ ነብያት ውድቀትና ስህተት

የተዓፊልን እንድንጠነቀቅና ከእነርሱ እንድንማር ነው። እንዲህ አይነት ታሪክ መጻፍ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ካላሰኘው ቁርዓን ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ምን እንበላቸው? የዳዊትን ኃጢሃት በሱራ7:172-173 የኖህ በሱራ71:24-28 የአብራሃም በሱራ26:81፣6:77-78፣2:263፣ የአሮን በሱራ7:146-151፣20:86-89 የመሐመድ በሱራ 47:19 ተጽፏል።

## 8. መጽሐፍ ቅዱስ ስነ መለኮታዊ /Theological / አስተምህሮአዊ /Doctrinal / እና ስነ ምግባራዊ /Ethical/ ግጭቶች አሉበት እነዚህን ግጭቶች ጥቅስ በጥቅስ ማቅረብ ይቻላል። ዘርፈ ብዙ ግጭቶች ያሉበት መጽሐፍ እንዴት እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይችላል ?

**መልስ**

መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጋጫል በውስጡም ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉበት የሚለው አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ባህርያት ያላገናዘበ ነው። ሰዎች መጽሀፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስላቸው የመጽሐፉን የአፃፃፍ ስልት ባህርያት የአጠናንና የአተረጓጎም ዘዴ ስለማያውቁና በእነዚህ ዘዴዎች ተጠቅመው ስለማያጠኑ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት ለመረዳት ከዚህ በፊት ከተለያየ አቅጣጫ የሰማናቸውን ሐሳቦች አስቀምጠን መጽሐፉ ራሱ እንዲናገር መፈለግ ይኖርብናል ከዚህ ቀጥለን የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ መልዕክት ለመረዳት የሚረዱን ነጥቦችን እንመለከታለን።

### ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና የመጽሐፉን አውድ /ከታችና ከላይ/ ያሉትን ሐሳቦች መመልከት በአንድ ጥቅስ ውስጥ ያለውን ሐሳብ እንድንረዳ ይጠቅመናል

**ለምሳሌ**

በዮሐ5:31 እና በዮሐ8:14 መሀከል ግጭት እንዳለ ዶክተር ሐሰን «ክርስቲያንና ሙስሊም» በሚለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል። ክፍሎቹም እንዲህ ይነበባሉ «እኔ ስለእኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም» ዮሐ 5:31 የሚለው በዮሐ8:14 «እኔ ስለራሴ ምንም እንኳን ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴት እንደምሔድም አውቃለሁ ምስክርነቴም እውነት ነው» ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ይጋጫል። በእርግጥም አውዱን በጥንቃቄ ካልተመለከትን የሚጋጭ ይመስላል። በዮሐ5:31 ያለው ሐሳብ ከቁጥር 31-40 ካለው ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው በዚህ ክፍል ኢየሱስ እየተናገረ ያለው በዘዳ 17:6 በተዓፊው ህግ መሰረት የአንድ ሰው ምስክርነት ተቀባይነት ስለሌለው በህጉ መሠረት ለብቻዬ የምሰጠው ምስክርነትን አትቀበሉም ነው የሚላቸው፣ ተቀባይነት እንዲኖረውም ምስክሮች ያስፈልጉታል። ስለዚህ ከቁጥር 31 በመቀጠል ሌላ ምስክር እንዳለውና ስለእውነትም እንዳሚመሰክር ይናገራል። ምስክሮቹንም ሲዘረዝር መጥምቁ ዮሀንስ፣አብ እየሰራው ያለውን ስራ እና ቅዱሳን መፃህፍት ናቸው ይላል።

ከቁጥር 31-40 ባለው ክፍል ደግሞ የሚገልፀው ኢየሱስ ብቻውን ስለራሱ ቢመሰክር በህጉ አንፃር ምስክርነቱ እውነት እንዳልሆነ ነገር ግን ሌሎች ምስክሮች እንዳሉት ይገልፃል። ምስክር ያቀረበበት ምክንያት ሰዎች ይድኑ ዘንድ ነው እንጂ ያለምስክር የራሱ ምስክርነት እውነተኛ እንደሆነ ይገልጻል። ነገር ግን በዮሐ 8:14 ፈሪሳውያን አንተ ሰው ስትሆን ስለራስህ የምትሰጠው ምስክርነት እውነት አይደለም ሲሉት እርሱ አምላክ ስለሆነ ያለምንም ምስክር ምስክርነቱ እውነት እነደሆነ ይናገራል። በዮሐ5:31 ላይም ምስክር ያቀረበው እነርሱ ይድኑ ዘንድ እንጂ ውሸት ስለሚናገር አይደለም። ስለዚህ ኢየሱስ ዮሐ5:31 ላይ የተናገረው ከህግ እና ከፈሪሳውያን መዳን አንፃር ሲሆን ዬሐ8:14 ላይ ግን ከመለኮታዊ ማንነቱ አንፃር የተናገረው ነው። ሁለቱ ጥቅሶች የሚጋጩ

አይደሉም:: ሌሎቹንም ጥቅሶች አውዳቸውን ጠብቀን ከመረመርናቸው አይጋጩም:: ሌላ ሁለተኛ ምሳሌ ልስጥና ወደ ሌላ አልፋለሁ::

በማቴ፡15:24 «ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ» ስለዚህ ኢየሱስ የአለም ሁሉ ጌታና መድሐኒት ነው ከሚለው የክርስትና ትምህርት ጋር ይቃረናል የሚል ተቃውሞ ይነሳል:: ይህንን ጥቅስ ብቻ ከተመለከትነው የሚቃረን ይመስላል:: ነገር ግን ይህንን ጥቅስ ከቁጥር 21-28 ጋር እንዴት እንደሚዛመድና በዚያን ጊዜ የነበረው የአይሁድና የአህዛብ ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበረ ከተረዳን በቀላሉ ያለመጋጨቱን መረዳት እንችላለን በመጀመሪያ ደረጃ በቁጥር 21 ላይ ኢየሱስ ወደ ጢሮስና ሲዶና አገር እንደሄደ ይነግረናል እነዚህ ከተሞች በአህዛብ ግዛት ውስጥ ያሉ ናቸው:: ወደ እርሱ የመጣችውም ሴት ከአህዛብ ወገን ስትሆን ወደእርሱ ስትመጣ ኢየሱስ ጌታና መሲህ እንደሆነ አምና ነበር ይህም እንዲህ በማለት ነው የገለጠችው«ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ማረኝ» ይህንን አይነት እምነት ጌታየሱስ ከአብዛኛው አይሁድ አላገኘም ነበር:: እርሱ ግን አብዝቶ እንድትጮህና እምነትዋ በዙሪያዋ ላሉት ሰዎች እንዲገለጥ ስለፈለገ ለሴትየዋ ተቃራኒ መልስ ሰጣት እርሷ የዳዊት ልጅ/መሲሁ/ጌታና የአለም ሁሉ አዳኝ ነው ብላ ስትመጣ እርሱ ለእስራኤል ቤት ብቻ መጥቻለሁ በማለት ተስፋ አስቆራጭ ንግግር ተናገራት እርሷ ግን በመሲሁ ሁሉን አዳኝነት ላይ የጠነከረ እምነት ስለነበራት ከጥያቄ አልፋ ሰገደችለት (ቁ25) እርሱ ግን መልሶ በዘያን ጊዜ አይሁዶች ለአህዛብ የነበራቸውን አመለካከት ተናገራት ይህም የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም አለ:: (ቁ26) አይሁዶችን ልጆች አህዛብን ደግሞ ውሾች ማለቱ ነው::

ሴትየዋ ግን መሲሁ ሲመጣ መጀመሪያ ለእስራኤል ከዚያም ለአህዛብ አዳኝ እንደሆነ ስላመነች እንዲህ ስትል ተናገረች «አዎን ጌታ ሆይ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለች» በዚህን ጊዜ ጌታ እንድትናገር የፈለገው ሀሳብ ይህ ስለነበረ እምነትዋን በማድነቅ ልጅዋን ፈውሶላታል:: እርሱ ለአለም ሁሉ አዳኝ ባይሆን ኖሮ እምነትዋን አያደንቅም ልጅዋንም አይፈውስም ነበር:: ኢየሱስ የሴትየዋን እምነት እንዲገለጥ ስለፈለገ ከጥያቄዋ በተቃራኒ በመሄድ ተናግሮአታል:: ስለዚህ መጽሀፍ ቅዱስን ለመረዳት አውዱን በደንብ መመልከት ያስፈልጋል:: አንድ ጥቅስ ብቻውን ማብራራት አይቻልም:: ሊሰጥ የታሰበውንም መልዕክት አይሰጥም::

## ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች ትኩረት ሰጥተው ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልዕክት መረዳት ያስፈልጋል

**ለምሳሌ**

በ1ኛሳሙ28:6 «ሳዖልም እግዚአብሔርን ጠየቀ እግዚአብሔርም በህልም ወይንም በኡሪም ወይም በነብያት አልመለሰለትም» ሲል በ1ኛዜና 10:13-14 ደግሞ እንዲሁም «ሳኦል በእግዚአብሔር ላይ ስላደረገው ኃጢአት የእግዚአብሔርን ቃል ስላልጠባቀ ሞተ ደግሞም መናፍስት ጠሪ ስለጠየቀ እግዚአብሔርንም ስላልጠየቀ ስለዚህ ገደለው»ይላል:: ስለዚህ ሳኦል እግዚአብሔርን ጠይቋል ወይስ አልጠየቀም? የሳሙኤል መጽሐፍ ፀሐፊና የዜና መጽሐፍ ፀሐፊ ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት አንድ አይነት አይደለም ሁለቱም ፀሐፊዎች ታሪኩን የሚዘግቡበት አቅጣጫ የተለያየ ነው:: የሳሙኤል መጽሐፍ ፀሐፊ ሳኦል ያደረገውን ነገር ታሪኩን ይዘግባል ይህም ሳዖል የፍልስጤማውያን ሰራዊት ሲመጣበት ፈርቶ ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔርን ጠየቀ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሳይመልስለት ሲቀር እንዳያደርግ በህግ የተከለከለውን ነገር ማለትም ጠንቋይን መጠየቅ ሄዶ እንዴት እንደፈፀመ ይገልፃል ከዚያ ጠንቋዩን ከጠየቀ በኋላ እንደሞተ ዝርዝሩን ጽፏል::

ነገር ግን የዜና ፀሀፊ ሳኦል የሞተበት ምክንያት እግዚአብሔርን ከልብ አለመፈለጉና የእግዚአብሔርን ቃል አለመጠበቁ እንደሆነ ከታሪክ  ሳይሆን ከስነ መለኮት አንፃር የእግዚአብሔርን ፈቃድ መተላለፉን እያስታከከ ጽፎአል ስለዚህ በ1ኛ ሳሙኤል 28:6 ሳኦል እግዚአብሔር ጥያቄዬን ይመልስ እንደሆነ በሚል በአንደበቱ ጠይቋል ነገር ግን በ1ኛዜና 10:13-14 የዜና ፀሐፊ የሚለው ሳኦል እግዚአብሔርን ከልቡ አልፈለገም::

ሻአል /Shaal/ የሚል ቃል ሲጠቀም ይህም ማለት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል በእብራይስጥ ቋንቋ በ2ኛ ሳሙ 28:6 በሚል ልብ መጠየቅ ማለት ሲሆን በ1ኛዜና10:13-14 ባለው ክፍል ደራህ /Darash/ የሚል ቃል ተጠቅሟል:: ይህም ማለት በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን አለመፈለግ ወይንም አለመጠየቅ ማለት ነው:: ስለዚህ የመጽሀፍ ቅዱስ ፀሀፊዎች ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልዕክት መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው::

## ሐ. የፀሐፊዎቹ የቃላት አጠቃቀም ካለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ የሚጋጭ ሊመስለን ይችላል

**ለምሳሌ**

ዘፍ6:6 «እግዚአብሄር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተፀፀተ» ሲል በ1ኛ ሳሙ15:29 እግዚአብሔር አይፀፀትም» ይላል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ይፀፀታል ወይስ አይፀፀትም በመጀመሪያ መረዳት ያለብን ቃላት በተለያየ ቦታ ሲገቡ እንደየአውዳቸው የተለያየ ትርጉም ይሰጣሉ:: ተፀፀተ የሚለውም ቃል በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተለያየ ትርጉም ይሰጣል::በዘፍ6:6 «ተፀፀተ» የሚለው ቃል የሚገልፀው የሰዎች ልብ ከእግዚአብሔር ሐሳብ በመራቅ ኃጢአት በመስራታቸውና ከኃጢአታቸው ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ቅጣት በማየት እግዚአብሔር አዘነ የሚል ነው:: የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀመው ቃል «Grieved» የሚል ሲሆን አዘነ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሰዎች ጽድቅን ሲሰሩ እንደሚደሰት ሁሉ ኃጢአት ሲሰሩ ያዝናል:: ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ሐሳቡን ይቀይራል ወይንም ውሳኔውን ይለውጣል ማለት አይደለም:: በ1ኛ ሳሙ 15:10-11 እግዚአብሄር ሳኦልን ንጉስ በማድረጉ «ተፀፀተ» የሚለው አዘነ ማለት ነው የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስም «Grieved» የሚለው ቃል ተጠቅሞአል:: ነገር ግን በ1ኛሳሙ15:29 «እግዚአብሔር አይፀፀትም» የሚለው እግዚአብሔር ከውሳኔው አይመለስም ወይንም ሐሳቡን አይቀይርም ማለት ነው:: የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ «He does not change his mind» ነው የሚለው ቃላት በተለያየ ቦታ ሲገቡ የተለያየ መልዕክት ስለሚሰጡ በአውዳቸው መሠረት ካልተረጎምናቸው የሚጋጩ ሊመስለን ይችላል:: ብዙ ሰዎች የሚሳሳቱትም ከዚህ የተነሳ ነው::

## መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች እይታ /Perspective/ ካለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የሚጋጭ ሊመስለን ይችላል

**ለምሳሌ**

በሐዋ1:18 «ይህም ሰው በአመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ ይላል:: ነገር ግን በማቴ27:6-7» የካህናት አለቆችም ተማክረው የሸክላ ሰሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት» ደግሞም ስለ አሟሟቱ ሲናገር «ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ» ይላል ስለዚህ ይሁዳ የሞተው ታንቆ ወይስ በግንባሩ ተደፍቶ አንጀቱ ተዘርግፎ ? መሬት የገዙት የካህናት አለቆች ወይስ ይሁዳ ?ይሁዳ የሞተው ታንቆም በግንባሩ ተደፍቶ አንጀቱ ተዘርግፎም ነው:: መሬት የገዙት የካህናት አለቆችም ይሁዳም ናቸው:: ይህ እንዴት ይሆናል ካልን የይሁዳ አሟሟትና የመሬቱ ግዢ አጠቃላይ ታሪክ ማወቅ ይኖርብናል::

ታሪኩ እንዲህ ነው ይሁዳ ኢየሱስን በ30 ብር ከሸጠ በኋላ እንደተፈረደበት ሲያይ ተፀፅቶ ብሩን በቤተመቅደስ ጥሎ ሔኖም ወደሚባለው ሸለቆ በመሄድ በኮረብታ ላይ ታነቀ:: ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ገመዱ ስለተበጠሰ ወደምድር ወደቀ ሲወድቅ በግንባሩ ተደፍቶ ነው አንጀቱም ተዘረገፈ የካህናት አለቆችም ገንዘቡን ከመባ ጋር እንጨምረው ዘንድ አይገባም በማለት የሸክላ ሰሪውን መሬት ገዙበት:: ስለዚህ የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ፀሐፊ (ሉቃስ) እና የማቴዎስ ወንጌል ፀሀፊ (ማቲዎስ) የታሪኩን የተወሰነ ክፍል በመውሰድ ነው የፃፉት:: ሉቃስ የይሁዳን አሟሟት ፍፃሜውን ሲጽፍ ማቴዎስ ደግሞ ጅማሬውን ጽፈዋል እንዲሁም ስለመሬት ግዢ ሉቃስ የተመለከተው ገንዘብ የይሁዳ ስለሆነ ግዥውን ማንም ቢፈጽመው ይሁዳ ባለቤት ስለሆነ መሬት ገዛ ብሎ ጽፏል ነገር

ግን ማቴዎስ ውስን የፈፀሙት የካህናት አለቆች ስለሆኑ መሬት ገዙ ብሎ የመሬት ግዢ ውል መፈፀማቸውን ያሳየናል። ሁለቱ ፀሀፊዎች የአንዱን ክስተት የተለያዩ ገፅታዎች ጽፈዋል እንጂ የሌለ ታሪክ አይደለም። ይሁዳ ሲሞት ታንቆም በግንባሩ ተደፍቶ አንጀቱ ተዘርግፎ ነበር መሬት የገዙት የካህናት አለቆችም ይሁዳም ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሀፊዎች አንድን ታሪክ እንዴት እንደሚመለከቱት ካልተረዳን የማይጋጩትን ጥቅሶች የሚጋጩ ሊመስሉን ይችላሉ።

## ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ስዕላዊ አገላለጦች እንዴት እንደሚተረጎሙ ካልተረዳን ልንቸገር እንችላለን

**ለምሳሌ**

በኢሣ54:5 «ፈጣሪሽ ባልሽ ነው» ስለሚል እንዴት እግዚአብሔር ሚስት ይኖረዋል? የሚል ጥያቄ ይነሳል። በመሰረቱ እግዚአብሔር ሚስት አልነበረውም የለውምም አይኖረውምም። «ፈጣሪሽ ባልሽ ነው» የተባለችው እስራኤል ናት። እስራኤል ደግሞ ህዝብ እንጂ ሴት አይደለችም በዚህ ስፍራ ነብዩ ኢሣይያስ ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ባል ለሚስቱ እንደሚጠነቀቅላት፣ እንደሚወዳት፣ እንደሚንከባከባትና እንደሚያስብላት እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ እንደባል በመሆን ባል ለሚስቱ የሚያደርገውን ሁሉ ያደርግላቸዋል የሚል ነው። የእግዚአብሔርና የእስራኤል ግንኙነት መንፈሳዊ ስለሆነ ስዕላዊ አገላለጥ ተጠቅሟል።

በኢሳ7:20 «በዚያን ቀን ከወንዝ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሶር ንጉስ የራሱን የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል»ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሁሉ ያለው ሲሆን እንዴት ምላጭ ይከራያል?» በመጀመሪያ ይህንን አረፍተ ነገር ከቁጥር 1-25 ካለው ጋር የተያያዘ ነው በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ «ተከራየ፣ እግር፣ ፀጉር፣ ጺም፣ ምላጭ እና ይላጨዋል» የሚሉት ቃላት ስዕላዊ አገላለጦች ናቸው። ታሪኩን ስንመለከት ነብዩ ኢሳያስና ልጁም ያሱብ ወደ ይሁዳ ንጉስ አካዝ ሄደው ከአሶርና ከእስራኤል ነገስታት በተላከበት ማስፈራሪያ እንዳይናወጥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ምልክት እንዲጠይቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከው ነበር።አካዝ ግን ምልክትን አልጠይቅም በማለት እመፀ። ስለዚህ በአመፅህ የአሶርን ንጉስ አስነስቼ አንተንና ህዝብህን አዋርዳለሁ የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ነብዩ ኢሳይያስ ስዕላዊ ንግግር ተጠቅሟል። በዚህም መሰረት ምላጭ የአሶር ንጉስ ነው። በእስራኤል ባህል መላጨት የውድቀት የጥፋት ምልክት ነው ተከራየ የሚለው ደግሞ በእግዚአብሔር የተመረጠና እርሱን የሚያመልከውን ህዝብ ለመቅጣት ያልተመረጠና ሌላ አምላክ የሚያመልከውን ህዝብ ተጠቅሞ የይሁዳን ህዝብ እቀጣለሁ ማለቱ እንጂ እግዚአብሔር የምላጭ ችግረኛ ነው ማለት አይደለም።

## ረ. መጽሀፍ ቅዱስ ሲፃፍ የነበረው የታሪክ፣የባህል፣የሰዓት አቆጣጠርና የአፃፃፍ ዘዴዎች መረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል እንድንረዳ ያደርገናል

**ለምሳሌ**

በማቴ12:40 ጌታ ኢየሱስ ሲናገር «ዮናስ በአሳ አንባሪ ሆድ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ይኖራል» ብሏል። ነገር ግን ኢየሱስ በመቃብር የቆየው ከአርብ ማምሻ እስከ እሁድ ማለዳ ነው። እነዚህ ቀናቶች ሲቆጠሩ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት አይሆኑም ስለዚህ ኢየሱስ ይዋሻልን?

የዚህ ጥያቄ መልስ አጭርና ግልፅ ነው። ይህም ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ሲያገለግል አይሁዶች ጊዜያትን የሚቆጥሩት እንዴት ነበር ብለን ራሳችንን መጠየቅና በዚያ ጊዜ የነበረውን ታሪክ ማጥናት አለብን። የአይሁድን ታሪክ ስንመለከት አይሁዶች አንድን ክስተት በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ከተፈፀመ ቀናቱን ቆጥረው ቀንና ሌሊት በማለት

ይዘግባሉ፡፡ በማቴ:12:40 ላይም ኢየሱስ በምድር ልብ የቆየው ለሦስት ቀናት ነው (አርብ፣ቅዳሜ፣እሁድ)፡፡ ስለዚህ ሶስቱ ቀናት ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ብለው ይቆጥሩታል፡፡ በእነርሱ አቆጣጠር የቀናት ብዛት እንጂ ድርጊቱ በስንት ሰዓት ጀምሮ በስንት ሰዓት እንዳበቃ ትኩረት አይሰጡትም፡፡ ዮናስም አሳ አንባሪው ስንት ሰዓት ላይ እንደዋጠው በስንት ሰዓት እንደተፋው አልተፃፈም፡፡ ነገር ግን በአሳ አንባሪ ሆድ ሶስት ቀናት ስለቆየ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ተባሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ያለብን በእኛ የሰዓትና የቀናት አቆጣጠር ሳይሆን በአይሁዶች አቆጣጠር ሊሆን ይገባል፡፡ ኢየሱስም አልዋሸም መጽሐፍ ቅዱስም እርስ በርሱ አይጋጭም፡፡

## ሰ. የሳይንስና የመፅሐፍ ቅዱስን ዝምድና አለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋር የሚጋጭ ሊመስለን ይችላል

### ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ መሰረታዊ ልዩነት አላቸው

ሳይንስ የሚዘግበው ቁሳዊውን አለም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ቁሳዊም መንፈሳዊንም አለም ነው፡፡ ሳይንስ አንድን ክስተት እንዴት ተፈፀመ? የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ምን ተፈፀመ ? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፡፡ ሁለቱም የመርህ /Principle and Discipline/ ልዩነት ስላላቸው በሳይንስ እይታ መጽሐፍ ቅዱስን መመዘን አይቻልም፡፡ በሌላ አንፃር መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተፃፈው የሳይንስን ምንነት ለማይረዱ ሰዎች ሲሆን ሳይንሳዊ ቃላትን ተጠቅሞ አይደለም፡፡

እግዚአብሔር ስለ ሳይንስ ስለማያውቅ አይደለም ነገር ግን መልዕክቱ የተፃፈላቸው ሰዎች የሳይንስ ግንዛቤ ስላልነበራቸው በራሳቸው አውድ ወይንም በጋራ መግባቢያ ቋንቋ ተጽፎላቸዋል፡፡ በኢያ10:12-14 «ፀሐይ በገባኦን ላይ ቆማለች» ሲል ፀሐይ ትዞራለች ማለቱ ሳይሆን በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች የሚረዱት የመሬት በራሷ ዛቢያ ላይ መዞርዋን ሳይሆን ፀሐይ ከምስራቅ ወጥታ ወደምዕራብ መቀጠልዋን ነው፡፡ ስለዚህ እነዚያ ሰዎች እግዚአብሔር የተፈጥሮን ስርዓት በመቆጣጠር ቆዱሳንን እንደረዳ የሚረዱት ፀሐይ ቆማለች ሲባሉ ነው፡፡ሳይንስ በራሱ ብዙ ችግሮች አሉበት፡፡ አንድ ሳይንቲስት ያገኘውን ግኝት ለዘላለም እውነት ሆኖ አይኖርም አንዳንዴ በአንድ ዘመን ሰፊ ተቀባይነት የነበረው ትምህርት በሌላ ጊዜ ትክክል እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ አንድ ሳይንቲስት ያስተማረውን ሌላው ያፈርሰዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሳይንስ በራሱ ፍፁምና ምሉዕ እንዳልሆነ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሳይንሳዊ ግኝቶች ሁሉ ሐሰት ናቸው ማለት አይደለም ሌላው ሳይንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ ተዓምራትና ቲዮሪ (Theories) በተመለከተ ነው፡፡

ተዓምራት እግዚአብሔር በሰዎች ህይወት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ታላቅነቱና ክብሩን የሚገልጥበት መንገድ ነው፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ ከተፈጥሮ ህግ ውጪ የሆኑ ተግባሮች ይፈፀማሉ፡፡ ሳይንስ የሚሰራው በተፈጥሮ ህግ ውስጥ ስለሆነ ከዚህ ውጭ የሆነውን ነገር ሳይንቲስቶች መቀበል ይቸግራቸዋል እግዚአብሔር ፈጣሪና የበላይ ተቆጣጣሪ እንደሆነ ቢያምኑ ሳይንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር አይጋጭባቸውም ነበር፡፡ ስለዚህ ችግሩ ያለው ሳይንቲስቶች ዘንድ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ጋ አይደለም. ቲዎሪ /Theories/ በተመለከተ ሳይንቲስቶቹ ሳይፈጠሩና ታሪክ የማያውቀውን ክስተት እንዲህ ሊሆን ይችላል ብለው የሚሰጡት ግምታዊ ትንታኔ ስለሆነ ከመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ቢጋጭ ችግሩ ያለው ሳይንሱ ዘንድ እንጂ እግዚአብሄር ወይንም መጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይደለም፡፡ የወደፊት መላምቶችም ቢሆን ሳይንስ በእርግጠኝነት መናገር ስለማይችል በሳይንስ መነጽር የእግዚአብሔርን ቃል አንክንንም፡፡ ይልቁንስ ሁሉን አዋቂና ለዘላለም በሁሉ ስፍራ የሚገኘውን ፈጣሪ አምላክ ቃል አምነን ልንከተል ይገባናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትናቸውን ሰባት ነጥቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት መጽሀፍ ቅዱስን ልናጠና ይገባናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ምንም ችግር የሌለበትን የእግዚአብሔርን ቃል እርሱ በርሱ የሚጋጭ እየመሰለን ወደስህተት እንወድቃለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ

ተበላሽቷል እርስ በርሱም ይጋጫል ብላችሁ የምታምኑ ከዚህ በፊት ከተሰየየ አቅጣጫ የሰማችኋቸውን ተቃውሞዎች በንፁህ ህሊና ሚዛናዊ በሆነ መንፈስ እንድትመረምሩአቸው እጠይቃችኋለሁ። ነገ ምን እንደምንሆን ስለማናውቅ ዛሬ ፈጥነን እውነተኛውን መንገድ መፈለግ ይኖርብናል። ፈጣሪ አምላክ ራሱ ይርዳን።

## የክርስቶስን አምላክነት ተቃውሞ

ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም ይላሉ። የክርስቲያኖች ፈጠራ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምላክነቱ ምንም ፍንጭ አይሰጥም። አምላክ ከሆነስ እንዴት ይበላል? ይጠጣል? ይተኛል? ይሞታል? እና ሌሎችም ጥያቄዎች ይነሳሉ። እንዲያውም አንዳንዶች የሚሉት ክርስቲያኖች ኢየሱስ ተዓምራትን ሲያደርግ አምላካችን ሲሆን ይችላል ብለው ከሰው ወደ አምላክነት አሳድገውት ነው።

**መልስ**

ክርስቲያኖች ክርስቶስ ተዓምራት ስለሰራ አምላክ ነው አላሉትም። ራሱ ግን አምላክ ስለሆነና ስለሚገባው ነው። ብዙ ሰዎች የክርስቶስ አምላክነትን መቀበል የሚቸግራቸው በዚህ ምድር የነበረውን ኑሮ ብቻ ተመልክተው ከዚያ በፊትና በኋላ ማን እንደሆነና ምን እንደሚሰራ ስለማይረዱ ነው።

ስለክርስቶስ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ከፍጥረት ጅማሬ በፊት ማን ነበር? እርሱ አለም ሲፈጠር ፈጣሪ ወይስ ፍጡር ነው? ስጋ መልበስ ለምን አስፈለገው? አምላክ ከሆነስ በሰው ምሳሌ ተገኝቶ መኖሩ ጠቀሜታው ምንድነው? አሁንስ ማን ነው ምንስ ይሰራል? ወደፊትስ ሌሎች? እና ተዛማጅ ጥያቄዎችን ራሳችን መጠየቅ አለብን። ለነዚህም ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስ መልስ አለው። የእግዚአብሔር ቃል በዮሐ1:1 «በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ: ቃልም እግዚአብሔር ነበር» ይላል። በዚህ ክፍል «በመጀመሪያ» የሚለው ቃል በፍጥረት ጅማሬ ማለት ነው። ይህም ዘፍ1:1 ካለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ፍጥረት ሲጀምር ቃል ነበር። ይህንንም ቃል ከእግዚአብሔር(አብ) ጋር ነበር። ቃሉ ራሱ እግዚአብሔር ነበር ነው የሚለን። ይህም ቃል ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ እንደሆነ በቁጥር 3 ላይ እንዲህ ይላል« ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ አልሆነም»ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ተፈጥሯል ያለክርስቶስ (ቃል) የተፈጠረ የለም ይህም በሱራ-3:45 ክርስቶስ የአላህ ቃል ነው ከሚለው ሐሳብ ጋር ይስማማል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በቆላስያስ 1:15 ባለው ክፍል ክርስቶስ የሰማይና የምድር ፈጣሪ እንደሆነ እንዲህ ይላል«እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፣ የሚታዩትንና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይንም ጌትነት ወይንም አለቅነት ወይንም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሟል።» በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል የሚለን በሙሉ ክብሩ ሊታይ የማይችለው አምላክ በሰው ምሳሌ(በክርስቶስ) ሆኖ ተገለጠ እርሱም የማይታየው አምላክ የባህርይው ምሳሌና የክብሩ ነፀብራቅ ነው። (ዕብ1:3) ይህንን አምላክ የሚታየው ቁሳዊ ዓለምና የማይታየው መንፈሳዊ ዓለም ፈጥሮአል። እርሱም ከፍጥረት በፊት «በኩር» ማለት የተለያየ ትርጉም አለው። በዚህ አውድ ግን የፍጥረት ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ ገዢ ከፍጥረት በፊት የነበረና የሁሉ ፈጣሪ ማለት ነው።

እርሱ ከሁሉ በፊት ነው ይህም ማለት እርሱ ዘላለማዊ ነው ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ክርስቶስ ደግሞ እግዚአብሔር ስለሆነ ከሁሉ በፊት ነው። እርሱ ዘላለማዊ እንደሆነ ለአይሁድ እንዲህ ብሎ ነበር የተናገራቸው «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው» «አለሁ» የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ብቻ የተጠቀመበት ቃል ሲሆን እርሱ ዘላለማዊና ጅማሬ የሌለው አምላክ እንደሆነ ያሳያል። ኢየሱስም ይህን ቃል ሲናገር አይሁድ እግዚአብሔርን ተሳድቧል ብለው ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ ይላል። ኢየሱስ «ነበርሁ» የሚል ቃል ቢጠቀም ኖሮ

ስለዚህ ከእግዚአብሔር በቀር ዘላለማዊ ማን ነው? ኢየሱስ ሰው ብቻ ከሆነ እንዴት ዘላለማዊ ይሆናል?

## 2. እርሱ እውነተኛው አምላክ (God) ተብሎ ተጠርቷል

ዮሐ1:1 «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ፊል2:6 «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ» ኢሳ9:6 «ኃያል አምላክ (Mighty God) » ዮሐ20:28 «ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት» ዕብ1:8 ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከዘላለም ድረስ ይኖራል» ሮሜ9:5 «እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን 2ጴጥ1:1 «በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» 1ኛዮሐ5:20 «እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ህይወት ነው።» መጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪ አምላክ እያለው እየገለጠው እንዴት ይህንን እውነት ልንክድ እንችላለን ?

## 3. እርሱ ከአብ ጋር እኩል ነው

በመለኮትም አንድ ነው።ዮሐ10:30-38 «እኔና አብ አንድ ነን » ዮሐ14:8-11 «እኔን ያየ አብን አይቷል እንዴትስ አንተ፡- አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» በአብና በኢየሱስ መሐከል ያለው አንድነት መለኮታዊ አንድነት ነው ነገር ግን በሰውና በእግዚአብሔር መሐከል ያለው አንድነት መንፈሳዊ ህብረት ነው፡(ዮሐ17:11)

## 4. እርሱ በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው

ዮሐ1:3 «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ቆላ1:15-18» የሚታዩትንና የማይታዩትንም ዙፋናት ቢሆን ወይንም ጌትነት ወይንም አለቅነት ወይንም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና።»

## 5. ኃጢአትን ያስተሰርያል (ይቅር ይላል)

ማር2:5-6 «ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ ኃጥአትህ ተሰርይልሃለች አለው»

## 6. እርሱ በሰው ዘር ሁሉ ላይ ፈራጅ ነው

ዮሐ5:22-23 «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድንም ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም» ማቴ25:31-46 ጌታ ኃጢአተኞችንና ፃድቃን በግራና በቀኝ ያስቀምጣቸዋል ኃጥአን ወደዘላለም ፍርድ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ደስታ እንዲሄዱ በሁሉም ላይ ይፈርዳል 2ቆሮ5:10« ሁላችንም በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል»

## 7. ክርስቶስ አምልኮና ስግደት የተገባው ነው ደግሞም በምድራዊ አገልግሎቱ ተቀብሎአል

ዕብ1:6 «የእግዚአብሔር መላዕክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ።» ማቴ15:25 «እርስዋ ግን መጥታ ጌታ ሆይ እርዳኝ እያለች ሰገደችለት» ዮሐ9:37 «እርሱም ጌታ ሆይ አምናለሁ አለ ሰገደለትም» ነገር ግን ሰዎችም ቢሆኑ መላዕክት የአምልኮ ስግደትን ተቃውመዋል። በሐዋ10:25-26 ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስ ሲሰግድለት ከልክሎታል። በራዕ19:10 እና ራዕ22:8-9 ሐዋርያው ዮሐንስ ለመልዓኩ ሲሰግድ ሲደፋ እንደ እርሱ ባሪያ እንደሆነ በመንገር ከልክሎታል ስግደት የሚሰጠውም ለአምላክ ብቻ ነው።

## 8. እርሱ የሰንበት ጌታ ነው

ማር 2:27-28 «የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው አላቸው።»

## 9. መላዕክት የእርሱና በእርሱ ትዕዛዝ የሚላኩ ናቸው

ማቴ.13:41-43 «የሰው ልጅ መልዕክቱን ይልካል»

## 10. የመለኮት ሙላት በእርሱ ተገልጦ ይኖራል ቆላ2:9

## 11. ክርስቶስ ከሦስቱ የስላሴ አካላት አንዱ ተደርጎ ተጽፏል

## 12. እርሱ ሁሉንም ያውቃል

ዮሐ2:24-25 «ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ስለሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና»

## 13. እርሱ በሁሉ ስፍራ ይገኛል

ዩሐ1:48-49 «ኢየሱስም መልሶ :-ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ አለው»

## 14. እርሱ ህይወትና የዘላለም ህይወት ምንጭ ነው ዮሐ5:26፣ዬሐ1:4፣14:6

## 15. የክርስቶስ ስሞች አምላክነቱን የሚገልጡ ናቸው

ኢየሱስ ማለት ጌታ አዳኛችን ማለት ነው ማቴ1:21
አማኑኤል ማለት ጌታ ከእኛ ጋር ማለት ነው ማቴ.1:23
ክርስቶስ ማለት የተቀባ ወይንም መሲህ ማለት ነው ማቴ.11:1-6፣16:16
ያህዌህ ይህም እግዚአብሔር ዘፀ 3:14 ላይ «ያለና የሚኖር» የሚለው ስም ይወክላል::ኢየሱስ በዮሐ8:58 «እኔ አለሁ» በማለት እንድ አይነት ስም ተጠቅሟል በእንግሊዘኛው «I am» የሚለው ሀሳብ ለራሱ ተጠቅሟል:: ይህ አባባል ከእግዚአብሔር ውጪ ለማንም አይሠራም::

**ጌታ** (Lord):- ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ከሆነው «አዶናይ» ጋር አንድ አይነት ነው::

**የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ** (አንድያ ልጅ) የሚያመለክተው ከአብ ጋር ያለውን ዘላለማዊ አንድነትን ነው:: በዮሐ5:17-18 ኢየሱስ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏል ብለው አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ:: ኢየሱስ ይህንን ስም ስለተጠቀመ አይሁድ እግዚአብሔርን ተሳድቧል ብለው የሞት ፍርድ ፈርደውበታል:: ማር14:61-64፣ማቴ.26:62-68 የሰው ልጅ የሚለው ስም አምላክ ቢሆንም ፍፁም ሰው እንደሆነ እንደሁም በነብዩ ዳንኤል የተነገረው ንጉስ የሚለውን ሐሳብ ገላጭ ነው::ዳን7:13-14 ማቴ.19:28

**የዳዊት ልጅ**:- ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን (Covenant) ላይ ለዘላለም የሚነግስ እንደሆነ ነው::2ሳሙ7:11-16፣ሉቃ1:32-33፣ማቴ.21:9-11 በአጠቃላይ የኢየሱስ አምላክነት መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በላይ ጥልቅ የሆነ ትምህርት ይሰጣል:: ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን ቀርቶ ሰዎች የፈጠሩት ቅጥፈት አይደለም:: ማንም ይህንን እውነት ሲረዳ ነው ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያውቀው ጌታ ኢየሱስን በትክክል የሚያውቅ አብንና መንፈስ ቅዱስን ያውቃል::

**በመጽሐፍ ቅዱስ** በተለይም በአዲስ ኪዳን የተወሰኑ ጥቅሶች ከክርስቶስ አምላክነት ጋር ይቃረናሉ ተብለው ይነሳሉ:: እነዚህ ጥቅሶች መጠናት ያለባቸው ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረው ቆይታም ሆነ ከዚያ በኋላ ፍፁም ሰውና ፍፁም አምላክ እንደሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው:: እርሱ የተናገራቸው ንግግሮች እንደ ሰው እንዲሁም እንደ አምላክ ነው:: በተጨማሪም አንዳንዶቹ በምድር ላይ ከነበረው አገልግሎት ጋርም የተያያዙ ናቸው::አንዳንዶቹ ደግሞ ከፈሪሳውያን ወይንም ከአይሁዶች ጥያቄዎች ጋር ተያያዥነት ስላላቸው አውዶቹን በጥንቃቄ ማጥናት አስፈላጊ ነው::

## ቁርዓን ስለቀደሙት መለኮታዊ መጽሐፍት (ስለመጽሐፍ ቅዱስ) ምን ይላል ?

በሱረቱል በቀራህ (2)136 «በአላህ ወደኛ በተወረደው (ቁርዓን) ወደኢብራሂም ወደ እስማኤል ወደ ይስሐቅ ወደ ያዕቆብ ወደ ነገዶች በተወረደው በዚያም በሙሳና በኢሣ በተሰጡት በዚያም ነብያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከእነርሱም በአንዱም መካከል የምንለይ ሳይሆን አመንን እኛም ለእርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።»

በሱረቱል አንከቡት (29)46 የመጽሐፍ ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር አትከራከሯቸው ከነሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር በሱም በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው አመንን አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው እኛ ለእርሱ ታዛዦች ነን።

በሱረቱል ኒሳህ4(136) «እናንተ ያመናችሁ ሆይ በአላህና በመልዕክተኛው በዚያም በመልዕክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽ ሐፍ እመኑ።»

በሱረቱል ኢምራን (3) «84 በአላህ አመንን በእኛ ላይ በተወረደው (በቁርዓን) በኢብራሂምና

በእስማኤል በይስሀቅ በያዕቆብም በነገዶች ላይ በተወረደው ለሙሳና ለኢሣ ለነብያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው (አመንን) ከነርሱ መካከል አንዱንም አንለይም እኛ ለርሱ ታዛዦች ነን በል።»

ሱረቱል በቀራ (2)85 «..በአላህ በመልዕክቱም በመጽሐፍቱም በመልዕክተኞቹም ከመልዕክተኞቹም በአንዱም መካከል አንለይም።»

ከዚህ በተጨማሪ ዘርዘር ባለ መልኩ ደግሞ ከቁርዓን በፊት ከአላህ ለሰዎች የተሰጠ መለኮታዊ መጽሐፍ በተመለከተ

- ሀ. ለነቢ ኢብረሂም ከአላህ የተሰጡ ሱረቱል አዕላ(87)19 «በኢብረሂም በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ»
- ለ. ለነብያት ሁሉ ከአላህ የተሰጡ ሱረቱል ኢምራን (3)84 ለነብያትም ሁሉ»
- ሐ. ለነቢ ሙሣ ከአላህ የተሰጡ ሱረቱል በቀራ(2)53 «ሙሳንና መጽሐፍትንና»
- መ. ለነቢ ዳውድ ከአላህ የተሰጠ ሱረቱል ኢስራዕ (17) 55 «ዳውድንም ዘቡርን ሰጥተነዋል»
- ሠ. ለነቢ ኢሣ ከአላህ የተሰጡ ሱረቱል ማኢዳ(5)46 የመርየም ልጅ ዒሣ ከተውራት በስተፊት ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን ...

አላህ ለሰው ልጆች በነብያት በኩል ያስተላለፈ መሆኑን ይገልፃሉ። ታዲያ እነዚህ መጽሐፍ ቀደም ብለው ካሉ ለምን ቁርዓን መጣ? ቁርዓን ራሱ የሚሠጠውን ምስክርነት ስንመለከተው

- ሀ. በሱረቱል ኢምራን (3)2-3 - ከርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን
- ለ. በሱረቱል የኑስ (10)37 – ከርሱ በፊት ያለውን የሚያረጋግጥ
- ሐ. በሱረቱል ፈጢር (35)31 - ከበፊቱ ያለውን የሚያረጋግጥ
- መ. በሱረቱል የሱፍ(12)111 ያንን በስተፊቱ ያለውን መጽሀፍ አረጋጋጭ በተጨማሪም በሱረቱል አንዓም (6)92 በቀራ (2)89፣91፣101፣ በሱረቱል አህቃፍ (46)72 በሱረቱል
  ማኢዳህ (5)43 ኢምራን(3)3 ላይ ቁርዓን የበፊቱን መጽሐፍ አረጋጋጭ ነው ይላሉ።

መ. በሱረቱል ማኢዳ (5)121 ተገቢውን ንባብ ያነቡታል
ሠ. በሱረቱል ዓንከቡት (5)66 ትክክለኛ ህዝቦች አሉ
ረ. በሱረቱል ዓንከቡት (29)46 አምላካችሁና አምላካችን አንድ ነው
ሰ. በሱረቱል ኢምራን (3)113-114 የማይሰግድ (የማያመልኩ) አንቀጽን የሚያነቡ አሉ?
ሸ. በሱረቱል ኢምራን (3)55 በኢሣ ተከታይ ክርስቲያኖች ከሌሎች ከማይከተሉት (ክርስቲያን ካልሆኑት) የበለጡ የላቁ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ በሱረቱል ማኢዳ (5)44:47 ላይ በተውራት ይፈርዳሉ በኢንጅል ይፍረዱ በማለት በነብዩ መሐመድ ዘመን በኢንጅል የሚፈርዱም ሆነ በኢንጂል እንዲፈረዱ የታዘዙ መኖራቸው በራሱ መጽሐፎቹ ያልተበረዙና ያልተለወጡ መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ የምንመለከተው ነገር ከአይሁዶችም ሆነ ከክርስቲያኖች መካከል ትክክለኛ የሆኑና የተሣሣቱ መኖራቸውን ሲሆን እኛ የመጽሐፉ ባለቤቶች (አህለል ኪታብ) ለተሳሳቱ ጠበቃ መሆን አንፈልግም። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና በክርስቶስና በስላሴ አስተምህሮ ላይ ከፍተኛ የዶክትሪን ልዩነት በመፍጠር በርካታ የክርስትና ልዩነት በመፍጠር በርካታ የክርስትና ክፍል ተፈጥሮ እንደነበር እናምናለን። በሌላ አንጻር ዳግም አልመሰህ ዒሣ በምድር ላይ በሚያገለግለበት ዘመን አይሁዶችን መለኮታዊ መጽሐፍ መለወጣቸው ሣይሆን ስለወጋቸሁ ብላችሁ የአላህን ሕግ ትሽራላችሁ ብሎ የሰዎቹን መለወጥ እንጂ የአላህን ቃል አለመለወጥ ተናግሯል። (ማር7:13 ማቴ22:29) ስለዚህ የተለወጡት ሰዎች እንጂ የአላህ ቃል አይደለም።

በአንጻሩ ዳግም ትክክለኛ የሆኑ ቀጥተኛ ያሆኑ ቀጥተኛ የቀደሙት ቀጥተኛው መለኮታዊ መጽሐፍት የሚከተሉ ከላይ ያየነውን የአህላል ኪታብ (የመጽሐፉ ባለቤቶች) እምነት ወራሾች የሆኑና፣ የእነዚህን ሰዎች እምነት የሚከተሉ ደግሞ አሁንም መኖራቸው እናበስራለን እኛም ወራሾች መኖናችንን ስንገልጽ አላህ በየዘመኑ የእሱ ተከታዮች እንዳሉት ግልጽ እንዲሆን እንፈልጋለን።

የተሣሣቱትን የመጽሐፍ ባለቤቶችን የማረምና የማስተካከል ሥራ መልካም ሆኖ ሳለ ግን ከዚህ ቀጥሎ መሆን የነበረበት ወዳልተሣሣቱት የመጽሐፉ ሰዎች እምነት መምራት ደግሞ ዋናና አስፈላጊ ጉዳይ ነበር። ሆኖም ግን የተከናወነው ይህ ሳይሆን በተቃራኒ ነው።እስኪ ጉዳዩን ለማጠናከር ሌላ ጥያቄ ጠይቀን እንጨርስ። ለመሆኑ የቀደሙ መለኮታዊ መጽሐፍት (መጽሐፍ ቅዱስ) መቼ ተለወጠ?

## 1. ከነብዩ መሐመድ በፊት ነውን?

## በፊት ቢሆን ኖሮ

ሀ. ወደአንተ ካወረድነው በመጠርጠር ውስጥ ብትሆን እነዚህ ከአንተ በፊት መጽሐፍት የሚያነቡትን ጠይቁ ሱረቱል የኑስ (10)94
ለ. የማታውቁም ብትሆኑ የመጽሐፉ ባለቤቶችን ጠይቁ ሱረቱል አንብያዕ (21)7
ሐ. የማታውቁም ብትሆኑ የዕውቀቱ ባለቤቶችን ጠይቁ ሱረቱል ነህል (16)43
መ. በተውራት ኢንጅል ይፍረዱ። ሱረቱል ማአዲ (5)44፣47
የሚሉት ክፍሎች የሚነግሩን ከነብዩ መሐመድ በፊት አለመሆኑን ሲሆን እነዚህም ከነብዩ መሀመድ በፊት አለመበረዛቸውን ይመስክራል።

## 2. ከነብዩ መሐመድ በኋላ ኖሮ ሌላ ነብይ ተነስቶ በነብዩ ዘመን ስህተቱ አልታወቀም ነበር

አሁን ስህተት ተደርሶበታል። ስለዚህ የቀደመውን መጽሐፍ የሚያረጋግጥ (ቁርዓን) ቀርቶ ሌላ የሚተካ መጽሐፍ ተሰጥቶኛል ብሎ ያነሳ ነበር።ይህንን እኛ እስከምናውቀው ድረስ የተናገረ ማንም የለም። በመሆኑ ከነብዩ በፊትም ሆነ ከነብዩ በኋላ ተለውጧል ተበርዟል የሚሉት ሃሳቦች የሚያስኬድ መሆናቸውን ሲሆን በጣም ግልፅ ለማድረግ ደግሞ ራሱ ቁርዓን

ሀ. በሱረቱል አንአም (6)115
ለ. በሱረቱል የኑስ (10)64 ላይ የአላህን ቃል ለዋጭ የለም ይላል::

አላህ ቁርዓንን ጠብቋል ካልን የእርሱን መጽሐፍ ለመጠበቅ ምንም የሚያግደው ነገር የለም:: ደግሞም መለኮታዊ መጽሐፍቶች ሁሉ ምንጫቸው ሉሁል መኃፍዝ (ሱረቱል) በመሆን በምድር ላይ ያለው ተበረዘ ማለት ከሠማይም ያለው ተበረዘ ማለት አይሆንም ወይ ? በሱረቱል ዙህረፍ (43)4፣ በሱረቱል አንቢያዕ (21)105 እንዲሁም በሱረቱል ረዕድ (13)39 ላይ በሱረቱል ሀጅ (22)52 ቃሉን መለወጥ የሚችለው አላህ ብቻ መሆኑን ይናገራል:: ስለዚህ አላህ ቁርዓንን ጠብቋል ካልን የቀደሙትንና መጽሐፍ የማይጠብቅበት ምክንያት የለውም:: የአላህን ቃል ሕግ ማንም አይለውጠውም ኢሣ አልመሲህ ከሕግ አንዲት እንኳን አታልፍም ሠማይ ግን ያልፋል ብሏል እንደውም በሱረቱል ሀጅ (22)52 ላይ ሰይጣናዊ መንፈስ በአንድ ወቅት ያሳሳተው ክፍል እንዳለ ያሳያል::

ቅዱስ ቁርዓን አማርኛ እትም በ1961 ዓ.ም ከታተመው መቅድም ከሚለው ገጽ 10 ሁለተኛ አንቀጽ ላይ የሚከተለውን እንነባለን:: ዳግመኛ ኸሊፍ ዑስማን በ2ኛው ዓመት ስደት ባነሳው ግጭት ስለተገኘበት በአራት የቁርዓን ሊቃውንት በተከናወነ ጉባዔ የቃላቱን አጻጻፍ ያለነጥብ ለምንባብ ተስማሚ አድርገው በመጀመሪያ አወራረድ መሠረት የሱራዎችንም ተራ ጠብቀው ሰበሰቡት:: ኸሊፋውም ለአምስት ኮፒዎች አጽፎ አንዱን ለራሱ አስቀርቶ አራቱን ለመካና ለደማስቆ ለበስራና ለኩፍ ከተሞች ልኮ ማንኛውም ሰው ከነዚህ በታች እንዲገለበጥ አድርጎ የቀረውን ስለ አቃጠለው ቁርዓን አንድነቱን ጠብቆ ይኖራል እስካሁን ምንም መለዋወጥ አልደረሰበትም::

ገና ቁርዓን ተሰብስቦ ከተጻፈ 13 ዓመት ሳይሞላው ከአንድ ዓረብኛ ውስጥ ባሉ የንግግር ዘይቤዎች ተጽፎ ሲሰራጭ ግጭት ደርሶበት የተወሰደው መፍትሄ ደግሞ የተጋጩትን አቃጥሎ እንደገና ሌላ በማዘጋጀት ማሰራጨት ነው:: ታዲያ በ13 ዓመት ዕድሜው ቁርዓን ግጭት ደርሶበት ከታረመ የመጽሐፍ ቅዱስ እድሜ ቢያንስ ከ3000-3400 ዓመት ዕድሜ ያለው ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ሲተረጎምና ሲገለበጥ ከሰው ድካም የተነሳ መጠነኛ ልዩነቶች ቢፈጠሩ የሚያስገርም ካለመሆኑ በላይ በመሠረታዊ መልዕክት ማስተላለፍ ላይ ያመጣው ተጽዕኖ ባለመኖሩ የእግዚአብሔር መንፈስ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ መልዕክት ማስተላለፉን ስለቀጠለ ማቃጠልን እንደ አማራጭ ሳንወስድ በግልጽ ተቀምጦ የሰዎችን ሕይወት እየለወጠ ያለ እርሱ ነው::

እኛስ የመጽሐፉ ባለቤቶች እንደዚህ አናደርግም:: ምንም እንኳ የመጀመሪያ የአላህ ቃል የተቀበሉበትና የተጻፉት የብሉይ ኪዳን በእብራይስጥ በአርማይክ የአዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቢሆንም እነዚህ ቋንቋዎች ብቻ የፈጣሪ ቋንቋዎች ናቸው ብለን አናምንም:: ሁሉም ቋንቋ የአላህን ቃል ማስተላለፍ እንደሚችል ስለምናምን በሁሉም ቋንቋ ሲተረጎም ሲተላለፍ በትርጉም ጊዜ ከሰዎች ድካም የተነሳ የቁጥርና የመሳሰሉ አለመጣጣም ቢፈጠሩ ከጥንቱ መጽሐፎች ውስጥ እነዚያ ስህተቶች ይኖራሉ ብለን ስለምናምን ከሚቃጠል የተፈጠረው ስህተት በአላህ ሣይሆን በሰዎች ውስንነት መሆኑን እየነገርን በግልጽ አስቀምጧል::

## ዋቢ መጽሐፍት (Bibliography)

Ali, Abdella Yusuf, The Holy quran- An English translation of the meaning and commentary Al-Munawarah, King fahd Holy quran printing complex, 1410 A.H

Casson, D.A, A call to Spiritual Reformation, Priorities from Paul and this Prayers. Grand Repids:Baker Books House Company, 1992.

Crist, Jone Gil Facing the muslim challenges cape Town 7735,Life challenge Africa, 2002

Crist, Jon Gil The Texual history of the quran and the Bible villach: Light of life,Life, 1988

Dewit, David A. Answering the tough ones Chicago: The Moody Bible institute,1980

Dowell, Jose Mc Reasons why skeptics out to consider Christianity san Bernar dino: Here's
life publishers, 1981.

Dowell, Jose Mc christanity a ready defence UK: scripture press foundation, 1990

Dowell, Josh Mc and Jone Gil Christ The Islam Debate san Bernardino, Here,s life Publishes, INC.1983

Geisier, Norman Christian apologetics Grand Rapids Baker book house, 1976

Kateregga, Badru D.and David W shenk, Islam and Christianity Nairobi: Act print Ltd,1980

Nehis, Gerhard Christian answer muslims. Nairobi English press limited. 1992

Nehis, Gerhard Christian ask muslims; Nairobi; English press limited.

Rice,D.D, Evangelist John., Prayer,.. asking and receiving. Wheaton;Sword of the lord Publishess, 1945.

Shoemaker, Helen S.,Prayer and Evangelism.Taxes:Word Books,1974

Thomson, James G.S.S, The Praying Christ, Grand Rapids: Wm.B.Eerdmans Publishing Company,1959.

Torrey,R.A., Power Filled living. New Kensington: Whitaker House, 1999.

Wagner, C.Petter., The Prayer Shield, How to Intercede for Pastors, Christian Leaders and others on the Spiritual Frontlines. California: Regal Books, 1992

Holy quran (Amharic) Addis Abeba Artistic printing, limted 1968 (1961E.C)

መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም

ወንድም ሽፈራው ፈይሳ ይህንን መጽሐፍ ስጽፍ መጻፍ እንዳለበት በማሰብ ብቻ የጻፈው አይመስለኝም ። ከልጅነት እስከ ወጣትነት ከዚያም እስከ ጉልምስና የኖረውና እየኖረ ያለውን የአገልገሎት እውነታ እየተረጎመ ነው የጻፈው ። የኖረበትን ሕይወት ጽፏል ። የጻፈውንም እየኖረበት ነው። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ የአገልግሎት ልምዱ ውጤት ነው። የአገልግሎት ልምዱን ብቻም ሳይሆን የሚያምንበትን እውነተኛ የክርስትና እምነት መርሆም እንደ መሠረት ተጠቅሞበታል ስለሆነም በብዕሩ ያሰፈረው የኖረበት ሕይወት ሌሎችም እንዲኖሩበት ንግቶም ተመኝቶም ነው ብንልም ያስኬደናል። ከደራ ው ጋር ያለኝ እውቂያ በሃያ አምስት ዓመታት ስለሚቆጠር የምለው እውነት ው። በተረፈ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያነሳቸው ቁምነገሮች ከሁሉም ባለይ ማኞች ስለሚሆኑ በማንበብ እውነታውን እንድታረጋግጡ ቀዳሚ ምስክር ኜአለሁ ።

## መልካም ንባብ

ጌታቸው በለጠ
የቃለሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የኮሚዩኒኬሽንና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ ኃላፊ

ይህ ለስልጠና የተዘጋጀው «ወንጌል ለሁሉም» መጽሐፍ በወንጌል የተገለጠውን ኃይል የሚያሳይ፣ ወንጌልም ለሁሉ ሰው ማስፈለጉን በተለይም የተወሰኑ የእምነት ክፍሎች፣ አስተምሮቻቸው ምን እንደሚመስልና እንዴት የሚያድነውን ወንጌል ለእነዚህ ሰዎች መመስከር እንደሚቻል በማሳወቅ አማኝ ሁሉ የዚህ የወንጌሉ ጥሪ ተካፋይና ባለአደራ መሆኑን ያሳስባል። ስለዚህ አማኞች በግል ቤተ ክርስቲያናትም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ያላቸው ማስልጠኛዎች ለስልጠና ቢጠቀሙበት ጌታ የሰጠንን አደራና በእግዚአብሔር ኃይል በዘመናችን «የተቻለንን» እንድናደርግ ያግዘናል ።

ፈቀደ ተፈራ
የአዲስ አበባና አካባቢው
ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Designed & Printed by Andenet Printers